# ክፍል ሁለት

## የገዢው መመለስ



# ምዕራፍ አምስት

## የመንግሥቱ ዳግመኛ መወለድ

*የሰው ትልቁ የመንፈሱ መሻት ከባቢውን መቆጣጠር ነው።*

የንጉሡ የመጨረሻው ግብ ልጆቹ ከእርሱ ጋር እንዲስማሙ፣ ለእርሱ እንዲለዩና ለእርሱ የተሰጡ እንዲሆኑ ነበር፤ ለዚህም ነው መንፈሱ እንደገና በእነርሱ ውስጥ የሚኖረው። ይህንን ማድረግ የሚችለው በነቢያቱ አፍ መሲህ ተብሎ የተጠራው ዘሩ ነው። ስለ ዘሩ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ውስጥ ሲሆን፤ ከዚያም በኋላ በነቢያቱ በኢሣያስ፣ በሚልክያስ እና በሌሎችም የመንግሥተ ሰማይ ንጉሥ የሆነው ራሱ እንደሆነ ተገልጧል። የመጀመሪያው ወይም ብሉይ ኪዳን ስለ ንጉሡ የመምጣት ተስፋ ሲገልጽ አዲስ ኪዳን ደግሞ በንገሡ መገለጥ የመንግሥቱን ዳግም መወለድ ያበስራል።

የመንግሥቱ ዳግም መወለድ የሚያመለክተው የምድርን እንደገና በቅኝ ግዛትነት መያዝ ነው። አንድን አገር እንደገና በቅኝ ግዛትነት የመያዝ ነገር በሰዎች ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም የማያውቅ ወይም አልፎ አልፎ ብቻ የሚታይ ነገር ነው። በመሆኑም ንጉሡ የገለጠው ይህ እውነት እኩያ የሌለው ነው።

### የንጉሡ በምድር ላይ መወለድ

ንጉሡ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ በሰማያዊ መንግሥቱ ገዢና ሁሉን ደግፎ የያዘ እንደመሆኑ እዚያው ይሆን ዘንድ ይገባው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ገዢው እንደገና የሚመለስበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ወደ ምድር መምጣትም ነበረበት። ንጉሡ ወደ ምድር በሚመለስበት ሁኔታ ላይ የንገሡ መንፈስ ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበረው። የወንጌል ጸሐፊ የሆነው ባለመድኃኒቱ ሉቃስ፤ እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

> *"መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፤ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ። የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበር። መልአኩም ወደርሷ ገብቶ፤ 'ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፤ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት፤' እርሷም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና፤ ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?*

*ብላ አለበች:: መልአኩም እንዲህ አላት፤ 'ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ፀጋ አግኝተሻልና አትፍሪ'::*

"ከእግዚአብሔር ዘንድ ፀጋን አግኝተሻል" የሚለው የመልአኩ መግለጫ፤ ማርያም ለሰማያዊው መንግሥትና ለንጉሡ ዓላማ የተሰጠች ሴት እንደነበረች የሚያሳይ ሲሆን፤ የሰማያዊው መንግሥት በምድር ጉዳይ ላይ ጣልቃ ለሚገባበት እጅግ ወሳኝ ለሆነ ዓላማ የተመረጠችበትን ምክንያትም ያመላክታል::

*"እነሆም ትጸንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ:: እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል:: በያዕቆብም ቤት ላይ ለዘላለም ይነግሳል፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም:: ማርያምም መልአኩን፤ ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል አለችው:: መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፤ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ሃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል:: . . . ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር የለምና:: እነሆኝ የጌታ ባሪያ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች::"*

እንደገናም ደግሞ ማርያም ለሰማያዊው መንግሥት የተሰጠች ሴት እንደነበረች ሌላ ማስረጃ እንመለከታለን:: እነሆ "የጌታ ባሪያ ... እንደ ቃልህ ይሁንልኝ::"

> **ንጉሡ ልጅ ፍፁም መስኮትና ፍፁም ሰው የነበረ ቢሆንም፤ በሰው በመጸኛ ባህርይ የተመረዘ ግን አልነበረም::**

በዚህ ምንባብ ውስጥ ትልቅ እውነት አለ፤ በመንፈስ የተጸነሰው እግዚአብሔር ወልድ ወይም ንጉሡ ልጅ፤ ምድራዊ መጠሪያው በማርያም ማህፀን ውስጥ ኢየሱስ እንደተባለ ነው:: ማርያም የዘላለማዊውና የማይታየው አምላክ እንደ ሰው ወደዚህ ምድር እንዲገባ ዘሩን የተሸከመች ምትክ እናት ናት:: እንዲሁም ንጉሡ ልጅ በተፀነሰ ጊዜ በመንፈስ ተሞልቷል:: ይህም ማለት በዚህ ጊዜ ገዢው ወደ ምድር የተመሰሰው ኢየሱስ በሚባል ሰው ውስጥ ሆኖ ነው:: መላው የሰው ዘር ሊቀበለው እስኪዘጋጅ ድረስ ገዢው በኢየሱስ አካል ውስጥ ይኖር ነበር:: በዚያን ጊዜ፤ ንጉሡ ልጅ ገዢውን በመላው ዓለም ላይ የመንግሥቱን አገዛዝ እንዲያሰፍንና ለመላውም የሰው ዘር እንደገና ዜግነታቸውን ይሰጣቸው ዘንድ መልሶ ሊሾመው ተዘጋጅቷል::



ንጉሡ - ልጅ፤ ፍፁም መለኮት (እንደ እግዚአብሔር ወልድ) እና ፍፁም ሰው (ሰው እንደሆነው ኢየሱስ) ነበር:: ይሁን እንጂ በአመጸኛው በሰው ዘር ባህርይ የተመረዘ አልነበረም:: የሴቲቱ ማሕፀን ታቅዶ የተዘጋጀው፤ የእናቲቱ ደምና ገና ያልተወለደው ህፃን ደም በጭራሽ እንዳይቀላቀል ሆኖ ነው:: የኢየሱስ ደም ንጹህ ደም ነበር፤ ህይወቱም ንጹህ ነበር:: በሙሴ ሦስተኛ መጽሐፍ (ዘፀአት) ውስጥ እንደምናነበው፤ "የማንኛውም ፍጥረት ሕይወት ያለው በደሙ ውስጥ ነው:: አዳም ከማመጹ በፊት እንደ ነበረው ሁሉ፤ ኢየሱስና ማናቸውም የእርሱ ነገር ለንጉሡ አባት የተለየና የተሰጠ ነበር::

## ገዢው ንጉሡን የሰጠ በመሆኑ ንጉሡ ደግሞ ገዢውን መስጠት ይችላል

ንጉሡ - ልጅ፤ ከመንፈስ የተወለደና በመንፈሱም የተሞላ ሲሆን ያስፈልገው ነበር፤ በመሆኑም የተሰጠው የተስፋ ቃል ይፈጸም ዘንድ ለህዝቡ ገዢውን ሊሰጣቸው ይችላል:: መጥምቁ ዮሐንስ መንፈሱን እንደገና የሚመልሰው ንጉሥ - ልጅ እየመጣ መሆኑን ይፋ አደረገ:: ስለ ኢየሱስ እንዲህ ብሎም ተናገረ፤ "ከላይ የሚመጣው ከሁሉም በላይ ነው . . . ከእግዚአብሔር የተላከ እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል:: እግዚአብሔር መንፈሱን (ለእርሱ) ለፍሮ አይሰጥምና እንዲሁም እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል:: " ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤

*"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፤ እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል:: እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይችል የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ:: ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ:: ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚያም በኋላ ዓለም አያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፤ እኔ ህያው ነኝና እናንተ ደግሞ ህያዋን ትሆናላችሁ:: እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፤ እኔም በእናንተ እንዳለሁ፤ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ::"*

በመሆኑም ገዢው ንጉሡን ልጅ ለምድር ሰጥቶታልና ንጉሡ - ልጅ ደግሞ ወደ ሰማያዊው መንግሥቱ ከተመለሰ በኋላ ገዢውን ወደ ምድር ሊልከው ይችላል::

## ንጉሡ ልጅ ሙሉ ለሙሉ በገዢው የተሞላ ነበር

ንጉሡ ልጅ በሚጸነስበት ጊዜ ብቻ አልነበረም በመንፈስ የተሞላው፤ ይልቁንም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በመንፈስ መሞላቱ ቀጥሎ ነበር፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ እንደተናገረው፤ "እግዚአብሔር መንፈሱን (ለእርሱ) ለፍሮ አይሰጥም፡፡ " ከአዳምና ከሄዋን አመጽ በኋላ የሰው ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ያ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና ሃይል ገደብ የሌለው ነበር፡፡

ንጉሡን በምድር ላይ እንዲመጣ በተደረገው ዝግጅት ወቅት፤ መጥምቁ ዮሐንስ የህዝቡን መንገድ ወደ እግዚአብሔር ለማቅናት በነበረው እቅድ ህዝቡን ያጠምቃቸው ነበር፡፡ በመሆኑም ኢየሱስ ይፋዊ አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት እርሱ ራሱ ደግሞ ሊጠመቅ ወደ ዮሐንስ ሄዶ ነበር፡፡

> *"በነገውም ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፡፡ አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል፣ ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ይሆናል ብዬ ስለ እርሱ ያልኩት ይህ ነው፡፡ እኔም አላውቀውም ነበር፡፡ ዳሩ ግን ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ ስለዚህ በውሃ እያጠመቅሁ እኔ መጣሁ፡፡ ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ፤ መንፈስ ከሰማይ እንደ እርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ፡፡ እኔም አላውቀውም ነበር፤ ዳሩ ግን በውሃ እንዳጠምቅ የላከኝ እርሱ መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፤ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ፡፡ እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እመሰክራለሁ፡፡"*

ዮሐንስ ስለኢየሱስ እንዲህ ብሎ መሰከረ፤ (1) የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው እርሱ ነው (በምድር የሚኖሩ ዜጎች መንገዳቸውን ከሰማያዊ መንግሥት ጋር ሙሉ በሙሉ እንዲያስተካክሉ የሚያስችል ነበር) (2) መንፈስ ከሰማይ መጥቶ በእርሱ ውስጥ ኖረ (ኢየሱስ፣ የንገሡ - አባት ሙሉ ፈቃድ ነበረው፡፡ (3) እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር (እርሱ በቀጥታ ከንገሡ - አባት ዘንድ የመጣና ከእርሱም ጋር አንድ ነበረ)፡፡ ጳውሎስ፤ "በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነቱ ተገልጦ ይኖራልና" በማለት ጽፏል፡፡ እግዚአብሔር አባት፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው፡፡ ንጉሡ ራሱን በሦስት ልዩ ገጽታዎች ይገልጻል፤ በእነዚህ ገጽታዎች የተገለጠው የሰውን ዘር እንደገና ለማደስ ባለው እቅድ ነው፡፡

በመሆኑም ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አሉት - እርሱ ፍፁም መለኮት ነው፤ ፍፁም ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔር አባት ንጉሥ ነው፤ ሰጋ ለብሶ



ወደ ምድር የመጣው ኢየሱስም ንጉሥ ነው፡፡ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የሆነው የዮሐንስ ወንጌል እንዲህ ይላል፤ "በመጀመሪያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡" ይሁን እንጂ፤ የንጉሡ ሰው ሆኖ መምጣት የእርሱን አገዛዝ በአንድ ጊዜ በሰማይና በምድር ላይ ለማስፈን አመቺ መንገድ አልነበረም፡፡ የእርሱ ተልዕኮ በወንዶችና በሴቶች ላይ፤ በቅድስና ተሃድሶ እንዲሆንና መንፈስ ቅዱስ እንደገና በውስጣቸው ይኖር ዘንድ አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ነበር፡፡ ወደፊት እንደምናየው፣ ይህንን ማድረግ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ እርሱ ራሱ ሰው መሆን ነበረበት፡፡

> **ኢየሱስ፤ ንጉሡ ልጁን ወደ ምድር በመላክ ሰማያዊውን አስተዳደር ለመመለስ የሰጠው ተስፋ ፍጻሜ ነው፡፡**

## ንጉሡ በምድር የነበረበት ዘመን

በቀደመው ምዕራፍ፤ ኢየሱስ ይፋዊ አገልግሎቱን የጀመረው፤ "ዘመኑ ተፈፀመ ... የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች" በማለት ነው፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ለማንሣት እፈልጋለሁ፤

- ስለየትኛው "ዘመን" ነበር የሚናገረው? ለምንስ?
- እርሱ ይናገር የነበረው መንግሥት ባህርይስ ምን ዐይነት ነበር?

"ዘመኑ" የተባለው "የጌታ ቀን" ተብሎ የተጠራው ወይም ንጉሡ ልጅ ወደ ምድር በመምጣት ገዢውን ለሰዎች እንደገና የሚመልስበት ዘመን ነው፡፡ የመንግሥቱ ዓላማና ባህርይ (1) በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር አባት ጋር መታረቅ፤ በዚህም የሰው ልጆች እንደገና የእርሱ ልጆች እንዲሆኑ ማስቻል፤ (2) በገዢው መገኘትና በንጉሡ ልጆች ሕይወት በሚሠራው ኀይል አማካይነት የሰማይ መንግሥት አገዛዝ በምድር ላይ መመለስ ነው፡፡

ቅኝ ግዛት በሆነችው ምድር የሚኖሩ የንጉሡን ግዛት ምስቅልቅል አድርገዋል - ስርቆት፣ ውሸት፣ ክህደት፣ እርስ በእርስ መገዳደል፣ ከመንግሥቱ ባህርይ ውጭ ሆነው መኖራቸው፡፡ ስለዚህ እንደ ሰማያዊው ንጉሥ ልጅና ወራሽነቱ ኢየሱስ የመጣው የአባቱን ግዛት እንደገና በይገባኛል ሊጠይቅ ነው፡፡ የእርሱ ወደ ምድር መድረስ በነቢዩ ኢዩኤል "የጌታ ቀን" ተብሎ የተተነበየው መፈጸሙን የሚያመለክት ነው፡፡

ንጉሡ ልጅ፤ የአባቱን ንብረት ሁሉ እንደገና ለመጠየቅ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በቤተልሔም ተወለደ፡፡ የገና በዓል ስለ አንድ ሰማኝ መምጣት የሚያወሳ ሳይሆን፤ የባለንብረቱን መገለጥ (መድረስ) የሚያወሳ ነው፡፡ እርሱ የመጣው የምድር ባለሙብትነቱን ሊገልጥ ነው፤

ምክንያቱም መዝሙረኛው የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት እንደጻፈው፤ "ምድርና መላዋ የጌታ ናት"። እንደ ህጋዊ ባለንብረትነቱ ፍጥረትን ሁሉ መልሶ ለመውሰድ ነበር የመጣው።

> **የሰው ልጆች በዓለም ላይ ምክትል ገዢዎች ሆነው የሚታደሱት በኢየሱስ በኩል ነው።**

ንጉሡ ልጅ ወደ ምድር የመጣው ሉሲፈር ንብረቱን ይመልስለት ዘንድ ሊለምነው አልነበረም። ሉሲፈርን የሚቆጥረው እንደ ሌባ ነበር፤ እንዲህ ይለዋል፤ "ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊያርድና ሊያጠፋ እንጂ ስለሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁም መጣሁ።" እንደገናም ደግሞ "ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያ ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል" ብሏል። ንጉሡ ልጅ የመጣው ኃይለኛውን፣ ሉሲፈር ሊያስር ነው ከዚያም ቤቱን ይነጥቀውና የቤቱ ባለቤቶች ለሆኑት ልጆቹ ይመልስላቸዋል። ስለዚህ ሰው የሆነው ኢየሱስ የንጉሥ - አባት ልጁን ወደ ምድር በመላክ የሰማያዊ አስተዳደሩን እንደገና እዚህ ለመመስረት ያለው አስደናቂ ዓላማ ፍጻሜ ነው።

ጳውሎስ ኢየሱስን "የመጨረሻው" ወይም ሁለተኛው አዳም ሲል ይጠራዋል። ንጉሡ ልጅ የመጣው የመጀመሪያው አዳም ሊያደርግ ያልቻለውን ሊፈጽም ነው። የኖረው ከንጉሡ - አባት፣ ከመንግሥቱና መንግሥቱም በምድር ካለው ዓላማ ጋር ፍጹማዊ በሆነ ስምምነትና ህብረት የተሞላ ሕይወት ነው። ደቀመዛሙርቱንም ያስተማራቸው እንዲህ እንዲጸልዩ ነበር፤ "በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን።"

እንደ ሁለተኛው አዳም፣ ኢየሱስ የመጣው በሉሲፈር ከሚመራው የጨለማ አገዛዝ ሊታደገንና ወደራሳችን መንግሥት ሊመልሰን ነው። ይህንንም በምድር በሕይወቱና በሞቱ አደረገው፤ እኛም ከንጉሡ ጋር እንደ ልጆች ልንታረቅ ቻልን።

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፤ የሰው ልጆች በምድር ላይ ወደ ምክትል ገዢነታቸው እንደገና ሊመለሱ ይችላሉ። ይህም መንግሥት ልዑላዊ ገዢ በሆነው በንጉሡ መንፈስ አመራር የሚገዛ ምድራዊ መንግሥት ነው። በመሆኑም ሰማያዊው መንግሥት የነገሥታት ቤተሰብ ነው። የእስራኤል መንግሥት "የካህናትና የተቀደሰ መንግሥት" ሆኖ መስል መንግሥትነቱን እንዲገልጽ የተፈለገው ለዚህ ነው። ገዢው ከንጉሡ አባትና ከንጉሡ ልጅ ጋር የተተካከለ ቢሆንም፤ ከሰው ዘር ጋር ባለው ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱስ ንጉሥ ብሎ አይጠራውም፤ ነገር ግን መካር ወይም አጽናኝ ይለዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት የእርሱ ተልዕኮ



የሰማያዊው መንግሥት ፈቃድና ሥራ በምድር በሚኖሩ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ተጠብቆ እንዲኖርና እንዲታሰብም ጭምር ማድረግ ነው።

## ንጉሡ ልጅ ሰማያዊውን መንግሥት ለሰው ዘር እንደገና አስተዋወቀ

የኢየሱስ በምድር የነበረው ይፋዊ አገልግሎት የተጀመረው እንዲህ በሚል መግለጫ ነው፤ "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሃ ግቡ"። በምድር ላይ በነበረው የሦስት ዓመት ተኩል አገልግሎቱ ሁሉ ውስጥ ይህንኑ መልዕክት ደጋግሞ ገልጾታል። በአዲስ ኪዳን በተዘገበው ሕይወቱ ሁሉ፤ በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ ውስጥ ደጋግሞ የገለጸው ስለ "መንግስተ ሰማይ" ያለውን ማዕከላዊ (ዋና) ጭብጥ ነበር። አንዳንድ ጊዜ "የእግዚአብሔር መንግሥት" የሚል ሐረግ ይጠቀም ነበር። ምንም እንኳን እነዚህ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም መንግሥተ ሰማይ የሚለውን "ስፍራን"፣ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚለውን ቃል ደግሞ "አገዛዝ" አድርገን ልንወስደው እንችላለን። መንግሥተ ሰማይ የአገዛዙ ማዕከላዊ ስፍራ ነው፤ ይህ በዓይን ሊታይ የማይችል አገር፤ የንጉሥ - አባት መኖሪያ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ደግሞ በግዛቶቹ ላይ የዚያ አገር አገዛዝ ነው። መንግሥቱን በሚመለከት ንጉሡ ልጅ ከሰጣቸው መግለጫዎች ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው፡-

- ✓ ኢየሱስ በገሊላ ምድር ሁሉ እየተመላለሰ፤ በምኩራቦቻቸው ውስጥ አስተማረ፤ የመንግሥቱን የምስራች ወንጌል ሰበከ፣ በህዝቡ መካከል የነበረውን በሽታና ህመም ሁሉ ፈወሰ።
- ✓ "እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆነ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደቀረበች እወቁ።"
- ✓ "የእግዚአብሔር መንግሥት ባሮቹን ሊቆጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች . . ."
- ✓ "መንግሥተ ሰማይ ለወይኑ አትክልት ሠራተኞች ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት ሰውን ትመስላለች . . ."
- ✓ "መንግሥተ ሰማይ . . . . ፍሬን በጊዜው ለሚሰጥ ህዝብ ትሰጣለች።"

ሉሲፈር (ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ ተጠርቷል)፣ ንጉሡ ልጅ ከሥልጣኑ ሊያስወግደውና በምድር ላይ ሰማያዊውን መንግሥት እንደገና ሊመሠርት እንደሚመጣ ያውቃል። በመሆኑም፤ ኢየሱስን ከተግባራዊ ዓላማው ለማደናቀፍ ሲል ተፈጥሯዊ በሆኑ ፍላጎቶቹ ላይ በመመስረት በምድር ላይ አገዛዙን እንዳያሰፍን ሊፈትነው ሞክሯል። ሉሲፈር ሞክሮ

የነበረው ኢየሱስ ሰማያዊውን መንግሥት በምድራዊው መንግሥት እንዲለውጥ እንደነበር ልብ ይበሉ፤ ይህ ደግሞ በመሠረቱ አዳምንና ሄዋንን የተፈታተነበት ነገር ነበር:: ይህ ሉሲፈር ጨቋኝ አገዛዙንና አጥፊነቱን በምድር ላይ እንዲያጠናክር ያስቻለው ነበር:: ይሁን እንጂ ንጉሡ - ልጅ ለመንግሥቱ ፍፁም ታማኝ የሆነ ነበር:: በንጉሡ - አባት ቃል የሉሲፈርን ፈተና በመቃወም ተቋቋመው፤ ይህም ቃል የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ምድር ከወጡ በኋላ የተሰጣቸው ቃል ነበር:: ይህንን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የሆነው የማቴዎስ ወንጌል እንዲህ ይዘግበዋል፤

"ደግሞም ዲያብሎስ እጅግ ረዥም ወደ ሆነ ተራራ ወስደው፤ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፤ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህንን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው:: ያን ጊዜ ኢየሱስ፤ ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና አለው:: ያን ጊዜም ዲያብሎስ ተወው::"

## በመንግሥቱ ፍልስፍና መጠመቅ

የኢየሱስ በዲያብሎስ መፈተን የተከሰተው ወዲያውኑ በዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ ነው:: እጅግ ብዙ ሰዎች ስለጥምቀት እውነተኛ ባህርይና ኢየሱስ ራሱ ለምን እንደተጠመቀ በማሰብ ግራ ይጋባሉ:: ጥምቀት በብዙ ሰዎች ዘንድ ጽድቅን የመፈጸም ሃይማኖታዊ ሥርዓት እንደሆነ ቢታሰብም፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ንጉሡ ቅኝ ግዛቱ ለሆነች ምድር ካለው ፈቃድና ፍላጐት ጋር እጅጉን የተያያዘ እውነታዊ ተግባር ነው::

> አንድ ሰው በሚጠመቅበት ጊዜ፤ ሀሳቡንና ድርጊቶቹን ሁሉ ከዋናው መምህር ጋር ማስለፉን እያመለከተ ነው::

## የአንድን ሰው አስተሳሰብና የሕይወት ዘይቤ መቀየር

ኢየሱስ በምድር ላይ ይኖር በነበረበት ጊዜ፤ የተለያዩ የምኩራብ አለቆች፣ አስተማሪዎችና እንደ ሰዱቃውያን የመሳሰሉ ቡድኖች ተከታዮቻቸውን ያጠምቁ ነበር:: ጥምቀት፣ በዚህ ዐውድ ማለት በአንድ የተለየ መምህር እና በፍልስፍናው ማመንህን በይፋ የምታውጅበት ሂደት ነው:: እንደ እውነቱ፣ ሰፋ ባለ መልኩ፣ ካየነው ይህ የዮሐንስን ጥምቀት "የንስሃ ጥምቀት" ተብሎ የተጠራውን ታላቅነት ያመለክታል:: "ንስሃ ለሚለው ቃል የኛ ዘመናዊ አተረጓጓማችን የዮሐንስን ትርጉም አያስተላልፍም:: በመሠረተ ሀሳቡ፣ ንስሃ ማለት ስለሠራነው ስህተት ማልቀስ ወይም የዋይታ ጩኸት ማሰማት ማለት አይደለም:: ንስሃ ማለት በቀላሉ አስተሳሰብን መቀየር፣ ከነበረን አመለካከትና ድርጊት መለወጥ (እቅጣጫ መቀየር) ማለት ነው:: አንድ ሰው በሚጠመቅበት



ጊዜ አመለካከቱንና ድርጊቱን መቀየሩን እያመለከተ ነው፤ አመለካከቱንና ድርጊቱን፣ ይከተለው ዘንድ ራሱን ከሰጠለት መምህር አመለካከትና ሕይወት ጋር እያሰለፈ መሆኑን ያመለክታል::

ይህ ዓይነቱ የመምህርና የተማሪ የተቀራረበ ግንኙነት ያልተለመደ ነገር አይደለም:: ብሉይ ኪዳን ለዚህ ጉዳይ "የነቢያት ጉባኤ" በተጨማሪም፤ "የነቢያት ትምህርት ቤት" ተብሎ የተጠራውን በምሣሌነት ይጠቅስልናል:: እነዚህ የተለዩ ነቢያት ታዋቂ ከሆኑት ነቢያት ከኤልያስና ከኤልሣዕ ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበራቸው፣ ይረዷቸውና ከእነርሱም ይማሩ ነበር:: በአዲስ ኪዳን ዘመንም፣ ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን፣ እና ሄሮድሳዊያን ደቀመዛሙርት ነበሯቸው:: ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዓለም ውጭም፣ ተመሳሳይ የሆነ የመምህር - ተማሪ ግንኙነት እንደነበረ እናስተውላለን፤ ግሪካውያኑ ፈላስፎች ሶቅራጥስ፣ ፕላቶና አርስቶትል ተከታዮች ነበሯቸው:: እርግጥ ነው ፈላስፋ ማለት ስለ ሕይወት ያለውን የራሱን አመለካከት የሚያስተምር ነው:: ፈላስፎች ሀሳቦቻቸውን ለመማርና የሕይወት ዘይቤያቸውን ለመከተል የሚፈልጉትን ሰዎች ይማርካሉ፤ እነዚህ የፈላስፎቹን የሕይወት ዘይቤ ለመምሰል የሚፈልጉ የነሱ ተማሪዎች ወይም ደቀመዛሙርት ይሆናሉ:: ደቀመዝሙር የሚለውን በግሪክ ቃል ስንተረጉም "ጀማሪ" ወይም "ተማሪ" የሚል ቃል እናገኛለን:: ደቀመዛሙርት የመምህሮቻቸው ፍልስፍናና የእምነት ዘይቤ ከአስተማሪዎቻቸው በግል የተማሩ፤ ምናልባትም እንደ መምህሮቻቸው ያስቡና ይተገብሩ ዘንድ እየተማሩ በሚሄዱበት ሥፍራ ሁሉ አብረዋቸው የሚዞሩ ናቸው::

## የአስተሳሰብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መግባት

የአንድ ፈላስፋ ወይም መምህር ተማሪ በምትሆንበት ጊዜ በአስተሳሰቡ ትምህርት ቤት ገብተሃል ማለት ነው:: ድሮ ድሮ ት/ቤቶች ከህንፃ ጋር የተያያዙ አልነበሩም:: በመሠረቱ ት/ቤቶች ልዩ ከሆነው ከአስተማሪው ሀሣብ ጋር የተያያዙ ነበሩ:: ት/ቤቶች የሚባሉት መምህሩ ተከታዮቹና በተከታዮቹ በኩል የሚያስተላልፋቸው ፍልስፍናዊ ጽንሰ ሀሳቦቹና የአመለካከት መንገዶቹ ነበሩ::

ከዚህ አይታ አኳያ፤ የጥምቀት ዋንኛው ቁም ነገር ውሃው ወይም የመጠመቅ ተግባሩ አይደለም፤ ቁም ነገሩ ከአመለካከትህና ከሕይወትህ መቀየር ጋር ይያያዛል፣ በዋና መምህርህ ስም በምትጠመቅበት ጊዜ "አሁን ካሉት መምህራን ፈላስፎች፣ የምኩራብ አለቆችና መሪዎች ይልቅ አንተን መርጫለሁ፤ ለአንተ አስተሳሰብ ትምህርት ቤት ራሴን መስጠቴን በይፋ አውጃለሁ፤

> ኢየሱስ ዋና መምህር ነው፤ መንግሥቱ የትምህርቱ ማማያ (ማረጋገጫ) ናት::

ከአንተ ጋር ብቻ ህብረቴን አደርጋለሁ፤ እናም ማንም ሰው ባየኝ ጊዜ ‘ይህ ሰው የዚያ መምህር ሰው ነው’ ብሎ ያውቁኛል” በማለት ማወጅህ ነው።

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፤ ኢየሱስ በምድር በኖረበት ዘመን፣ በርካታ አስተማሪዎችና ፈላስፎች ነበሩ፤ የየራሳቸው አስተሳሰብ ትምህርት ቤቶችና ደቀመዛሙርት ነበሯቸው። በዘመኑ በነበረው ባህል፣ ዕድሜው ሰላሣ ዓመት ያልሞላው ሰው እንዲህ ዐይነት ትምህርት ቤቶች መጀመር አይችልም፤ ምክንያቱም ይህ ዕድሜ አንድ ወጣት ሰው በይፋ እንደ ዋና መምህር የሚሰየምበት ጊዜ ነው።

በመሆኑም፤ የሰማይና የምድር ሁሉ ፈጣሪ ራሱ ሰው ሆኖ - ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፤ በጊዜው በነበረው ባህል ውስጥ ገባ፤ ሰዎች ሕይወት ለዋጭ የሆነ መልዕክቱንና ለእርሱ ሙሉ ለሙሉ ለመታዘዝ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ሊረዱ በሚችሉበት መንገድ ራሱን አቀረበ። ኢየሱስ አገልግሎቱን በይፋ ሲጀምር ዕድሜው ሰላሳ ሞልቶ ነበር፤ የመጨረሻው (እጅግ ከፍ ያለ) ዋና መምህር ሆነ፤ እርሱን ሊከተሉ የሚፈልጉትን ተቀበለ። መንግሥቱ የትምህርቱ የተጨበጠ ማረጋገጫ (አርአያ) ነበር።

## የኢየሱስ መልዕክት ከመጥምቁ ዮሐንስ መልዕክት ጋር የተስማማ ነበር

መጥምቁ ዮሐንስ ስለመንግሥቱ የሰጠው ገለፃ ተመሳሳይ የሆነ መልዕክት እንደነበር ልብ ይበሉ። ኢየሱስ ሊጠመቅ ወደ እርሱ በሄደ ጊዜ የዮሐንስን መልዕክት ሙሉ ለሙሉ ተረድቶት ነበር። ብዙ ሰዎች በመጀመሪያ ንጉሡ - ልጅ በዋናው መምህር (በዮሐንስ) ለመጠመቅ ራሱን አሳልፎ መስጠቱን ሲያነቡ ግራ ይገባቸዋል። ይሁን እንጂ ይህንን ያደረገው የእርሱ ትምህርት ከዮሐንስ ትምህርት የተለየ እንዳልነበረ፤ ይልቁንም ሙሉ ለሙሉ ከትምህርቱ ጋር እንደሚስማማ ለህዝቡ ያሳያቸው ዘንድ ፈልጎ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ኢየሱስ ራሱ የመጥምቁ ዮሐንስ ትምህርት ፍጻሜ ነው፣ መጥምቁ ዮሐንስ እንደ የንጉሡ አባት ታማኝ ነቢይ በመሆን የመንግሥቱን መልዕክት ያወጀ ነው፣ ለንጉሡ - ልጅ በዓለም እንዲገለጥ መንገድ ያዘጋጀው እርሱ ነው።

ዮሐንስ በርካታ ደቀመዛሙርትን አፍርቶ ነበር፤ እናም ሰዎች ትሁት በሆነ ዓላማ ለንስሃ (የአስተሳሰብና የሕይወት ዘይቤያቸውን ከጨለማው መንግሥት ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመለወጥ) በመጡ ጊዜ ያጠምቃቸው ነበር። እንዲሁም ኢየሱስ ለመጠመቅ ወደ እርሱ በሄደ ጊዜ፤ ዮሐንስ ወደኋላው አፈግፍጎ፤ በእውነቱ “መምህሩ አንተ እንጂ እኔ ልሆን አይገባኝም” አለ። ዮሐንስ ኢየሱስን ገዢውን ወደ ምድር የሚልከው ንጉሥ እንደሆነ ያውቀዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ዮሐንስ ለህዝቡ እንዲህ ብሏቸው ነበር፤ “ከእኔ በኋላ ከእኔ የበረታው ይመጣል፤ ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር ልፈታ እንኳን አይገባኝም፤ እኔ በውሃ አጠመቅኋችሁ፤ እርሱ ግን *በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል*።”



ይሁን እንጂ ኢየሱስ ለዮሐንስ እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል።” ኢየሱስ እንዲህ ሲል “አንተ የእኔ ዋነኛ መምህር ለመሆን ፈቃደኛ አለመሆንህን ተረድቻለሁ፤ ይሁን እንጂ እኔ ከሰማያዊ መንግሥት ጋር ትክክለኛ ህብረት እንዳለኝ ዓለም ሁሉ ይረዳ ዘንድ፣ በዚህ ጥምቀት በኩል ህብረት እንዲረጋገጥ እፈልጋለሁ፤ እኔ ለሰማያዊ መንግሥት ትምህርት ቤት አካል መሆኔን በይፋ ማወጅ እፈልጋለሁ፣ ከመንግሥቱም አስተሳሰብና መንገዶች ጋር ሙሉ ለሙሉ ኅብረት እንዳለኝ በይፋ ማወጅ እፈልጋለሁ” እያለው ነበር።

## የመንግሥቱ ት/ቤት ወደ ኢየሱስ ተላለፈ

ዋናው መምህር (ዮሐንስ) ማስተማር ባልቻለ ጊዜ፣ ከደቀመዛሙርቱ መካከል እርሱን የሚተካው ማን እንደሆነ መወሰን ያስፈልገዋል። ማንም ይሁን ማን ይተካው ዘንድ የተመረጠው ሰው ወዲያውኑ ተማሪዎቹ የእርሱ ይሆናሉ። ኢየሱስ የአመራር ቦታውን ይወስድ ዘንድ የዮሐንስ ት/ቤት አካል መሆን ነበረበት። በመሆኑም ዮሐንስ ት/ቤቱን ሁሉ ለኢየሱስ አስተላለፈ። ደቀመዛሙርቱን ለእርሱ ለቀቀ፤ ከዚህ በኋላ ሊከተሉት የሚገባቸው እርሱን ብቻ እንደሆነ አመለከታቸው፤ ምክንያቱም ወደ መንግሥቱ እንደገና የሚመልሳቸው እርሱ ነበር። የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የሆነው የዮሐንስ ወንጌል ሁኔታውን እንዲህ ይዘግበዋል፦

> የኢየሱስን ሕይወት ስንኖር፣ መልዕክቱን ስንሰማና በዋና መምህርነቱ ስንገዛለት ተከታዮቹ ነን።

> *"በነገው ደግሞ ዮሐንስ፤ ከደቀመዛሙርቱም ሁለቱ ቆመው ነበር፤ ኢየሱስም ሲሄድ ተመልክቶ፦ እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ። ሁለቱም ደቀመዛሙርት ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት። ኢየሱስም ሲከተሉት አይቶ ዘወር በማለት፦ “ምን ትፈልጋላችሁ?” አላቸው። እነርሱም “ረቢ”፣ ወዴት ትኖራለህ? አሉት፤ (ትርጓሜውም መምህር ማለት ነው።) “መጥታችሁ እዩ” አላቸው። መጥተውም የሚኖርበትን አዩ፤ በዚያን ቀን ከእርሱ ዘንድ ዋሉ፤ ዐሥር ሰዓትም ያህል ነበር። ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምኦን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ።*

ማስተዋል ያለብን እጅግ ጠቃሚው ነገር፤ ንጉሡ - አባት ኢየሱስን የመንግሥቱ ት/ቤት የመጨረሻው ዋና መምህር አድርጎ መሾሙን ነው።

ኢየሱስ በመንግሥቱ ፍልስፍና ውስጥ እንደተደፈቀና ከመንግሥቱም ጋር እንደተሰለፈ ያሳይ ዘንድ ለዮሐንስ ጥምቀት ራሱን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ በእርሱ ላይ የሆነው ምን ነበር? መንፈስ ቅዱስ - ገዢው - በእርሱ ላይ ወረደበት። የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የሆነው የማቴዎስ ወንጌል እንዲህ ይላል፤

*"ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃው ወጣ። እነሆ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ እርግብ ሲወርድ በእርሱም ላይ ሲመጣ አየ፤ እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ 'በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው' አለ።"*

ንጉሡ - አባት፤ "መንፈስ ቅዱስ ያለው፣ እርሱ ልጄ ነው፤ እርሱም ሙሉ ለሙሉ ከአሳቤና ከመንገዴም ጋር ይተባበራል። መንፈሴን ወደ ምድር የሚመልሰውም እርሱ ነው" በማለት እያረጋገጠ ነበር። ከዚያ በኋላ፤ ንጉሡ - አባት፣ በማርቆስና በሌሎች ስፍራዎችም እንደተዘገበው፣ ደቀመዛሙርቱ ከሌሎች ከማናቸውም ይልቅ እርሱን እንዲሰሙት፤ "ይህ የምወደው ልጄ ነው፤ እርሱን ስሙት" ሲል አረጋግጦላቸዋል።

ኢየሱስ ብዙ ደቀመዛሙርት ወይም ተማሪዎች ነበሩት፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ሙሉ ጊዜአቸውን ሰጥተው አብረው እየተጓዙ ሲሠሩና በጉዟቸው ላይ ባላቸው ግንኙነትም ከሚያጋጥሟቸው ነገሮች ከእርሱ እንዲማሩ አሥራ ሁለት ሰዎችን መረጠ። ከእነዚህም ውስጥ ታዋቂዎች የነበሩት ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ ይገኙባቸዋል። ኢየሱስ የተለያዩ ደቀመዛሙርትን ሲጠራ፤ "ተከተለኝ" ነበር የሚላቸው፤ ወደ መንግሥተ ሰማይ ትምህርት ቤት እንዲቀላቀሉ ነበር የሚጋብዛቸው።

ከኢየሱስ ሕይወትና መልዕክት ለመወገን ስንወስንና እንደ ዋና መምህራችን አድርገን ራሳችንን ለእርሱ ስንሰጥ የኢየሱስ ተከታዮች ነን። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፤ "አንድ ሰው ለሁለት ጌቶች ባሪያ መሆን አይችልም። አንዱን ይወዳል ወይም ሌላውን ይጠላል፤ ወይም ለአንዱ ይታዘዛል ሌላውንም ይንቃል። እግዚአብሔርን እና ገንዘብን በአንድ ጊዜ ማገልገል አትችሉም።" ምንም እንኳን ይህ መግለጫ ስለ ገንዘብ የተነገረ ቢሆንም፤ እንዲሁ ደግሞ ሰፋ ያለ ሀሳብ አለው። በጥምቀት አውድ ውስጥ፣ "በሁለት ት/ቤቶች ውስጥ ልትሆኑ አትችሉም። እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ሁለት ዐይነት ፍልስፍናዎች ሊኖሯችሁ አይችሉም" እያለ ነው የሚነግረን።

## በእሳት መጠመቅ

የውሃ ጥምቀት የኢየሱስን ተከታዮች በመንገዳቸው ከመንግሥቱ ትምህርት ጋር እንዲሰለፉና እንዲወግኑ አድርጓቸዋል። ይሁን እንጂ ዮሐንስ፤ "በመንፈስ ቅዱስ"ና "በእሳት" "ያጠምቃችኋል" ሲል ምን ማለቱ



ነበር? በመንፈስ ቅዱስ ስለመጠመቅ በቀጣይ ምዕራፎች በዝርዝር እንነጋገርበታለን፤ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ከንጉሡና ከመንግሥቱ ጋር ለመፈረጅ ሙሉ ለሙሉ መሰጠትን የሚያመለክትና፤ የሰማዊውን መንግሥት ኃይል መቀበልን የሚያመለክት ነው። መንፈስ ቅዱስ የሰማያዊው አስተዳደር ምሳሌ ነው። በዚህ መንገድ መጠመቅ ማለት በመንግሥቱ ፍልስፍናና የሕይወት ዘይቤ ውስጥ ተዘፍቀሃል ማለት ነው። ይህም በአስተሳሰብህና በድርጊቶችህ ሁሉ ላይ ሙሉ የሆነ ተጽእኖን የሚያሳድር ነው።

ፍልስፍና የሚለው ቃል የተገኘው "ፊሎሶፎስ" ከሚል የግሪክ ቃል ነው፤ ይህም ከሁለት ትናንሽ የግሪክ ቃላት ተዋህዶ የተገኘ ሲሆን "ፊሎስ" ማለት "መውደድ" ወይም "መወደድ" ሶፎስ ደግሞ ."ጥበበኛ" ማለት ነው። ስለዚህ ፊሎሶፎስ ማለት በጥበብ የተሞሉ ነገሮችን መውደድ ወይም ማፍቀር ማለት ነው። የመንግሥቱ ፍልስፍና ደቀመዛሙርት፤ በንጉሡ አስተሳሰብና ፈቃድ ፍቅር ውስጥ ሊወድቁ ይገባቸዋል፤ በዚህም ምክንያት ሀሳቡና ፈቃዱ የእነርሱ ሀሣብና ፈቃድ ይሆናል። ድርጊታቸውም ከእርሱ ድርጊት ጋር ይመሳሰላል። ጠቢቡ ሰለሞን እንደጻፈው፤ "ሰው በውስጡ የሚያስበውን ያንኑ ይመስላል።"

> የመንግሥቱን ሕይወት መኖር የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ በንጉሡ የአመለካከት ክበብ ውስጥ መዘፈቅ ነው።

ይህ ወደ መንግስቱ አስተሳሰብና የሕይወት ዘይቤ የመሸጋገር ሂደት ሙሉ ለሙሉ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ፈጣሪው - ንጉሥ በምድር ላይ ዐምጸውብት የነበሩትን አስመልክቶ እንዲህ ሲል ገልጿል፤ "ሀሳቤ እንደ ሀሳባችሁ መንገዴም እንደ መንገዳችሁ አይደለም . . . ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል መንገዴ ከመንገዳችሁ እንዲሁ ከፍ ያለ ነው።" አስተሳሰባችንና መንገዳችን ከፈጣሪው ንጉሥ ጋር መስማማት አለበት፤ ይህንንም ማድረግ የምንችለው ሙሉ ለሙሉ በንጉሡ አስተሳሰብ በመወገን፣ ራሳችንን ለመንግሥቱ ጌታ በመስጠትና በኃይሉም በመጠመቅ ነው።

በመሆኑም የመንግሥቱን ሕይወት ሙሉ ለሙሉ መኖር የምንችለው፣ በመንፈሱ በመጠመቅ ነው። በፈጣሪው - ንጉሥ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ራሳችንን ልንዘፍቅ ይገባናል፤ ይህ ሲሆን ሁልጊዜ የእርሱን ሀሳብ ልናስብ፣ የእርሱን ሀሳብ ልንኖርና የእርሱን ሕይወት በሕይወታችን ልንገልጸው እንችላለን።

የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የሆነው የሉቃስ ወንጌል፣ ኢየሱስ በዮሐንስ ጥምቀት ከተጠመቀ በኋላ “በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ . . . ወደ ምድረ በዳም በመንፈስ ተመራ፤ ለአርባ ቀናትም በሰይጣን ተፈተነ ” ሲል ይነግረናል።

ከዚያ ልምምዱ እያንዳንዱን ፈተና በድል አጠናቆ ሲወጣም፤ ሉቃስ፣ “መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ወደ ገሊላ ተመለሰ” ብሎ ይዘግብልናል። የማቴዎስ መጽሐፍም፤ “ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፤ ‘መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና ንስሃ ግቡ’” እያለ መስበክ ጀመረ በማለት ያክልልናል። የመንግሥቱ መልዕክት እና የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ኃይል በጥብቅ የተያያዙ ነገሮች ናቸው።

> የመንግሥቱ
> መልዕክትና የመንፈሱ
> ኃይል በጥብቅ
> የተያያዙ ነገሮች ናቸው

## ንጉሡ ልጅ የመንግሥቱን አገዛዝ በምድር ላይ አሳየ

ንጉሡ ልጅ የመንግሥቱን መልዕክት ተናግሮ ብቻ አላበቃም፤ ይልቁንም መልዕክቱን ኖረው። በምድር የኖረው መላው ሕይወቱ የመንግሥቱን አገዛዝ የሚመሰክር ነበር። ኢየሱስ የተናገረው ወይም ያደረገው ማንኛውም ነገር፤ በንጉሥ - አባት አስተዳደር ፈቃድ በእርሱ ውስጥ በነበረው ገዢ ኃይል አማካይነት የተከናወነ ነበር። ይህንን እውነታ አስመልክቶ እንዲህ የሚሉ መግለጫዎች ሰጥቷል፦

- ✓ ትምህርቴ የራሴ አይደለም፤ ከላከኝ ከአባቴ ዘንድ ነው።
- ✓ የምትሰሙት ይህ ቃል ከራሴ አይደለም፤ ከላከኝ ከአባቴ ነው።
- ✓ አባቴ እስከዚች ሰዓት ድረስ ይሠራል፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ።
- ✓ እኔና አብ አንድ ነን።
- ✓ እውነቱን እነግራችኋለሁ፤ ልጅ በራሱ አንዳች ሊያደርግ አይችልም፤ የሚያደርገው አባቱ ሲያደርግ ያየውን ብቻ ነው፤ ምክንያቱም አባት ሲያደርግ ያየውን ልጅ ደግሞ ያንኑ ያደርጋል። አባት ልጁን ይወዳልና የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል።
- ✓ አባቴ የሚያደርገውን ካላደረግኩ በእኔ አትመኑ። ባደርገው ግን እኔን ባታምኑኝም እንኳን ተአምራቶቹን እመኑ። እናም አባቴ በእኔ እንዳለ እኔም በአባቴ እንዳለሁ ያን ጊዜ ታውቃላችሁ ትረዱማላችሁ።



- ✓ እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን፤ እኔን ትወዱኝ ነበር፤ እኔ ከእብ ዘንድ መጥቼ እነሆ በዚህ አለሁ። እኔ በራሴ አልመጣሁም፣ ነገር ግን እርሱ ልኮኛል።
- ✓ እኔ ከአባቴ ዘንድ መጥቼ ወደ ዓለም ገብቻለሁ፤ እነሆ አሁን ቃሉን እተውላችኋለሁ፣ ወደ አባቴም ዘንድ ተመልሼ እሄዳለሁ።

ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን ዘገባዎች ላይ ተመስርተን በከለስነው ምዕራፍ፤ ተአምራት ብለን የምንጠራቸው ነገሮች በመሠረቱ የሰማያዊው መንግሥት አገዛዝ በምድር ላይ መኖሩን አመልካች እንደሆኑ ታመልክተናል። ኢየሱስ ለፈፀማቸው ተአምራት ተመሳሳይ መርህ ልንጠቀም እንችላለን። ኢየሱስ በየትኛውም ስፍራ ታሞ የነበረን ሰው ሲፈውስ (ይህም በሰው ልጆች የዐመጽ ውጤት ላይ የመሰልጠን ኃይል ነው)፤ በሉሲፈር ወኪሎች ታስሮ የነበረን ሰው ነፃ ሲያወጣ (ይህ በጨለማው መንግሥት ላይ የመንግሥቱ ኃይል መሰልጠን ነው)፤ ጥቂቱን ምግብ በማብዛት በሺህ የሚቆጠሩትን ሲመግብ (ይህ በተፈጥሯዊው ዓለም ላይ የመንግሥቱ ኃይል መሰልጠን ነው)፣ ወይም ሰዎችን ከሙታን ሲያስነሳ (ይህ ሕይወትን የመስጠት ኃይል ነው)፣ የመንግሥቱ አስተዳደር በይፋ እንደተገለጸ ሊታይ ይችላል። እነኝህ ተግባራት ሁሉ ሰማያዊው መንግሥት በምድር ከባቢ ላይ የመሰልጠኑ ማረጋገጫ ናቸው፤ እንዲሁም የመንግሥቱ ኃይል በሁኔታዎች ላይ መሆኑን ማሳያ ናቸው። በመሠረቱ ኢየሱስ ያለውም፣ “የምታዩት ሰማያዊ አስተዳደር የሚሠራውን ነው፤ እኔም አሁን እየገለጥኩት ነው።”

## ንጉሡ - ልጅ የሰውን ልጆች ለመቤዠት እና ወደ ንጉሡ - አባትና ወደ መንግሥቱ ለመመለስ ሞተ

ንጉሡ ልጅ በምድር ላይ የነበረው ተልዕኮ፤ የመንግሥቱን መልዕክት ለማስተላለፍና አገዛዙን ለማሳየት ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን የሰው ልጆች ወደ መንግሥቱ እንደገና የሚገቡበትንና ከንጉሡ አባት ጋር የሚታረቁበትን መንገድ ለማዘጋጀት ጭምር ነበር። ልጆቹ በዐመጻቸው ምክንያት ከንጉሡ አባታቸው መለያየታቸው፤ መነገር አለበት። ሊቀደሱ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድ፤ (ከአባት ጋር የሚያደርጉት ህብረት ወይም ውስጣዊ ሙሉነትና መሰጠት) እንደገና ሊመሠረት የሚችለው በመስዋእቱ በኩል ነው።

ቀደም ሲል እንዳየነው፤ በብሉይ ኪዳን በመገናኛው ድንኳንና በመቅደሱ ውስጥ የሚቀርበው የእንስሳት መስዋእት ጊዜያዊ ነበር። የእንስሳት መስዋእት፤ ለሰው ልጆች አመጽ፣ የጥላቻና የሞት ባህል፣ ሰዎች ወደምድር ላመጡት አመፅ ሁሉ ሊከፈል የሚችል ብቃት ያለው ደም ክፍያ አልነበረም። የእንስሳት መስዋእት በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ክፉ ልብ ለዘላለም የሚለውጥበት ኃይል የለውም። የሰውን ልጆች

አመጽና የደም ማፍሰስ ለማንፃት የሚችለው የሰው ደም ብቻ ነው። ሰዎች ሰፈጸሙት ዐመጽ ሰዎችን በራሳቸው ደም ዋጋ እንዲከፍሉ ከማድረግ ይልቅ፣ ንጉሡ አባት በራሱ ደም ዋጋውን ይከፍል ዘንድ ልጁን እንደ ሰው ልጅ ወደ ምድር ላከ። በምድር የሚኖሩት ሁሉ ይቀበሉት ዘንድ የተገባውን ቅጣት ልጁ ተቀበለ፤ ይህም ከመንግሥቱ ጋር ይታረቁ ዘንድ አስቻላቸው። እንደ ሰው ስጋን ለመልበሱ የመጨረሻው ምክንያት ይህ ነበር።

ንጉሡ - ልጅ የሰውን ፍጥረት ከንጉሥ አባት ጋር ሊያስታርቅ ይችላል፤ ምክንያቱም እርሱ ቅዱስ ነበር። እንደገናም ደግሞ፣ ሰው በመሆኑ፣ ከአንድ ነገር በቀር በነገር ሁሉ እንደሌሎች ሰዎች ነበር - በእርሱ ውስጥ አመጸኝነት የለም ወይም በሰማያዊ መንግሥት ላይ የሚነሳ ሸፍጠኝነት የለበትም። ሙሉ ለሙሉ ከንጉሥ - አባት ጋር የተስማማ፣ የተሰጠና የተለየ ነበር። የኖረው በሰው አካል ውስጥ ነበር፤ ምክንያቱም የሰው ልጆች በሚያልፉባቸው የሕይወት መንገዶች ሰማለፍ በመፈለጉ ነው። እኛ የሚሰማን እንዲሰማውና የሰው ልጅ በሚያልፍበት የሕይወት ጎዳና ሁሉ ያለ ዐመጽ ሰማለፍ ፈልጎ ነበር። ኢየሱስ ገዢው በእርሱ ውስጥ የሚኖርበት ሰው ማለት ምን ማት እንደሆነ በሕይወቱ አሳይቷል። እርሱ፣ ከንጉሡ - እባትና ከመንግሥቱ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት የነበረው እውነተኛ የሰው ዘር ነበር።

ቀራኒዮ (የራስ ቅል) በሚባለው ስፍራ የተፈጸመው የኢየሱስ የመስቀል ሞት፣ ገዢው ወደምድር ይመለስ ዘንድ የንጉሡ - አባት እቅድ ነበር። በስህተት የተፈፀመ ነገር አልነበረም፤ ይልቁን የመርሃ ግብሩ አካል ነበር። በኢየሱስ በራሱ አካል ሰማያዊ መቅደስ ወደ ምድር መጥቶ ነበር። ምድራዊ የሆነው መቅደስ ከመስዋእቶቹ ጭምር አስፈላጊ አልነበረም፤ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ውስጥ ነበር። በተጨማሪም ኢየሱስ የመጨረሻው መስዋእት ሊሆን ብቁ ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ ከንጉሡ - አባት ጋር መንገዱን ያስተካከለና ፍጹም የሆነ ሕይወት የኖረ ነበር። ኢየሰ ስ ከመሞቱ በፊት የሞቱን ባህርይ እንዲህ ሲል ገልጾት ነበር፦

> “ነፍሴን ደግሞ አነሳት ዘንድ አኖራለሁና፤ ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሳት ሥልጣን አለኝ። ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀብያለሁ።”

ንጉሡ ልጅ የሰው ልጆች ስለፈጸሙት ያቀፈውና የአሁኑ ኃጢአት ዋጋ ሊከፍል ነፍሱን አኖረ። ይህ በተከፈለ ጊዜ፤ ንጉሡ - አባት እንደገና ነፍሱን ያነሣት ዘንድ ስልጣን ሰጠው፤ እናም ከሞት ተነሳ። የሕይወት ምንጭ የሆነው እርሱ መሞትን መረጠ፤ እርሱ ሰፈጠራቸው ሰዎች ባሰው ፍቅር፤ ከጨለማው መንግሥት ሊያድናቸውና እንደገና በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ ይኖሩ ዘንድ ሊያስችላቸው ፈለገ።



ጳውሎስ፤ በንጉሡ ልጅ መስዋእትነት ወደ መንግሥቱ የምንገባበትን ሁኔታ “በአዲስ ሕይወት” መመላለስ ይለዋል፤

> *“ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።”*

አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ወደሞታባት ቀን ወደ ኋላ ተመልሰው ሞቱን ሊከለክሉ ይመኛሉ። ሁላችንም ብንሆን ማንንም ሰው ቢሆን ከዚህ ዐይነቱ አሟሟት ልንታደገው እንፈልጋለን። ይሁን እንጂ የእርሱ ሞት የአባቱን ሁሉን እንደገና የማደስ እቅድ ፍጻሜ ነበር። የኢየሱስ ሞት በግዳጅ የሆነበት ሞት አልነበረም። ከመሰቀሉ በፊት፣ ሰአንድ ጊዜ፣ ሞቱን የሚሞተው በገዛ ፈቃዱ እንደሆነ እንዲሁ ሲል ገልጿል።

> *“መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ የራሴም በጎች ያውቁኛል። ነፍሴንም ስለ በጎቼ አኖራታለሁ። ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል። ድምጼንም ደግሞ ይሰማሉ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ።”*

ምንም እንኳን በጊዜው ሊገነዘቡት ባይችሉም ‘ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ፤ ስለ ሰው ልጆች አመጽ እንደሚሞት አስቀድሞ ነግሯቸዋል፤ ይህ እንዲህ በንጉሡ ነቢያት አስቀድሞ የተተነበየ ነው፣ እንዲህ ሲል “ክርስቶስ መከራን እንደሚቀበል በሦስተኛውም ቀን ከሞት እንደሚነሳ።”

በመሆኑም ኢየሱስ የተገደለው በአሳዛኝ ስህተት አይደለም። መስዋእት አድርጎ ነፍሱን ሰጠ፤ በመሆኑም ገዢው መጥቶ በእኛ ውስጥ ይኖር ዘንድ ንጹህ ሸክላዎች ሆንን። ከአብ ጋር የምናደርገው እርቅ ሁሉም ነገር ቀድሞ በነበረበት ሁኔታ እስኪስተካከል ድረስ፤ በተሃድሶው እቅድ ውስጥ በዘላቂነት ይሠራል። ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ እንዲህ አለ፤ “ተፈጸመ”። ጠላቶች ኢየሱስን አልጨረሱትም። ተልእኮውን ባጠናቀቀ ጊዜ ነፍሱን እሳልፎ ሰጠ። ከመያዙ ጥቂት ቀደም ብሎ እንዲህ አለ፤

> *“አባት ሆይ ሰዓቱ ደርሷል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ በስጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደሰጠኸው ለሰጠኸውም ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ ልጅህን አክብረው። እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ አንተን የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት። እኔ ላደርገው*

*የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርኩህ፤ አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ።"*

እንደገና፣ ኢየሱስ ረዳት አልባ የሆነ በቅናት የተንጨረጨሩ ጠላቶች ተጠቂ አልነበረም። እርሱ ኃጢአትንና ሞትን ያሸነፈ የክብር ንጉሥ ነበር። ወደ አባቱ እንዲህ ሲል መጸለዩን ልብ ይበሉ፤ "ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርኩህ።" የብሉይ ኪዳን ነቢይ የነበረው ዕንባቆም እንዲህ ሲል አስቀድሞ ተንብዮአል፤ "ውሃ ባህርን እንደሚከድን፤ ምድር የጌታን ክብር በማወቅ ትሞላለች። ኢየሱስ የተሃድሶውን ሥራ ስላጠናቀቀ የሰማያዊው መንግሥት ክብር (ባህርይ) ተመሠረተ፤ በምድርም ሁሉ ላይ ተስፋፋ።

> **ኢየሱስ የተሀድሶውን ሥራ ስላጠናቀቀ፤ መንግሥቱ በምድር ላይ ተመሠረተ፤ መስፋፋትም ጀመረ።**

## ንጉሡ ልጅ፤ በቅኝ ግዛቱ ውስጥ የነበረውን የነፃነትና የዐመጽ መንፈስ ደመሰሰው

በቀራኒዮ የተፈጸመው የኢየሱስ ሞት፤ በመስቀሉ ላይ ያፈሰሰው ደምና ከሙታን ተለይቶ መነሣቱ፤ በሰው ዘር ውስጥ የነበረውን ዐመጸኝነት ለመስበር የሚያስፈልጉ ነበሩ። "መንፈስ" የሚለውን ቃል የተጠቀምኩት አመጽ በማንኛውም ሰው ውስጥ የሚገኝ ዝንባሌ ወይም ባህርይ በመሆኑ ምክንያት ነው። አብረነው የተወለድነው፤ በውስጣችን ሥር የሰደደ ነገር ነው። ይህ የዐመጽ መንፈስ የሰማያዊው መንግሥት ተፃራሪ ነው። ታጥቦ ሲጠፋ የሚችል ወይም ቻል ሲባል የሚገባው አይደለም። መሰበር ይገባው ነበር። እናም ኢየሱስ ኃይሉን ሰበረው፤ በምድር የሚኖሩ ሰዎችም ለመንፈስ ቅዱስ ራሳቸውን ይሰጡ ዘንድ አስቻላቸው። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በስጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በእርሳቸው ይቃዋወማሉ። ስለዚህ የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከህግ በታች አይደላችሁም። "

> **በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ፤ በንጉሡ ልጅ መተማመን ሕይወትን ለመለማመድ ብቸኛው መንገድ ነው**

የነፃነትን መንፈስ መስበር በጣም አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ የፈፀመው ይህንን ነው። ኢየሱስ በምድር ላይ ሲኖር ሕይወቱ እጅግ አስቸጋሪ በሆነበት ሰዓት እርሱ ራሱ፤ "የእኔ ፈቃድ አይሁን፤ ነገር



ግን የአንተ ፈቃድ ይሁን" እንዳለ፤ ለአብ እንዲሁ ማለት እንድንችል ብቃቱን ሰጥቶናል። የአመጽ መንፈስ ለሰማያዊ መንግሥት ፍጹም በመስጠት መንፈስ እንዲተካ አስችሏል። የአብን ፈቃድ እንድንታዘዝ ችሎታን ሰጥቶናል። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ለኢየሱስ ሙሉ ለሙሉ ራስን መስጠት፤ ለአብ ሙሉ ለሙሉ ራስን እንደ መስጠት እንደሆነ ራሱ ተናግሯል፤ ምክንያቱም እርሱና አብ አንድ ናቸው። ለተከታዮቹ እንዲህ አላቸው፤ "ብትወዱኝስ፤ ያዘዝኳችሁን ትፈጽማላችሁ፣ እኔም አብን እለምናለሁ፤ ከእናንተም ጋር ለዘላለም እንዲኖር ሌላ አጽናኝ (ገገርው) ይሰጣችኋል።"

በአሜሪካ ፖለቲካ ውስጥ መራጮቹን፤ "እኔ ያልኳችሁን ሁሉ አድርጉ ብሎ የሚናገር ሰው እንደሚኖር ትገምታላችሁ? ያ ሰው እብድ እንደሆነ ሰዎች ይገምታሉ፤ ምክንያቱም እንደዚህ ያለውን እንዳናምን ተምረናል። ነገር ግን ኢየሱስ የመጣው ፍጹም የሆነውን መንግሥት ሊመልስ ነው። በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ በንጉሡ ልጅ መተማመን ሕይወትን ለመለማመድ ብቸኛው መንገድ ነው። በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ ከንጉሡ ልጅ ነፃ መውጣት ሞትን ያስከትላል፤ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ገልጾላቸዋል፤

> "በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችል እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም። እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፤ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል፤ ይደርቅማል፤ እነርሱም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሏቸዋል። ያቃጥሏቸዋልም"

ኢየሱስ የነፃነትንና የአመጸኝነትን ሀሣብ ደመሰሰው፤ የእነዚህ ነገሮች ፍጻሜም ወደ ሞት የሚያመራ እንደሆነ አሣየ። በተቃራኒው፤ በእርሱ መታመን ወደ ሕይወት ይመራል፤ ምክንያቱም "ያለ እርሱ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" ተብሎ እንደተጻፈው ነው። እንሆን ዘንድ የተፈጠርንበትን እንድንሆን፤ ይረዳን ዘንድ በእርሱ ልንተማመን ይገባናል። ጳውሎስ ይህንን ሀሣብ አስቀድሞ ተረድቶታል፤ "ፀጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ በድካም ይፈፀማል።" ጳውሎስ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጠ፤ "ስደክም ያን ጊዜ ብርቱ ነኝ (በመንግሥቱ ኃይል)።"

በመሆኑም ቁልፉ ነገር፤ ከአመጽ እጆች ነፃ መውጣት፤ ሙሉነትን እንደገና ያቀዳጃል፤ ለንጉሥ አባት የተሰጠ ሕይወትን ያመጣል፤ የመንፈስን ኃይልና ሕይወት እንዲለቀቅ ያደርጋል፤ በዚህም ንጉሡ - ልጅ ለሰዐመጸ በሞቱ አጠናቆ የሠራውን ሥራ እንድንገነዘብና

መንፃታችንንም ልንቀበል ያስችለናል:: እርሱ ያቀረበው መስዋእት በሰው ዘር ውስጥ ያለውን የዐመጻኝነት ዋጋ ሊከፍል የሚችል የላቀ መስዋእት ነበር:: መስዋእቱ የቀረበው ለሰው ዘር ሁሉ ነበር:: ለሁሉም ሰዎች አስፈላጊ የሆነ መስዋእት ነው:: ይሁን እንጂ እያንዳንዱ የሰው ዘር፤ ለኢየሱስ መንግሥት ትምህርት ቤት ራሱን ሲሰጥ የግል ውሳኔ ማድረግ አለበት፤ የዐመጽን መንፈስ ለመስበርና ሰዎች ከንጉሡ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደገና ለማስተካከል ያቀረበውን መስዋእት መቀበል አለበት:: ይህ ሲሆን ወደ መንግሥቱ ለመግባት ይችላል:: ማንም ይህንን ባደረገ ጊዜ የመንግሥቱን ባህርይ በውስጡ ይቀበላል::

## "ከእናንተ ዘንድ ይኖራል፤ በእናንተም ውስጥ ይሆናል"

ይህ፤ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ስለገገርው - የንጉሡ መንፈስ - ወደ ተናገረው መለሰ ብለን እንድንመለከት ያደርገናል፤ "ከናንተ ዘንድ ይኖራል እናም በእናንተ ወስጥ ይኖራል:: " የኢየሱስ ተከታዮች በእርሱ ውስጥ የሚኖረውን የመንፈሱን ኃይል በተጨባጭ ሁኔታ አይተዋል:: የገገርው ሥራዎች በምድር ላይ ተገልጠው ነበር፤ ይሁን እንጂ ከኢየሱስ በስተቀር በሌላ በማንኛውም ሰው ውስጥ መንፈሱ አይኖርም ነበር:: ኢየሱስ በእርሱ መስዋእትነት፣ ገገርው ተመልሶ እንደሚመጣና በእነርሱ ውስጥ እንደሚኖር ለደቀመዛሙርቱ ቃል ገባላቸው፤ በዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ 3 ዐመፅ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ተገባው ተስፋ እንደሚሆን ነው የነገራቸው:: ይህ ከመንግሥቱ ባህርይ አስተሳሰብ ጋር መስመራቸውን እንዲያስተካክሱ ብቻ አይደለም የሚያስችላቸው፤ ይልቁንም ደግሞ ኢየሱስ በምድር ላይ እንደተመላለሰ ይመላለሱ ዘንድ "ኃይልን" ይሰጣቸዋል:: ነቢዩ ኢዮኤል እንደ ተነበየው ገገርው በምድር በሚኖሩ ሰዎች ውስጥ ዳግመኛ ለመኖር ህጋዊ የሆነ የመኖሪያ ስፍራውን በቶሎ ይወስዳል::

## የንጉሡ ልጅ ወደ ምድር የመምጣት ትልቁ ምክንያት

ከትንሣኤው በኋላ፤ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፣ "አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ":: ንጉሡ - ልጅ የአገልግሎቱን - መሠረታዊ ምክንያት ደግሞ እያሳሰባቸው ነበር:: ቀጣዩ ቃል ምናልባት ጥቂት ሰዎችን ያስደነግጣቸው ይሆናል፤ ነገር ግን ልንረዳው የሚገባ ዋንኛ ነገር እንደሆነ እምናለሁ:: የእብ የተስፋ ቃል የኢየሱስ መከራ መቀበል አይደለም፤ በቀራኒዮ የሆነው ሞቱ ወይም ትንሣኤውም እንኳን አልነበረም:: ከምዕተ ዓመታት በላይ፣ ቤተክርስቲያን ለእነዚህ የክርስቶስ አገልግሎት ትልቅ ትኩረት ሰጥታቸው ቆይታለች፤ እንደ እኔ እምነት ግን ፀንቶ የተጋበት ትልቁ ምክንያት ተሰውሯል::

በዓመታት መካከል፤ ሰዎች - በተለይ ደግሞ ሃይማኖተኛ ሰዎች - አብ ለሰው ዘር የሰጠውን ተስፋ ትርጉም ለውጠውታል:: ክርስትና፣



ኢየሱስ ያደረገበትን ምክንያት ከመቀበል ይልቅ እሱ ላደረገው ነገር የሙገሣ ተግባር ሆኗል:: ኢየሱስ ፈጽሞ ያልሰጠንን መልዕክት እናውጃለን:: የተስፋውን ቃል ምድርን ለቆ ወደ መንግሥተ ሰማይ በሚሄደው ቀይረነዋል፤ የተጠራነው በውስጣችን በሚኖረው መንፈስ አማካይነት በምድር ላይ አገዛዛችንን እንደገና ልናሰፍን ነበር::

ውጤቱ ግን እንዲህ ሆነ፤ በቀራኒዮ በሆነው ተጠቃሚ ከመሆን ይልቅ ቀራኒዮን አመለክን:: የኢየሱስ መከራ፣ ሞትና ትንሣኤ ወደ ፍጻሜው የሚወስዱን መንገዶች ናቸው:: ፍፃሜው የሰው ዘር ከንጉሡ ጋር መታረቅና የመጨረሻውም የመንፈስ ቅዱስ እንደ ገና ወደ ሰዎች መመለስ ነው:: የኢየሱስ መከራ፣ ሞትና ትንሣኤ በራሳቸው የፍጻሜ ግቦች አይደሉም:: እኛ ሂደቱን ዓላማ (ግብ) አድርገናል:: የእነዚህ ተግባሮች ውጤት የአብ የተስፋ ቃል የመንፈስ ቅዱስ እንደገና መሸም ነው:: የንጉሡ - ልጅ ወደ ዓለም የመምጣቱ መላው ምክንያት፤ የሉሲፈርን ምሽግ ለመስበር፣ ከሰው ልጆች ውስጥ የዐመጸኝነትን ይዞታ ለመደምሰስ፤ ገገርው ወደ እነሱ ይመለስ ዘንድ ከንጉሡ - አባት ጋር እንደገና ግንኙነት እንዲያደርጉ ማስቻል ነው::

> የሰው ልጆች በምድር ላይ ያላቸውን ዓላማ ያሣኩ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ያስፈልጋቸዋል

ሰዎች ሁሉ መንገዳቸውን ከንጉሡ ጋር ያደርጉና በምድር የሚጠበቅባቸውን ዓላማ ያሳኩ ዘንድ የሚያስፈልጋቸው መንፈስ ቅዱስ ነው:: እንድ ነገር ልብ በሉ፤ መጥምቁ ዮሐንስ የኢየሱስን ደም ወይም ሞት ወይም ትንሳኤ ትኩረት ሰጥቶ ከቶ አልገለጸም:: ትኩረት የሰጠውና የገለጸው ስለመንፈስ ቅዱስ ነው፤ ምክንያቱም ዮሐንስ ኢየሱስ ስለመጣበት የተለየ ምክንያት እንዲህ ሲል ገልጾ ነበር፤ "እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል::" የሰው ዘር "ሃይማኖት" እየፈለገ አይደለም:: የመስዋእት አቀራረብ ሥርዓቶችና ልማዶችም አያስፈልጉንም:: የሚያስፈልገን ይህ የአብ ተስፋ በሕይወታችን እውን መሆን ነው::

ሰማያዊው አስተዳደር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንደተገለጠ በእውነት ልንረዳ ያስፈልገናል:: እርሱ በሕይወታችን ያለው የመንግሥቱ የኃይል ምንጭ ነው:: በብሉይ ኪዳን የካህናትና የነቢያት ልምምድ ሲመጣ ያለው ነገር ጥላ ነበር:: በዚያን ጊዜ፤ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ውስጥ መኖር አይችልም ነበር፤ በእነርሱ መካከል ብቻ ይሆን ነበር:: አሁን ግን፤ ኢየሱስ እንዳለው፤ "የእውነት መንፈስ ... በእናንተ ዘንድ ይኖራል በእናንተ ውስጥም ይሆናል:: "

ቀደም ብዬ እንዳልኩት፤ ኢየሱስ የሠራቸው ተአምራት፣ ሁሉም ፈውሶች፣ ማንኛውም የሥልጣን ተግባር - በውሃ ላይ መራመድ ቢሆን፣ አጋንንትን ማውጣት ወይም ለምፃሙን ማንጻት ቢሆን - የተደረጉት ለመዝናኛነት ወይም አግራሞትን ለመፍጠር አልነበሩም፤ እንዲሁም ሃይማኖትን ለመፍጠር ወይም ለስብከት የሚሆኑ ማራኪ ሀሳቦችን ለማቅረብም አልነበረም። እነዚህ ነገሮች የተከናወኑት፤ የሰማያዊ መንግሥት መንፈስ ወደ ምድር እንደተመለሰና ብዙም ሳይዘገይ እንደገና በሰዎች ውስጥ መኖር እንደሚጀምር ተጨባጭ ማስረጃ ለዓለም በመስጠት ዓላማ ላይ ተመስርተው ነው።

ኢየሱስ ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ፤ ለደቀመዛሙርቱ በርካታ መመሪያዎች ሰጥቷቸዋል፤ እነዚህም መመሪያዎች ስለንገሩው ጠቃሚ መረጃዎች የያዙ ነበሩ። እርሱ ይነግራቸው የነበረው "ከፊቴ መከራ ልቀበልባቸው ያሉ ነገሮች ሁሉ ምክንያታቸው፤ መንፈስ ቅዱስ በእናንተና ወደፊትም በሚያምኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ስለሚኖርበት ጉዳይ ነው" የሚል ነበር። በመሠረቱ ያላቸው፣ "እኔ አሁን ትቻችሁ እሄዳለሁ፤ አትፍሩ ወይም አትጨነቁ። ገዢው ተመልሶ ሊመጣ ነው፤ መጥቶም ከእናንተ ጋር ለዘላለም ይሆናል፤ ከቶ አይጥላችሁም።" የሚል ነበር።

አስደናቂውና በሚታይ መንገድ የገዢውን መመለስ የሚገልጽ ሁኔታ የተከሰተው ኢየሱስ ሕይወቱን አሳልፎ በሰጠበት ወቅት ነበር። ይህም ሰዎችን ከቅድስተ ቅዱሳን ለይቷቸው የቆየው የቤተመቅደሱ መጋረጃ፤ ከላይ ጀምሮ ወደ ታች ለሁለት መቀደዱ ሲሆን፤ የሚያሣየውም የሰው ልጆች ለመቀደስ የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታ ኢየሱስ እንደፈጸመውና አንድ ጊዜ ደግሞ እንደገና መንፈስ ቅዱስን መቀበል የመቻላቸውን እውነት ነው። ከዚህ በኋላ መንፈሱ ከእነርሱ አይለይም፤ በሁለቱ ኪሩቤሎች መካከል የእንስሳት ደም በሚረጭበት የስርየት መክደኛ ላይ ብቻ የመኖሩ ሁኔታም አብቅቷል። ኢየሱስ ተወዳዳሪ የሌለውን የደም መስዋእት በማቅረቡ ምክንያት፤ ከንጉሡ አባት ጋር በቀጥታ ይገናኙ ዘንድ ሊያስችላቸው፤ መንፈስ እንደገና ለአንድ ጊዜ በሰው ልጆች ውስጥ ባለው ቤቱ መቀመጥ ችሏል።

## የንጉሡ ግብ

መንፈስ ቅዱስን ለሰው ዘር እንደገና መመለስ የንጉሡ ፍላጎት በመሆኑ፤ የኢየሱስ የመቤዠት መርሃ ግብር እጅግ አስፈላጊ ነበር። ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበት ታላቁ ግብና ቀዳሚ ዓላማው፤ ሰማያዊውን ገዢ ቅኝ ግዛት ወደ ሆነች ወደ ምድር ማምጣት ነበር። በመሃል የሆኑት ነገሮች ሁሉ ወደ ፍጻሜው ለመድረስ የተከናወኑ ናቸው። ኢየሱስ የመጣው ወደ መንግስተ ሰማያት ሊወስደን አልነበረም፣ የመጣው መንግሥተ ሰማይን ወደ ምድር ሊያመጣ ነበር ስለዚህም ነው ዋና መምህራችን፤ እንዴት እንደምንፀልይ ያስተማረን። የጌታ ፀሎት



ብለን በምንጠራው ፀሎት ውስጥ፤ የንጉሡ አባት አገዛዝ፣ ፈቃድ፣ መሻትና ህግ በሰማይ - በአገር ቤቱ - እንደሆነ እንዲሁ በምድር - በቅኝ ግዛቱ ላይ - እንዲሆን እንድንጸልይ አስተምሮናል።

## የሮም ግዛት እንደ ሰማያዊው መንግሥት ዓይነት

በታሪክ ውስጥ ስለሰማያዊው መንግሥት ጽንሰ ሀሳብ በምድር የሚኖሩ ሰዎች አግባብ ያለው መረዳት እንዲኖራቸው፤ ለማድረግ አመቺ የነበረው ጊዜ የሮም መንግሥት በግዛቶቹ ላይ ሰልጥኖ የነበረበት ወቅት ነው። ንጉሡ - ልጅ፣ መሲሁ፣ በዚያን ጊዜ የተወለደበትም ምክንያት ይሄው ነበር። ወቅቱን ንጉሡ እንዲያው በዘፈቀደ የመረጠው ወቅት አልነበረም፣ ፍጹም ትክክለኛ የሆነ ጊዜ ነበር። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤

> *"የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ፤ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፣ ከህግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከህግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ። ልጆች ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮህ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም። ልጅ ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ'*

በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን የነበረው የሮም መንግሥት አወቃቀርና የአሰራር ስልት (ምንም እንኳን የተሰመደ ባህርይው ባይሆንም) የሰማዩን መንግሥት አሰራር የመሰለ ነበር። በፍልስጤም ውስጥ በአገዛዙ ሥር ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች ተመሣሣይነቱ ፍንትው ብሎ የሚታይ ነው። ቄሳር በሮም የሚኖር ንጉሠ ነገሥት ወይም ንጉሥ ነበር፤ እርሱ በሰማያዊው ንጉሥ ይመሰላል።

ቄሣር፤ ጲላጦስን በይሁዳ ምድር የሮምን መንግሥት ባህል እንዲያሰፍንና እንዲቆጣጠራት ወደ ይሁዳ ልኮታል። በተመሣሣይ ሁኔታም፤ ኢየሱስ ወደ አባቱ በሚመለስበት ጊዜ እንደተናገረው ገዢው ወደ ምድር ይመጣል፤ በምድር የሚኖሩ ሰዎች አንድ ጊዜ እንደገና የንጉሡን ፈቃድ ያደርጉ ዘንድ ያስችላቸዋል፤ ምድርም መንግሥተ ሰማይን ትመስል ዘንድ ያደርጋታል። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤ "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ፤ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል"፤ እንዲሁም "እነሆ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።"

እነዚህ በዘመኑ ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች እንግዳ ያልሆኑ ፖለቲካዊ ጽንሰ ሀሣቦችን ተመስርተው የቀረቡ መግለጫዎች የሚገልጹት፤ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ሰዎች የመንግሥተ ሰማይን ፈቃድና ሥራ

በውጤታማነት እንዲያከናውኑ ያስቻላቸው ዘንድ ገዢው ወደ ምድር ስለመመለሱ ነበር። የሚያስገርመው ደግሞ፤ የኢየሱስ ጠላቶች የነበሩት ሰዎች መልዕክቱ ስለ "መንግሥት" እንጂ ስለ "ሃይማኖት" እንዳልነበረ በትክክል ተገንዝበውታል። ይህም መንግሥት በንጉሡ - ልጅ አማካይነት ለንጉሥ - አባት ሙሉ ለሙሉ ታማኝ መሆንን ይጠይቃል። የኢየሱስ ጠላቶች ራሳቸውን ለሰማያዊው አስተዳደር ሥልጣን ለማስገዛት ስላልፈለጉ፤ ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር። ወደ ጲላጦስም ቀርበው "እኛ ቄሣር እንጂ ሌላ ንጉሥ የለንም" በማለት፤ ኢየሱስ በጊዜው የነበረውን የፖለቲካ ሥርዓት የሚቃወም ሰው እንደሆነ ተናገሩ።

በዚህ መንገድ፣ ጲላጦስ ንፁሁን ሰው ከመግደልና ወይም ከቄሳር የተለየ ንጉሥ ከመደገፍ አንዱን ምርጫ እንዲያደርግ ተፅዕኖ አደረጉበት። እርሱም ተጽእኖ ወዳየለበት አቅጣጫ በማዘንበል ኢየሱስ እንዲሰቀል ፈቀደ። ምንም እንኳን የኢየሱስ ሞት የተሃድሶው ዓላማ አካል ቢሆንም፤ ጲላጦስ ስለወሰደው ምርጫ ሃላፊነት አለበት። በመሰረቱ እያንዳንዱ ሰው በተመሳሳይ ምርጫ ውስጥ ያልፋል። ለሰማያዊ መንግሥት ታማኝነት ማንኛውንም ሰው ወይም ነገር የንጉሥን ቦታ እንዲወስድ አያደርገውም።

## የገዢው መምጣትና አቀባበል

ንጉሡ ልጁ ከምድር ከሄደ በኋላ፤ ገዢው ለእርሱ ተከታዮች የመስጠቱ ሂደት ይፋ ተደረገ። በቅድሚያ፣ እርግጥ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ አካል ውስጥ ይኖር ነበር - እርሱም ከአዳምና ሄዋን በኋላ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ የነበረ የመጀመሪያው ሰው ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት፤ የአይን ምስክርና ደቀመዝሙር የነበረው ዮሐንስ እንደዘገበው፤ "እርሱ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ" ይላል። ምንም እንኳን ይህ ሀረግ አንድ ሰው የመጨረሻ እስትንፋሱን መተንፈሱን የሚያመለክት ቢሆንም፤ ይህ ጉዳይ ጥልቅ የሆነ ጠቀሜታ እንዳለው እምናለሁ። "አሳልፎ ሰጠ" ለሚለው የግሪክ ቃል አቻ ፍቺው፤ "ለቀቀ" የሚል ነው። በመሆኑም ይህ ሀረግ ኢየሱስ በሞቱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን በሰማይ ላለው አባቱ የለቀቀ መሆኑን የሚያሳይ እንደሆነ አስባለሁ።

ኢየሱስ ከሞት በተነሣ ጊዜ፤ የተነሣው በመንፈስ ኃይል ነበር፤ እናም መንፈስ እንደገና አደረበት። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፤ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ፤ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፤ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል"። ልክ ንጉሡ - ልጅ በመንፈስ ኃይል ከሙታን እንደተነሣና መንፈስ በርሱ እንዳደረ፣ በንጉሡ - ልጅ መስዋዕትነት በኩል ወደ መንግሥቱ የሚገቡ መንፈሱን ይቀበላሉ።



በኢየሱስ ትንሳኤ መንፈስ ቅዱስ በአመጽ፣ ግራ በመጋባትና በተስፋ ቢስነት ከጨለማው መንግሥት በታች ይኖሩ ወደነበሩ የሰው ልጆች ለመመለስና ሊታደጋቸው ዝግጁ ሆኖ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ምድር በተፈጠረ ጊዜ ከባዶነት ውስጥ ሕይወትን እንዳወጣና ምስቅልቅል ለነበረው ነገር ሁሉ ሥርዓትን እንዳበጀለት ሁሉ፤ መንግሥቱ ወደ ምድር ዜጎች ሲመለስ በነሱ በኩል ምድርን አንድ ጊዜ እንደገና ወደ መንግሥተ ሰማይ ቅኝ ተገዢነት ይለውጣታል።

# ምዕራፍ ስድስት

## ንጉሡ ለዜጎቹ ያለው ፍቅር

*ፍቅር የንጉሡና የመንግሥቱ ባህርይ ነው።*

በበጎ ፈቃድ የሚደረግ የፍቅር ገደብ

የመንግሥቱን ባህርይ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት የሚያስችል ዕድል አለን፤ በዚህም በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ያልተገባቸውን ፍቅር ሊሰጣቸው ንጉሡ - ልጅ ወደ ምድር ለመምጣት የነበረውን ታላቅ መነሣሣት ልንመሰከት የግድ ነው። በዓለም ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ከልክ በላይ ስለወደደ፤ ወደ መንግሥቱ ይመልሳቸው ዘንድ፤ ራሱን በተገደበ ሁኔታ ውስጥ ሊወስን ፈቃደኛ ሆነ። የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ጸሐፊ የሆነው ዮሐንስ፤ በወንጌል መልዕክቶች ውስጥ ታዋቂ ከሆኑት መግለጫዎች አንዱ የሆነውን ክፍል እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፤ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና"። ፍቅር የንጉሡ - አባት እና የንጉሡ - ልጅ ባሕርይ ነው።

ኢየሱስ በሰው መልክ የተገለጠ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር መገለጫ ነው። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ሊያሳየን፤ ንጉሣችን ብቻ ብለን ልንጠራው ሳይሆን እንደገና ደግሞ አባታችን ብለን ልንጠራው እንድንችል እና ያለ አግባብ እንዳንፈራው (እንድንቀርበው) ሊያደርገን ነው የመጣው። ምክንያቱም በእርሱ ውስጥ ያለው ያው መንፈስ በእኛም ውስጥ ደግሞ አለ።

## የገዢው ገደብ

የንጉሡ - ልጅ በፈቃደኝነት ራሱን የመገደቡ ሁኔታ፤ ከሰው ልጆች ማመጽ ጀምሮ ገዢው በምድር በሚኖሩ ሰዎች ውስጥ ሲሠራ ከተገደበባቸው ሁኔታዎች የመነጨ ነው። ቀደም ሲል እንደገለጽነው፤ ገዢው በብሉይ ኪዳን ዘመን በሰዎች ላይ ይመጣ የነበረው የመንግሥቱን ሥራ በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ለማከናወን ነበር። ገና በሰዎች ውስጥ ሆኖ መስራት አልቻለም ነበር። የእግዚአብሔር ልጅ ሰው በሆነው ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፤ መንፈስ በእርሱ ውስጥ ሆኖ በምድር ላይ ለመኖር ቻለ። ይሁን እንጂ ገዢው ገና በሰዎች ሁሉ ውስጥ መኖር አልቻለም ነበር።



የንጉሡ - አባት እቅድ፤ በንጉሡ ልጅ ስጦታ በኩል ለሚቀበሉት ለሰው ልጆች ሁሉ ገዢውን መልቀቅ ነው።

## ንጉሡ ልጅ ራሱን የገደበው ዳግመኛ ላለመገደብ ነው

የኢየሱስ ትምህርቶች ትልልቅ እውነቶችን በያዙ አይአዎች (አዎን-አይደለም) የተሞሉ ነበሩ። ለምሣሌም ያህል፤ አንድ ሰው የዘላለምን ሕይወት ለመኖር ከፈለገ መሞት አለበት፣ በመንግሥቱ ኃይል ብርቱ ለመሆን፤ ማንነቱ መድከም አለበት። ራሱን በፈቃደኛነት በመገደብ ይህንን የአይአዎ ሕይወት የኖረው፣ በተከታዮቹ ሕይወት ውስጥ ያልተገደበ ሆኖ ለመኖር ይችል ዘንድ ነው - ተከታዮቹም የንጉሡ ልጆች ለመሆን የበቁትና በውስጣቸው ገዢውን የተቀበሉት ናቸው። ኢየሱስ ራሱን የገደበው በሚቀጥሉት መንገዶች ነበር። እርሱ . . .

- ✓ እኛ ሙሉ እንሆን ዘንድ ራሱን ባዶ አደረገ፤ እኛ ባለጠጎች እንሆን ዘንድ ደኸየ።
- ✓ ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ሊያገናኘን ይችል ዘንድ፤ ራሱን ከዓለም የስፍራና የጊዜ ውስንነት በታች አስቀመጠ።
- ✓ ከህግ በታች የነበርነውን ነፃ ሊያደርገን ከህግ በታች ሆነ።
- ✓ የዘላለም ሕይወት ይኖረን ዘንድ ለፍጥረታዊ ሞት ራሱን አሳልፎ ሰጠ።

ጳውሎስ በፊልጵስዮስ ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ልጆች ስለ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ጻፈ፤ "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ፤ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም። ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፤ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፤ ለሞትም ይኸውም እስከ መስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ።"

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁሉ የሚገልጡት ንጉሡ ልጅ በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ያለውን ፍቅር ነው። እነዚህን ነገሮች ያደረገው ገዢውን እንደገና ወደ እኛ ለመላክ ነበር፣ በእኛ ውስጥ ያለ ምንም ገደብ እንዲኖር። *መንፈስ ቅዱስ፣ ኢየሱስ በምድር የጀመረውን አገልግሎት ይቀጥላል። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤*

> *"እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይችለው የእውነት መንፈስ ነው። ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር፤ በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።"*

እስኪ አሁን ደግሞ ንጉሡ ልጅ ስለ እኛ ሲል ራሱን የገደበባቸውን መንገዶች በጥልቀት መመልከት እንጀምር።

## ራሱን ከክብር ገደበ

በቆሮንቶስ ይኖሩ ለነበሩ ተከታዮች ጳውሎስ በጻፈው መልዕክቱ እንዲህ ብሏል፤ "የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ እውቃችኋልና፤ ሀብታም ሲሆን እናንተ በእርሱ ድህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሃ ሆነ።" ንጉሡ - ልጅ ከሰማያዊ ኃይሉ፤ ክብሩና ባለጠግነቱ ራሱን ባዶ ያደረገው፤ እንደ ፍጥረታዊና ምድራዊ ለሁሉ ነገር በመንፈሱ በኩል በንጉሡ አባት ላይ ጥገኛ ሆኖ ለመኖር ነበር። ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ልጅ በራሱ አንዳች ሊያደርግ አይችልም፤ የሚያደርገው አባቱ ሲያደርግ ያየውን ነገር ብቻ ነው፤ ምክንያቱም አባቱ የሚያደርገውን ልጅ ደግሞ ያንኑ ያደርጋል።"

የእግዚአብሔር ልጅ ሰው በሆነ ጊዜ፤ ለጊዜውም ቢሆን የቀደመ ክብሩን ትቷል። ከመሞቱ ጥቂት አስቀድሞ ኢየሱስ እንዲህ ጸለየ፤ "አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር፤ አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ። አባቱ ለአጭር ጊዜ እንዲለወጥ ባደረገው ወቅት የክብሩን ብልጭታ ለማየት እድል ያገኙት ከኢየሱስ ደቀመዛሙርት መካከል ሦስት ብቻ ነበሩ፤

> *"ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረዥም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ፤ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፤ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩዋቸው። ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፦ ጌታ ሆይ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ በዚህ ሦስት ዳስ፤ አንዱም ለአንተ አንዱም ለሙሴ አንዱም ለኤልያስ እንስራ አለ። እርሱም ገና ሲናገር እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፤ እነሆም ከደመናው፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምጽ መጣ።"*

የዚህ ውጤት በጴጥሮስ፣ በያዕቆብና በዮሐንስ ስሜት ላይ የፈጠረው መበረታታት ቀላል አልነበረም። ልጁ ይህንን ታላቅ ክብሩን ወደ ጎን ያደረገው በምድር ላይ የነበረውን ተልዕኮ ይፈጽም ዘንድ ነበር።

## በጊዜና በስፍራ ራሱን ገደበ

ዘላለማዊው ንጉሡ - ልጅ እንደገና ራሱን በጊዜ ውስጥ ይገደብ ዘንድ ፈቅዶ ነበር። በምድር በነበረው የሠላሣ ሦስት ዓመት ሕይወት፤ የግዝፈ-ዓለሙ ሁሉ ባለቤት ሆኖ ሳለ በትንሽ ፕላኔት ውስጥ ትንሽ በሆነች ግዛት ራሱን ገደበ፤ በዚህም በአንድ ጊዜ በአንድ ስፍራ ለመገኘት ብቻ



ነበር የቻለው። እዚያው ኖረ፣ እዚያው ሞተ፣ እንደገናም እዚያው ተነሣ፤ ወደ ሰማይ ያረገውም እንኳን ከዚያው ስፍራ ነበር። ዘላለማዊነት ራሱን በጊዜ ውስጥ ለመገደብ ፈቀደ፣ በመሆኑም በጊዜ ውስጥ ያሉት እነዚያም እንደገና ዘላለማዊ ከሆነው መንግሥት ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላሉ።

## ከህግ በታች ራሱን ገደበ

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፤ ከህግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከህግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ፤" የሙሴ ህግና የመስዋእቱ ሥርዓቶች የተመሠረቱት ከንጉሡ ጋር ለተለያዩት ነበር። ኢየሱስ ከሰማያዊው አባት ጋር ሙሉ የሆነ ግንኙነትና ህብረት ነበረው፤ ይሁን እንጂ ህጉ የሚጠይቀውን ሁሉ ለመፈጸም ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እናም ሙሉ ለሙሉ ፈጸማቸው። በራሳችን በኩል የሚጠበቅብንን ድርሻ ማለትም ፍጹም የሆነውን መስዋዕቱን ስንቀበል፤ በውስጣችን በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ በኩል እግዚአብሔርን ልንታዘዘው እንችላለን። የነቢዩ የሕዝቅኤል መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤

> "አዲስንም ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስንም መንፈስ በውስጣችው አኖራለሁ፤ ድንጋዩንም ልብ ከውስጣችሁ አወጣለሁ፣ የስጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴን በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ በትዕዛዜም አስኬዳችኋለሁ፤ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉማላችሁ። ህዝብም ትሆኑኛላችሁ፣ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ።"

በተጨማሪም ኢየሱስ በዚህ ፍጥረታዊ ዓለም ውስጥ ለተፈጥሮ ህግ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል። እግዚአብሔር የሚደክም አካል ኖሮት መገመት ትችላላችሁ? ሲራብስ? ሲጠማስ? ዓለማትን ሁሉ የፈጠረ ውቅያኖሶችን፣ ባህርንና ወንዞችንም የሠራ፤ ያጠጣው ዘንድ አንድን ሰው ውሃ ለምኗል። ዛፎችን የፈጠረ ፍሬ እንዲያፈሩም ያደረገ ከእርሱ ይበላ ዘንድ ወደ አንድ ዛፍ ተጠግቷል። ዘማሪው፤ "አይተኛም፣ አያንቀላፋም" ያለለት እግዚአብሔር ዕረፍት ማድረግ አስፈልጎታል። እውነቱን ለመናገር ኢየሱስ አንድ ጊዜ እጅግ ከመድከሙ የተነሣ በኃይለኛ ወጀብና ዐውሎ ነፋስ በተጋለጠበት ሁኔታ ውስጥ ተኝቶ ነበር! የመግዛትን ኃይል ለሰው ዘር መልሶ ይሰጥ ዘንድ ለጊዜውም ˊ ሊሆን ፍጥረታዊ ለሆነው መገደብ ራሱን አሳልፎ ሰጥቶ ነበር።

## በሞት ራሱን ገደበ

የሕይወት ሁሉ ምንጭ በሞት አይኖች ፊት አልፏል። ፊት ለፊት ተጋፈጠው፣ ራሱንም አሳልፎ ሰጠ። በመጨረሻም አሸነፈው፤ ከሰው ልጆች ላይም መውጊያ መርዙን አስወገደ። ነቢዩ ኢሣያስ እንደተናገረው፣

ንጉሡ - ልጁ መሰቃየቱና መሞቱ ንጉሥ - አባትን አስደስቶት ነበር:: ያንን መከራ ጭንቀትና ሞት ልጁ በመቀበሉ ያስደሰተው ለምን ነበር? እንደገናም ምክንያቱ በምድር የሚኖሩ ሰዎች በዐመጻቸው ሳቢያ መንፈሳዊ ሞት እንዲያገኛቸው ባለመፈለጉ ነበር:: በዚህም ምክንያት በእኛ ምትክ በፈቃደኝነት ሞተ:: ፍጥረታዊ የሆነ አካል ሊገደብና ሞትንም ለመቅመስ ራሱን ለመገደብ በራሱ ፈቃደኛ ሆነ፤ ምክንያቱም ደግሞ ለሌላው የሰው ፍጥረት እውነተኛ ምትክ ይሆን ዘንድ ብቻ ነው:: ጳውሎስ እንዲህ ጽፏል፤ "የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም ሕይወት ነው::" ኢየሱስ ኃጢአት አልነበረበትም፤ ነገር ግን ኃጢአታችንን ሁሉ ተሸከመ፤ እናም ለዚህ ነው እርሱ - ፍጹሙ ሰው፤ ሁለተኛው አዳም - የሞተው::

> የንጉሡ ልጅ በሞት መገደብ ለኛ ያልተገደበን ሕይወት አመጣልን

ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከሞት ተነሣ፤ እንደገና በጭራሽ በሞት አይገደብም:: እንደዚሁ ሁሉ፣ እኛ ወደ መንግሥቱ በገባን ጊዜ፤ የዘላለምን ሕይወት እንቀበላለን፤ ለዘላለሙም ሞት በመቃብር ይዞን ሊያቆየን አይችልም:: እንደገናም ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "በገዛ ኃይሉም እግዚአብሔር ጌታን ከሞት አስነስቶታል፤ እንዲሁ ደግሞ እኛ ንም ያስነሣናል":: የልጁ በሞት መገደብ ለኛ ያልተገደበን ሕይወት ወደ እኛ አመጣ:: ሞት በፍጻሜው በእኛ ላይ ሊሰለጥን አይችልም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በእኛ ላይ የነበረውን የሞት ቅጣት ዋጋ ከፍሏል:: ጳውሎስ እንዳለውም፤ "እኛ በእርሱ ሆነን ለእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ፤ ኃጢያት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢያት አደረገው::" በዚህም የዘላለምን ሕይወት ልንቀበልና ለመንግሥቱም ፍጹማን እንሆን ዘንድ ችለናል::

ይህ በቅርብ በምናውቃቸው ምድራዊ መሪዎችና በሰማያዊው ንጉሥ መካከል ያለ ሌላው ግልጽ ልዮነት ነው:: ዜጐቻቸውን ነፃ ለማውጣት ሲሉ በቢሮአቸው ውስጥ የሞቱ ፕሬዚዳንቶች ወይም ጠ/ሚኒስትሮች ተሰምተው አይ ታወቅም:: ምናልባትም ስለ ህዝቡ በመቆሙ ወይም ያለበቂ ምክንያት ወይም በጥላቻ በሰዎች ሊገደል ይችላል:: ግን ስለ ዜጐቹ ለመሞት የመረጠስ? በእኛ ዘመን ይህ ተሰምቶ የሚያውቅ አይደለም:: የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የሆነውን የዮሐንስን ቃል አስታውሱ፤ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና::" ኢየሱስ ራሱን ስለሰዎች አሳልፎ የመስጠቱን ጉዳይ፤ ስለበጎቹ ራሱን አሳልፎ ከሰጠ እረኛ ጋር ያመሳስለዋል:: "መልካም የበጎች እረኛ እኔ ነኝ፡ አባቱ እንደሚያውቀኝ እኔም እርሱን እንደማውቅ በጎቼን



አውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ደግሞ ያውቁኛል፤ ስለ በጎቼም ነፍሴን አኖራታለሁ::" ሞቱ ስለ ህዝቡ ያለው የእውነተኛ ፍቅር መግለጫ ነው::

## የማይገደበው መንግሥት አገዛዝ ተስፋ

ኢየሱስ ራሱን መገደቡ፤ የማይገደበው የመንግሥቱ አገዛዝ በምድር ላይ እንደገና ይሰለጥን ዘንድ አስችሏል:: አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ዛሬ በምድር ላይ ቢኖር እያሉ በከፍተኛ ጉጉት ሲናገሩ እሰማለሁ:: እርሱ በዚህ ቢኖር ኖሮ፣ በግላቸውም ቢያገኙት፤ ሕይወታቸው የተለየ ሊሆን እንደሚችል ያምናሉ:: ምናልባትም እናንተ እያሰባችሁ ያላችሁት ልክ እንደዚህ ነው፣ እኔም እንዲሁ አስብ ነበር:: ነገር ግን እኔ ይህ መጥፎ የሆነ ምኞት እንደሆነ ለማየት ችያለሁ፤ ነገሩ የእኛ መልካም ፈቃድ ጉዳይ አይደለም:: የሕይወታችን መለወጥ እውን የሚሆነው ኢየሱስ በአካል በምድር ባለመኖሩ ምክንያት ነው::

ይህ የሆነው ለምንድን ነው? በመጀመሪያ ከምክንያታዊነት አንጻር ነገሩን እንመልከተው፤ ኢየሱስ በአካል በዚህ ቢኖርና ልትጎበኘው ብትፈልግ ወደ ፖለስታይን (ፍልስጤም) ለመሄድ የሚያስፈልግህን የአይሮፕላን የመጓጓዣ ወጪ መክፈል ይኖርብሃል:: እዚያ ከደረስክ በኋላም ወደ እርሱ ለመቅረብ በዙሪያው በሚታራመስ ህዝብ መካከል እያቆራረጥክ መሄድ ይኖርብሃል:: ከዚያም በኋላ ደግሞ ጊዜውን ሁሉ ከአንተ ጋር እንዲያጠፋ ተስፋ አታደርግም:: በሚሊዮን ወይም በቢሊዮን የሚቆጠሩትን በየቀኑ ከእርሱ ጋር መገናኘት የሚፈልጉትን ሰዎች አስብ:: ነገሩ እንዲህም ሆኖ እያለ እንኳን የኢየሱስን በምድር ላይ የመገኘቱን ሀሣብ አጥብቀን ይዘን እንፈልገዋለን:: ይህ የሆነበት ምክንያት ገዢው በየትኛውም ጊዜ ለሰዎች ሁሉ ለመገኘት የተዘጋጀ መሆኑን ያለመገንዘባችን ነው::

የኢየሱስ ደቀመዛሙርትም እኛ የምንሠራውን ዐይነት ስህተት ሰርተዋል:: ንጉሡ - ልጅ ለተከታዮቹ ምድርን ትቶ በሰማያዊ ቤቱ ወዳለው አባቱ ሊሄድ እንደሆነ በነገራቸው ጊዜ ደስተኞች አልነበሩም:: ከኢየሱስ አካላዊ መገኘት ጋር ሕይወታቸውን አቆራኝተው ስለነበር፤ ያንን ግንኙነት ማጣትን ፈሩ:: ይሁን እንጂ ለዚህ አመለካከታቸው ኢየሱስ የሰጠውን ምላሽ እንመልከት፤

> ገዢው በመጣ ጊዜ ሁልጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ከነርሱ ጋር ይሆናል::

"አሁን ግን ወደላከኝ እሄዳለሁ፤ ከእናንተም፡- ወዴት ትሄዳለህ ብሎ የሚጠይቀኝ የለም:: ነገር ግን ይህን ስለተናገርኳችሁ ሀዘን በልባችሁ ሞልቷል:: እኔ ግን እውነት

እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና። እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። "ጥቂት ጊዜ አለ አታዩኝም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ ታዩኛላችሁ።"

ኢየሱስ ይህን የተናገረው፤ ሁልጊዜም ከእነርሱ ጋር ይሆን ዘንድ ገዢውን እንዲልክላቸው ወደ ሰማይ መመለስ ስለሚገባው ነበር። ኢየሱስ ትቷቸው ከሄደ ዳግመኛ አያዩትም፤ ነገር ግን ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ገዢውን ከመንግሥተ ሰማይ ሲልክላቸው፤ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራቸውና ኢየሱስ የተናገራቸውን ሁሉ የሚያሳስባቸው መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥ ያድራል።

ገዢው በሚመጣበት ጊዜ፤ ከእነርሱ ጋር ሊሆን የሚችለው በተገደበ መንገድ አይደለም፤ ለምሣሌም ኢየሱስ በጊዜና በስፍራ ተገድቦ አንድን ሰው ያገለግል እንደነበረ ወይም ወደ አባቱ ይጸልይ እንደነበረው አይደለም። ገዢው ያለማቋረጥ ከእነርሱ ጋር ይሆናል፤ ቀንም ይሁን ሌሊት፣ ደግሞም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ አብሮ ይሆናል። ቀድሞ ግን፣ ኢየሱስ በሰማርያ ከሆነ በገሊላ ሊገኝ አይችልም። በኢየሩሳሌም ውስጥ ከሆነ በቢታንያ ውስጥ ሊሆን አይችልም ነበር።

ወደ መንግሥተ ሰማይ በመሄዱ ደስተኞች ልንሆን ይገባናል፤ ምክንያቱም አሁን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፣ በመንግሥቱ ዜጎች ሁሉ ውስጥ በሚኖረው፣ መንግሥቱ በአንድ ጊዜ በዓለም ሁሉ ላይ ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ፣ እንዲህ ባለው ቃል፣ ለደቀመዛሙርቱ አረጋግጦላቸዋል፤ "የእኔ መሄድ ለእናንተ ጥቅም ነው። አሁን ገዢው ከእናንተ ጋር ነው፤ ነገር ግን በእናንተ ውስጥ ይሆናል።" በአካል ሆኖ በምድር ላይ መቆየት የኢየሱስ ዓላማ አልነበረም፤ ምክንያቱም ይህ በገዢው ወደ ምድር መመለስ የሚፈፀመውን የንጉሡን የተሃድሶ እቅድ የሚገድብ ስለሆነ ነው።

ኢየሱስ በተያዘና በተሰቀለ ጊዜ፤ ሉሲፈር ይህንን የሚፈልገውን ድል በንጉሡ ላይ የተቀዳጀ እንደሆነ አስቧል። እውነቱ ግን ፍጹማዊ ወደ ሆነ ሽንፈት ውስጥ ገብቶ ነበር። ኢየሱስ ወደ መስቀል ሞት ባይጓዝና ከሞትም ባይነሣ ኖሮ፤ አሁንም በአመጽና በጨለማው መንግሥት ወጥመድ ውስጥ እንወድቅ ነበር። ኢየሱስ ሰማያዊ ወደሆነው አገር ቤቱ ባይመለስና እንድንሞላ ገዢውን ባይልክልን ኖሮ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ወደ ምድር መመለስ አይችልም ነበር። ይህን አስመልክቶ ኢየሱስ ይህንን የሚመስል ቃል ተናግሯል፤ "እኔ ወደ መስቀል የወጣሁ እንደሆነ፤ ሰዎችን ሁሉ ወደራሴ ልስብ ወደ መንግሥቴም ላመጣ እችላለሁ። በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችንም አስቀድሞ ወደተፈጠሩበት መንግሥታዊ ወደሆነው ማስተዳደርና የመግዛት ዓላማ አመጣቸዋለሁ።"



ኢየሱስ በድርጊቶቹ በብዙ መንገድ ራሱን ገድቧል፤ ይህን ያደረገውም ከንጉሡ አባታቸው ጋር ተራርቀው ለነበሩ ልጆቹ በነበረው መስዋእትነት የተሞላ ፍቅርና ራሱን ሙሉ ለሙሉ አሳልፎ ለመስጠት በነበረው ፈቃድ ነው።

## ዋጋው ሊታመን የማይችል ለሰው ዘር የተሰጠ ስጦታ

እስካሁን ድረስ እንዳየነው በምድር ላይ ዋና (ከፍተኛው) ገዢ መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱም የሰማያዊው መንግሥት ገዢ ነው። ዋጋ ሊተመንለት የማይችል ለሰው ዘር የተሰጠ ስጦታ ነው፣ እናም ንጉሡ - አባት ገዢውን እንደገና ወደ እኛ በመመለሱ ደስተኛ ነው። ሐኪሙ ሉቃስ፣ እየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል እንደተናገራቸው ዘግቧል፤

"እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ (በጨለማው መንግሥት ቁጥጥር ስር ሆናችሁ) ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፤ በሰማይ ያለው አባት (የብርሃን መንግሥት ገዢ) ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው!" በተጨማሪም ደግሞ፤ "መንግሥትን ይሰጣችሁ ዘንድ የአባታችሁ ደስታ ነው" ብሏል።

በሚቀጥለው ምዕራፍ፤ ገዢው እንዴት ወደ ምድር እንደተመለሰ እናያለን።

# ምዕራፍ ሰባት

## ግንኙነቱን ማደስ

*የአንድ ተክል መጻኢ እድል ከአፈሩ ጋር ተጣብቆ በመቆየቱ ላይ የሚወሰን ነው::*

ንጉሡ ልጅ ገዢውን አስመልክቶ፤ "በእናንተ ውስጥ ይኖራል፤ በእናንተም ዘንድ ይሆናል" ሲል ለደቀመዛሙርቱ ቃል ገብቶላቸዋል:: በመንፈስ ቅዱስ በኩል ከአብ ጋር ያገናኛቸዋል፤ ከትንሣኤው በኋላ፣ የሰው ዘር ገዢውን እንዲቀበል የማዘጋጀቱ ሥራ ተፈጽሟል:: የዐመፅና የነፃነት መንፈስ ከመንግሥቱ ተሰብሯል:: የኢየሱስን መስዋእትነት በግሉ የተቀበለ፤ በሕይወቱም የተገበረው ማንኛውም የሰው ልጅ አሁን ነጽቷል፤ የገዢው መኖሪያ ይሆን ዘንድ ብቁ ሆኗል::

### የኢየሱስ እስትንፋስ

የኢየሱስ ሕይወት፣ አገልግሎት፣ ሞትና ትንሣኤው በምድር ላይ ሊተገበር ወዳለ ወደ አንድ ትልቅ ሥራ ገዢውን ወደ መስጠት ተግባር - አምርቷል:: ከትንሣኤው በኋላ ብዙም ሳይቆይ፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ተሰብስበው ወደነበረበት ክፍል መጥቶ እንዲህ አላቸው:: "አባቴ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ፤" ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" አላቸው::

ኢየሱስ "እፍ" እንዳለባቸው አስተውሉ:: እንዲህ አይነቱ ድርጊት የተለመደ ይመስላል? ይህ ጉዳይ ፈጣሪ በመጀመሪያ አዳምን ህያው ነፍስ አድርጎ ሲፈጥረው ካደረገው ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው:: "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ህያው ነፍስ ሆነ::" ይሁን እንጂ በዚህ ሕይወትን በመስጠት ተግባር፣ ንጉሡ - ልጅ ምን እያደረገ እንደሆነ ለይቶ ገልጿል:: እንዲያው ዝም ብሎ "የሕይወትን እስትንፋስ ተቀበሉ" አላላቸውም፤ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" ነበር ያላቸው::

የሕይወት እስትንፋስ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ገዢው የሰው ዘር ሕይወት ነው:: ምንም እንኳን ለተወሰነልን ዘመን በአካል መኖር ብንችልም፤ ያለ መንፈስ ቅዱስ ለመንግሥቱ፤ ልንኖርበት ለተፈጠርንበት ለሰማያዊ አገዛዝና ለራሱ ለፈጣሪው ንጉሥ ሙታን ነን::



በሌላ አባባል፤ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወደ አዳም እፍ ሲል፤ በመሠረቱ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበል" ማለቱ ነበር:: አሁን ደግሞ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ለመሞላት (ከእርሱ ከራሱ በቀር) እንደ የመጀመሪያ የሰው ልጆች ለተቆጠሩት፣ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" አላቸው:: በእንግሊዝኛ ቋንቋ ceive "ተቀበል" የሚለውን ቃል እንደ ግስ እንጠቀምበትም፤ receive "እንደገና መቀበል" የሚለው ቃል የመጣው re (እንደገና) እና capere (መውሰድ) ከሚሉ ሁለት የላቲን ቃላት ነው:: አዳም ባመጸ ጊዜ ተሰጥቶት የነበረውን መንፈስ አጥቶት ነበር:: በመሆኑም ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ፤ በመሠረቱ የተናገራቸው፤ የሰው ዘር ሆይ፣ አዳም እንዳደረገው፣ እናንተም መንፈስን እንደገና ውሰዱ" የሚል ነው:: የሰው ልጆች አጥተውት የነበረውን ነገር እንደገና መልሶ ሰጣቸው::

> የመንፈስ ቅዱስ መመለስ፤ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ለመቤዠት ባለው እቅዱ ውስጥ እጅግ ከፍ ያለው ተግባር ነው::

ኢየሱስ በደቀመዛሙርቱ ላይ እፍ በማለቱ የሰውን ዘር ከሰማያዊው መንግሥት ጋር እንደገና አገናኘ:: ደቀመዛሙርቱን ግልጽ በሆነ መንገድ የሰማያዊው አስተዳደር ዜጎች ወደመሆን ነው ያመጣቸው:: የሰው ልጆች በመንግሥቱ ያላቸውን አቋምና ሥልጣን እንደገና አደሰው:: በምድር ላይ ምክትል ገዢዎች እንዲሆኑ ወደተሰጣቸው ወደ ቀደመው ተግባራዊ ግዳጅ መለሳቸው:: በመሆኑም የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ከእርሱ በኋላ በውስጣቸው የሚኖረውን ገዢ ለመቀበል የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጆች ነበሩ::

የመንፈስ ቅዱስ መመለስ፣ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ለመቤዠት ባለው መርሃ ግብሩ ውስጥ እጅግ ከፍ ያለው ተግባር ነው:: በዚያን ጊዜ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደምድር እንደገና ተመለሰ፤ ምክንያቱም መንፈስ በሰዎች ውስጥ እንደገና መኖር ጀምሮ ነበር!

ከትንሣኤው በኋላ የኢየሱስ መልዕክት የመንግሥቱ መልዕክት ሆኖ መተላለፍ መቀጠሉን ልብ ይበሉ:: ባለመድኃኒቱ ሉቃስ እንዲህ ሲል ዘግቦታል፤

"ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ያደረገውና ያስተምረው ዘንድ ስለጀመረው ሁሉ መጀመሪያውን ነገር ጻፍኩ፤ ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከህማማቱ በኋላ ህያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው::"

አንዳንድ ሰዎች፤ አሁን የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ አለችን? ሲሉ ይጠይቃሉ። መልሱ በእርግጥ አዎን ነው። ይህ ለምን እንደሆነ ለመረዳት፤ የመንግሥታትን ባህርይ ልንገነዘብ ያስፈልገናል። ገዢው ባለበት ሥፍራ ሁሉ መንግሥቱ አለ። የንጉሡ መንፈስ ባለበት በየትም ስፍራ መንግሥቱ ደግሞ አለ። ገዢው፣ የማይታየው ንጉሥ የመገኘቱ መገለጫ ነው። ኢየሱስ ይህንኑ ጥያቄ በተጠየቀ ጊዜ የሰጠውን መልስ ሉቃስ እንዲህ ዘግቦታል፤

"ፈሪሣውያንም የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች? ብለው ቢጠይቁት መለሰ:- የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም ደግሞም:- እነኋት በዚህ ወይም እነኋት በዚያ አይሏትም። እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት አላቸው።"

ገዢው በእናንተ ውስጥ የሚኖር ከሆነ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት በእናንተ ውስጥ ነች። እናም ገዢው በአንተ ወይም በአንቺ ውስጥ መኖር ከጀመረ ጊዜ አንስቶ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ አለች። ኢየሱስ ለተከታዮቹ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፤ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በዚህ ከቆሙት አንዳንዶቹ የእግዚአብሔር መንግሥት በሃይል ስትመጣ ሳያዩ ሞትን የማይቀምሱ አሉ።" ሉቃስ በሁለተኛው መጽሐፍ ውስጥ እንደዘገበው (የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው)፤ ገዢው በወረደ ጊዜና በምድር ላይ ሙሉ በሙሉ በተመሰሰ ጊዜ፤ አንድ መቶ ሃያ የሚያህሉ ደቀመዛሙርት በስፍራው ተገኝተው ነበር።

## እሳቱን መጠበቅ

የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ፤ በሰዎች ዐመጽ ምክንያት ከምድር ላይ ተጠርቶ የሄደውን አስተዳደር እንደገና የማስተዋወቅ ዓላማ ነበር። በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች እንደገና የሚቀደሱበትን መንገድ የመስጠት ተግባራዊ ግዳጁን ካጠናቀቀ በኋላ፤ ወደ ሰማያዊው መንግሥቱ ተመለሰ። የኢየሱስ ዕርገት የተጠናቀቀ ሥራው ማረጋገጫ ነው፤ ይህም ለገዢው ሙሉ ለሙሉ መመለስ ሁሉ ነገር የተዘጋጀ መሆኑን ያመለክታል። በማርቆስ ወንጌል እንዲህ ተዘግቦ ይገኛል፤ "ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር (ከደቀመዛሙርቱ ጋር) ከተነጋገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።" በዚያን ጊዜ በምድር በሚኖሩ ሰዎች ላይ ገዢው ይወርድ ዘንድ ሁሉም ነገር የተመቻቸ መሆኑን ለአባቱ ሪፖርት እንዳደረገ አምናለሁ። ኢየሱስ ይህንን ኃይል ከገዢው ላይ እንዴት እንደሚቀበሉ ለደቀመዛሙርቱ መመሪያን ሰጥቷቸዋል፤ በተለያዩ ሁኔታዎችና ጊዜዎች ውስጥ ለደቀመዛሙርቱ እነዚህን መግለጫዎች ሰጥቷቸዋል፤

"እኔም አብን እለምናለሁ፣ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና



የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው። ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።

"አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።"

"እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሣሌም ከተማ ቆዩ።

በአንድ ወቅት፣ ከእነርሱ ጋር እንጀራ እየቆረሰ ሳለ፣ ይህንን ትእዛዝ ሰጣቸው፤ "ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፤ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ . . . ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም፣ በይሁዳ ሁሉ፣ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ . . .።"

> ደቀመዛሙርቱ ከመንግሥቱ ጋር ግንኙነት ፈጥረዋል፣ ነገር ግን ከመንግሥቱ ኃይል ጋር መገናኘት ያስፈልጋቸዋል።

ቀደም ሲል ኢየሱስ በደቀመዛሙርቱ ላይ መንፈስን እፍ ብሎባቸዋል። ገዢውን በሕይወታቸው ተቀብለውታል፤ ከመንግሥቱም ጋር ተገናኝተዋል። ነገር ግን ገና ከመንግስቱ ኃይል ጋር መገናኘት ያስፈልጋቸው ነበር፤ ይህንንም ንጉሡ ፈጥኖ ይልክላቸዋል። መጥምቁ ዮሐንስ፤ "ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በእሣት ያጠምቃችኋል" ሲል ይህንን ማለቱ ነበር። ኢየሱስ ወደ ሰማያዊው መንግሥቱ ከተመለሰ በኋላ "እሳቱ" መጣ፤ ከመንግሥቱ ጋር እንደገና የማገኛኘትና ኃይልንም እንደገና የመመለስ ሁለቱ ተልዕኮው ሙሉ በሙሉ ይፈጸማሉ።

በሌላ አገላለጽ፤ ኢየሱስ እንዲህ ነው ያላቸው፤ "ላለፉት ሦስት ተኩል ዓመታት የሰማያዊው መንግሥት አገዛዝ ይመጣል ስላችሁ ቆይቻለሁ። ስለዚህ መንግሥት በነገርኳችሁ ጊዜ ሁሉ፤ ገዢው በእናንተ ሕይወትና በዓለም ላይ እንደሚገዛ አስገንዝቤአችኋለሁ። አሁን በኢየሩሳሌም ቆዩ፤ ምክንያቱም አባቴ የገባላችሁ የተስፋ ቃል ሊፈጸምና እናንተም ልትቀበሉት ጊዜው ቅርብ ነው።

ኢየሱስ ኃይልን "ከላይ" እንደሚለብሱ ነግሯቸዋል። ይህ ነጥብ እጅግ ጠቃሚ ነው፣ ኃይላችንን የምንቀበለው ሰማያዊና ከዚህ ዓለም ውጭ

ከሆነው አገር ነው፤ ምክንያቱም ይህ ዓለም በጨለማው መንግሥት ቁጥጥር ሥር የዋለ ነው። እንደገናም ደግሞ ልክ አንድ ልዑላዊ የሆነ ገዢ ሉዓላዊ የሆነውን የመንግሥቱን ተግባር ይፈጽም ዘንድ ከንጉሡ ዙፋን ፊት ወደ ቅኝ ግዛት እንደሚላከው ሁሉ፤ እንዲሁ ንጉሡ ልጅ ገዢውን ወደ ምድር የላከው ከአብ ዙፋን ፊት ነበር።

## መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሣ ቀን ወረደ

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፤ ደቀመዛሙርቱና ሌሎች መቶ የሚሆኑ ተጨማሪ ተከታዮች በአንድነት ሆነው የገዢውን መመለስ ይጠባበቁ ነበር። የእርሱም መምጣት በበዓለ ሃምሣ ቀን ሆነ፤ ይህም በግሪክ ቋንቋ "ሃምሣኛ" ማለት ነው። በዓለ ሃምሣ ከፋሲካ በዓል በኋላ በሃምሣኛው ቀን የሚከበር አዲሱ የእህል ቁርባን ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት በዓል ነው። ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለደቀመዛሙርቱ ከአርባ ቀን በላይ ታያቸው ከዕርገቱም በኋላ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ለዐስር ቀናት ጠብቀዋል። እነኚህ ሃምሣ ቀናት በትክክል ወደ በዓለ ሃምሣ ቀን ያመጡናል። ባለመድኃኒቱ ሉቃስ እንዲህ ዘግቦታል፤

"በዓለ ሃምሳ የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፤ ድንገት እንደሚነጥቅ ዐውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ፤ ተቀምጠው የነበረበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሣትም የተከፋፈሉ ልሣኖች ታዩዋቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች (ቋንቋዎች) ይናገሩ ጀመር።"

የኢየሱስ ተከታዮች በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ጊዜ፤ የበዓለ ሃምሣን ክብረ በዓል ለማክበር ከመላው ዓለም ወደ ኢየሩሳሌም ለተሰበሰቡ አይሁዳዊያን በሚናገሩአቸው ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ይናገሩ ዘንድ ኃይል ተሰጣቸው። የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ወደ ምድር የመመለሱን ታላቅ የምስራች የብዙ አገራት ህዝቦች ይሰሙት ዘንድ እንዲችሉ፤ ሰማያዊ አስተዳደር በመልዕክቶቻቸው ህዝቡን ማግኘት የሚችሉበትን አቅም ሰጣቸው። በእነዚህ ቋንቋዎች መናገራቸው፤ ከንጉሡ ጋር ግንኙነት እንዳላቸውና የእግዚአብሐርን መንግሥት ወደ ምድር የማምጣት ተልዕኮ እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ነበር። በማርቆስ መጽሐፍ ላይ እንደተዘገበው፤ ኢየሱስ ቀደም ሲል ለደቀመዛሙርቱ፤ "እነኚህም ምልክቶች ያመኑትን ይከተሏቸዋል፤ በስሜም . . . ያደርጋሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ" ብሏቸዋል።

ደቀመዛሙርቱ በልዩ ልዩ ቋንቋ ሲናገሩ የሰሙ "ለምንድነው እንዲዚህ የምትናገሩት፤ ምን እየሆናችሁ ነው" ሳይሉ አይቀሩም። ለጠየቁ ሰዎች ደቀመዝሙሩ ጴጥሮስ የሰጠውን ምላሽ ሉቃስ እንዲህ ሲል ይዘግባል፤



"አይሁድ፣ በእየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፤ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፤ ቃሎቼንም አድምጡ። ለእናንተ እንደመሰላችሁ እነኚህ የሰከሩ አይደሉም፤ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና፤ ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዮኤል የተባለው ነው፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሣለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢትን ይናገራሉ፤ ጎበዞቻችሁም ራዕይን ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ህልም ያልማሉ።" ይህንንም ኢየሱስን (ንጉሡን ልጅ) እግዚአብሔር አስነሳው፤ ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን። ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን (ገዢው) የተስፋ ቃል ከአብ (ንጉሥ - አባት) ተቀብሎ፤ ይህንን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው።"

በዚህ ስፍራ እንደገና፤ የአብ ተስፋ ሲነገር እንመለከታለን፤ ነገር ግን አሁን ዜናው የተስፋው ቃል በገዢው መመለስ ተፈጸመ የሚል ነው። ጴጥሮስ እየነገራቸው የነበረው፤ በመንፈስ ቅዱስ መድረስ ለሰማያዊ አስተዳደር አገዛዝ የዓይን ምስክሮች መሆናቸውን ነው።

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉና በበዓለ ሃምሣ ቀን በወረደበት ጊዜ፣ በመንፈስ መሞላታቸው እንቅጥቃጤያዊ ለውጥ በምድር ላይ መከሰቱን ያመለክታል። የገዢውን ህልውናና ኃይል ለመቀበል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን መንጻት ለተቀበሉ ሰዎች ሁሉ፣ አሁን መንገዱ ተከፍቷል። ሰማያዊውን መንግሥት ከሌሎች ፍልስፍናዎች፤ የእምነት ሥርዓቶችና ሃይማኖቶች የሚለየው፤ ዜጎቹ በውስጣቸው መንፈስ ቅዱስ መኖሩ ነው። ሃይማኖቶች የእምነት መግለጫዎች መርሆዎችና "የአድርግ"ና "የአታድርግ" ዝርዝሮች አሏቸው፤ ነገር ግን በውስጣቸው የሚኖር መንፈስ ቅዱስ የላቸውም።

## በሁሉም ሥፍራ የመገኘት ኃይል

ባለፉት ምዕራፎች እንደተመለከትነው፤ መንፈስ ቅዱስ ይኖር የነበረው በኢየሱስ ውስጥ ብቻ ቢሆንም፤ አሁን ግን በምድር ላይ በሚኖሩ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ውስጥ ይኖራል። መላዋ ግዛት በንጉሡ ክብር ትሞላ ዘንድ ተመልሶ ወደቅኝ ግዛቱ መጥቷል። ወደ ምድር ከመፍሰሱ የተነሣ አሁን በአንድ ጊዜ በመላው ዓለም ላይ ሊሆን ችሏል። በተለያዩ ዘሮችና ልዩ ልዩ የቆዳ ቀለም ባላቸው ሰዎች ውስጥ ይኖራል። በወንዶችና በሴቶች በህፃናቱም ውስጥ ይኖራል። በፍጥረታዊ አካል የነበረው ኢየሱስ፤ ህፃናትን ሊባርክ፣ ለተራቡት እንጀራን ሊቆርስና የታመሙትን ሊፈወስ የነበሩት ሁለት እጆች ብቻ ነበሩ። አሁን በተከታዮቹ ሕይወት ውስጥ በሚኖረው መንፈስ በኩል፤ የመንግሥቱን ሥራ የሚሠሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ እጆች አሉ። ኢየሱስ በምድር ላይ

አገልግሎቱ በፍልስጤም አካባቢ ብቻ የተወሰነ የነበረ ሲሆን፤ አሁን ግን በአንድ ጊዜ በአውስትራሊያ፣ በቻይና፣ በአሜሪካ፣ በባሃማስና በመላው ዓለም ሊከናወን ይችላል:: የእርሱ ዓላማ የእግዚአብሔርን መንግሥት በእልፍ አእላፋት ሰዎችና ቁጥር ስፍር በሌላቸው መንገዶች በምድር ላይ ማስፋፋት ነው::

ለምሳሌም ያህል፤ መንፈሱ በአንተ ውስጥ የሚኖር ከሆነ፤ በሥራ ላይ ባለህበት ጊዜ፣ ሰማያዊው አስተዳደር በዚያው ስፍራ ይገኛል:: አንተ ስመንግሥቱ በምትገልጠውና በምትሰጠው ዋጋ፣ በዝንባሌህ፣ በይቅርባይነትህ፣ በፍቅርህና በትእግስትህ፤ በምትሠራበት ሥፍራ የእርሱን አገዛዝ ተፅዕኖ እንድታመጣ ይፈልጋል:: ማንኛውም ሰው፤ "ለምንድን ነው እንዲህ ልዩ የሆንከው?" ብሎ ቢጠይቅህ፤ መልስህ ልክ ኢየሱስ እንደተናገረው፤ "መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም" የሚል ይሆናል:: ንጉሡ፤ አንተ በዚህ በጨለማው መንግሥት መካከል የእርሱ መንግሥት ወኪል እንድትሆን ይፈልጋል፤ እንዲህ ሲሆን ደግሞ ሌሎች ከሰማያዊው አገዛዝ ጋር ስመታረቅ ይችላሉ::

## በምድር ላይ ታላላቅ ሥራዎች

ኢየሱስ ከመሞቱና ከትንሳኤው ጥቂት ቀደም ብሎ የሰጠውን መግለጫ፣ ዮሐንስ እንዲህ ሲል ዘግቦታል፤ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፤ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና::" እንዴት አድርገን ነው ኢየሱስ ከሠራቸው ሥራዎች ይልቅ የበለጠ ማድረግ የምንችለው?

> መንፈሱ በአንተ ውስጥ የሚኖር ከሆነ፤ በየትም ሥፍራ ብትሆን ሰማያዊው አስተዳደር አለ::

በዚህ ሥፍራ "የሚበልጥ" የሚለው ቃል በመጠን የሰፋንና የበዛን ነገር እንጂ ጥራትን የሚገልጽ አይደለም:: በኢየሱስ የተሰሩትን ሥራዎች ጥራት ልናሻሽላቸው አንችልም:: ነገር ግን አካሄዳችንን ከእግዚአብሔር አባት ሃሳብና ፈቃድ ጋር ስናደርግና ዓላማውም በሕይወታችን ቀዳሚ ሥፍራ ከያዘ ኢየሱስ "አብ ስለወልድ ይከብር ዘንድ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርጋለሁ" ሲል ቃል ገብቶልናል:: የሰማያዊው አስተዳደር ባህርይ፤ በቅኝ ግዛቱ ሁሉ ውስጥ ይስፋፋል፤ እናም ይሄ በሰማይና በምድር ንጉሥ ለሆነው ክብር ያመጣል:: መንፈሱን የተቀበሉት ሁሉ በአንድነት ሆነው በምድር ላይ የእርሱን ሥራ ያበዙታል::

የገገርው ኃይል የመንግስተ ሰማይን እውነታ በምድር ላይ የሚቻል ማድረግ ነው:: ስዚህ ነው እያንዳንዱ ሰው መንፈስ ቅዱስ



የሚያስፈልገው:: እኛን ከንጉሡ ጋር የሚያገናኘን ብቸኛ እርሱ ነው፣ በእኛም አማካይነት የጨለማውን መንግሥት አስወግዶ በብርሃን መንግሥት የሚተካ እርሱ ብቻ ነው:: በምድር እጅግ ከፍተኛ ገገር እርሱ ነው::

# ምዕራፍ ስምንት

## ገዢውን ወደ ስፍራው መመለስ

*እንቆቅልሽ እስኪፈታ ድረስ እንቆቅልሽ ሆኖ ይቆያል::*

ወደ መንግሥተ ሰማይ የመግባታችን እውነታ "አዲስ ልደት" እየተባለም ይጠራል፤ ይህም በምድር ላይ እንደ ገዢዎች ያለንን ሕጋዊ ሥልጣን መልሶ የሚያስጨብጠን ነው:: ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃችን ደግሞ ይህን ሥልጣናችንን ለመለማመድ የሚያስፈልገን ኃይል ወይም ችሎታችን ወደ እኛ መመለሱን የሚያሣይ ነው:: እነኚህን ሁለት ጽንሰ ሀሣቦች በአግባቡ መረዳታችን በምድር ላይ በመንግሥቱ ባህል ውስጥ ሆነን ስንኖር ውጤታሞች እንድንሆን ያደርጉናል፤ ሁለቱም ገዢው ወደ ስፍራው እንዲመቀስና በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ስለ ሚጫወተው ሚና አስፈላጊ ነገሮች ናቸው::

እስኪ አሁን ደግሞ እነኚህን ሁለት ጽንሰ ሀሳቦች ጠለቅ አድርገን በመመልከት፤ አዲስ ልደትን ከውሃ ምንጭ ጉድጓድ፤ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ደግሞ ከሚፈስ ወንዝ ኃይል ጋር እያወዳደርን እንቃኝ::

### አዲስ ልደት:- የመንግስቱን ሥልጣን ወደ ስፍራው መመለስ

ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ የገዢውን ወደ ሰው ዘር መመለስ አስመልክቶ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል እንዲህ ሲል ዘግቦታል፤ "እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት *የሚፈልቅ የውሃ ምንጭ* ይሆናል እንጂ::" ውሃ በዚህ አውድ የመንፈስ ቅዱስ ምሣሌ ነው:: የአዲስ ልደት እውነታ፤ አሁን በእኛ ውስጥ የማያቋርጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ሙላት መኖሩን የሚያሳይ ነው:: ለዘላለም የሚፈልቅና እንደ አዲስ የሚፈሰቀስቅ፣ ንጹህና ሕይወትን የሚሰጥ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነው:: ከዚህ በውስጣችን ካለ የመንፈስ ውሃ ደህና አድርገን ያለማቋረጥ ስንጠጣ፤ ከመንግሥቱ ሕይወት ጋር ያለማቋረጥ ግንኙነትን እናደርጋለን::

እስቲ ገዢው፤ በአዲስ ልደት በኩል የመንግሥቱን ሕይወት ወደ እኛ እንዴት እንደሚመልሰው በጣም በጥልቀት እንመልከት::



### የሰውን ልጆች ከአስተዳደሩ ጋር እንደገና ያገናኛል

የመንፈስ ቅዱስን እስትንፋስ በመጀመሪያ በተቀበልን ጊዜ - የገዢውን ወደ እኛ መመለስ ያመለክታል - የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂ የሆነው የተርሴሱ ጳውሎስ በጽሁፎቹ ሁሉ ውስጥ በተደጋጋሚ የመንፈሱ "መያዣ" ሲል እንደገለጸው፤ እኛ አሁን የንጉሡ መሆናችንንና በሰማያዊው መንግሥቱም ወራሾች እንሆን ዘንድ እርስት እንደተሰጠን የሚያሣይ ነው::

"በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፤ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው::"

"አሁን፤ ለዚሁ የሠራን እግዚአብሔር ነው እርሱም ሊመጣ ያለውን ነገር ያረጋግጥልን ዘንድ የመንፈሱን መያዣ ሰጠን::"

"እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ፤ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፤ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል::"

### የሰው ልጆችን ዜግነት በሰማይ እንደገና ያፀናል

ይሁን እንጂ፤ አስቀድመን እንደማንም በምድር ላይ ነዋሪዎች ነበርን፤ የንጉሡ ልጆችና የመንግሥቱም ሙሉ ዜጎች ለመሆን በቃን:: ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም":: ሰማያዊው ዜግነታችን የተሰጠን በራሱ በንጉሡ ነው፤ ይህም ዜግነት የሚያስገኘው ሙሉ መብትና ጥቅም ሁሉ አብሮ ተሰጠን::

### በሰው ልጆች በኩል መንግሥቱን ወደ ምድር እንደገና ይመልሳል

ገዢው በምድር በሚኖሩ የመንግሥቱ ዜጎች ውስጥ የሚኖር በመሆኑ ምክንያት፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ራሱ በምድር ላይ ነው:: ይህ እንደገና ወደ ስፍራ የመመለስ ሂደት በመጀመሪያ የተከሰተው ንጉሡ - ልጁ በምድር ላይ እንደ ሰው ለመኖር በመጣበት ጊዜና ኢየሱስ በመጀመሪያ በደቀመዛሙርቱ ላይ መንፈስ ቅዱስን እፍ በማለት ለወደቀው የሰው ዘር በመለሰበት ጊዜ ነው:: ሰማያዊው አስተዳደር በአዲስ ልደት በኩል በምድር ላይ ወኪሎች አሉት:: ወደ ሰማያዊው መንግሥት የሚገቡ የምድር ነዋሪዎች ቁጥር እየጨመረ በሄደ መጠን፤ በዓለም ላይ የመንግሥቱ አገዛዝ መስፈን ይበልጥ እየታወቀ ሊሄድ ግድ ነው::

## ከሁለቱ ዓለማት ጋር ግንኙነትን የመፍጠርና ወደማይታየው ዓለም መግባትን እንደገና ያድሳል

አዲስ ልደት፤ ከሰማይ ወደ ምድር እንዲሁም ከምድር ወደ ሰማይ የሚደረገውን የሁለትዮሽ ግንኙነትን እንደገና የሚያድስ ነው:: ቀደም ሲል ከሁለቱ ዓለማት ጋር ግንኙነት መፍጠር ያልኩት ይህንን ነው:: በመጀመሪያ የሰው ልጆች ከንጉሥ - አባት ጋር ፍፁም የሆነ ግንኙነት ነበራቸው፤ ይሁን እንጂ ለግንኙነቱ መንገድ የነበረውን ገዢውን ባጣን ጊዜ ይህን ግንኙነት አጥተናል:: ከንጉሥ ጋር ያለንን ግንኙነት እንደገና በመሠረትን ጊዜ፤ ያኔ እርሱ ወደ እኛ በቀጥታ ሊመጣና ሊገናኝ፤ እኛም ወደ እርሱ በቀጥታ ልንገባና ልንገናኝ እንችላለን:: አዲስ ልደት ማለት፤ ንጉሡ በሚኖርበት በማይታየው ዓለም ውስጥ ተቀባይነትን ማግኘት ብቻ ሳይሆን፤ የመንግሥቱን ዓላማ በምናገለግልበት በዚያ ገዢነትን መለማመድ ጭምር ማለት ነው:: ቀደም ሲል በጠቀስነው፣ በሚከተለው ዘገባ ውስጥ ኢየሱስ ይህንኑ ማለቱ ነበር፤

> "እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሠረ ይሆናል:: በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል:: ደግሞ እላችኋለሁ፤ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ፤ ከሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል:: ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና"

## በሰው ዘር ውስጥ የንጉሡን ባህርይ እንደገና ይመልሳል

ይህ ጽንስ ሀሳብ ኢየሱስ፤ ለፈሪሳዊው ኒቆዲሞስ ያስተማረው ነው፣ ኒቆዲሞስ የአዲስ ልደትን ትርጉም ለመረዳት ሞክሮ የነበረ ነበር:: "እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም:: ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው:: ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልኩ አታድንቅ::"

ይህ መግለጫ "አዲስ ልደት" ለሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቸኛው ዋቤ ቢሆንም፤ ዛሬ ዛሬ በግርድፉ ብቻ እዘውትረን የምንጠቀምበት፤ ነገር ግን ትክክለኛ ትርጉሙን የሳትንበት ክፍል ነው:: ዳግም ልደት ማለት ገዢውን መቀበላችንንና በዚህም ሳቢያ፤ በመንግሥቱ ግዛት ውስጥ ዜጎች እንሆን ዘንድ ብቁ የሚያደርገን አዲስ ባህርይ እንደተሰጠን የሚያሣይ ነው:: እንደገና እግዚአብሔርን የምንመስል ሆነናል:: ጳውሎስ እንዳለው፤ "እንግዲህ እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፤ ክርስቶስም ደግሞ እንደወደዳችሁ ለእግዚአብሔር የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባና መስዋዕትን አድርጎ ስለ



እናንተ ራሱን አሣልፎ እንደሰጠ በፍቅር ተመላለሱ::" የንጉሡ ልጆች ነንና በመንፈሳዊ ስሪታችን "DNA" ውስጥ ይህ ባህርይ በመኖሩ አሁን በዓለም ውስጥ ሊንጸባረቅ ይችላል::

## በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፡ የመንግሥቱ ኃይል እንደገና መመለስ ነው

አዲስ ልደት ወይም መለወጥ ለመንግሥተ ሰማይ ያዘጋጀናል፤ ይህም ማለት ከሰማያዊው መንግሥት ጋር እንደገና መገናኘትና ከንጉሡ ጋር ያለን ህብረት እንደገና መታደስ ማለት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ለምድርም ያዘጋጀናል፤ ይህም ምድር ሰማይን እንድትመስል የማድረግ ተግባራዊ ግዳጃችንን ለመወጣት የአገዛዝ ሥልጣናችን እንደገና መመለስ ማለት ነው:: የተለያዩ ልምምዶች በመሆናቸው ምክንያት እነዚህን እርስ በእርስ የሚቃረኑ ሀሳቦች ከመንፈስ ጋር ማነጻጸር እፈልጋለሁ::

ንጉሡ ልጅ በሰማያዊው አስተዳደር ወዳለው ወደ አባቱ ከመመለሱ ከጥቂት ጊዜ በፊት፤ ለደቀመዛሙርቱ ይህንን ነገራቸው፤ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ":: በዚህ ስፍራ ለተጠቀሰው "ኃይል" ለሚለው ቃል የግሪክ አቻ ትርጉም "ዱናሚስ" የሚል ሲሆን ይህም "ተአምራዊ ኃይል" ማለት ነው:: "ተአምራት" ብለን ስለምንጠራቸው ነገሮች ቀደም ሲል ያደረግነውን ውይይት አስታውሱ:: ተአምራት የሰማያዊው መንግሥት አገዛዝ በምድር ላይ የመኖሩ መግለጫ ናቸው:: በመሆኑም ይህ ኃይል የሚመጣው በቀጥታ ከሌላ ዓለም፣ ከሰማያዊ አስተዳደር ነው፤ ይህም ንጉሡን በመወከል በዓለም ላይ ሥልጣናችንን ለመለማመድ እንዲያስችለን ነው::

> **አዲስ ልደት ለመንግሥተ ሰማይ ያዘጋጀናል::**
>
> **በመንፈስ መጠመቅ ለምድር ያዘጋጀናል::**

የዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ ይህንን የኢየሱስን ቃል ይዘግባል፤ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል" ብሎ ጮኸ:: "ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለመንፈስ ቅዱስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበርና::"

በተለወጥን ጊዜ መንፈስ በእኛ ውስጥ ያድራል:: በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ለንጉሡ መታዘዛችንና በእኛ ውስጥ አስቀድሞ የተቀመጠው በኃይል እንዲለቀቅ መፍቀዳችን ነው:: አዲስ ልደት ሳያቋርጥ እንደሚፈስ ምንጭ ሲሆን፤ ጥምቀት ደግሞ ኃይል እንዳለው ወንዝ ነው፤ ይህም ልክ

ለሰው ልጆች መሸሸልና ለዕለታዊ ኑሯቸው የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ለማንቀሳቀስ፣ ለምሳሌ እንደወፍጮ ለመሳሰሉ፣ ኃይልን ከሚመግብ የውሃ ኃይል ጋር የሚመሳሰል ነው።

እስኪ አሁን ደግሞ በሰው ዘር ዐመጽ ያጣነውን ኃይል በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እንዴት እንደሚመልሰው እንመልከት።

## የመግዛትን ኃይል እንደገና ይመልሳል

አዲስ ልደት ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር የነበረንን ግንኙነት እንደገና የሚያድስ ሲሆን፤ ጥምቀት ደግሞ በአስተዳደሩ የተሰጠንን ሥልጣን መጠቀም የምንችልበትን ብቃት ያቀዳጀናል። ኃይል ሁኔታዎችን የመግዛትና የመቆጣጠር ብቃታችንን የሚያመለክት መሆኑን ልብ ይሏል። በፍጥረታዊው ምድርና በዓለም ላይ በሚያጋጥሙን የተለያዩ ሁኔታዎች ላይ የበላይነትን ለማስፈን የግድ ሊኖረን የሚያስፈልግ ኃይል ይህ ነው።

## አስተዳደሩን ለመወከል የሚያስችለውን ብቃት ለሰው ዘር እንደገና ይመልሳል

የሰማያዊው አስተዳደር ወኪል ሆኖ እንደገና መሾም አንድ ነገር ሲሆን፤ በአስተዳደሩ መላክህን ለማረጋገጥ ማስረጃ ማሳየትህ ግን ሌላ ነገር ነው። ጥምቀት ንጉሥህ ከአንተ የሚፈልገውን ማሟላትህን በተጨባጭ የምታረጋግጥበትን ኃይል ይሰጥሃል። የመንፈስ ስጦታዎች ጠቃሚ የሚሆኑት እዚህ ጋ ነው። በምዕራፍ ዐስራ ሶስት ላይ እንደምንመለከተው፤ የስጦታዎቹ አውድ በምድር ላይ መንግሥታዊ የሆነ አስተዳደር ነው። ገዢው በሰማያዊው አስተዳደር የተሰጠንን ተግባራዊ ግዳጅ መወጣት እንችል ዘንድ ኃይልን ይሰጠናል። በመሆኑም ስጦታዎቹ እንግዳ የሆኑ ልዕለተፈጥሯዊ ክስተቶች ሣይሆኑ፤ ተግባራዊ የሆኑ አስፈላጊነት ያላቸው ስጦታዎች ናቸው።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "እኔስ በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንኩኝ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ እንደቀረበች እወቁ።" እየተናገረ የነበረው፤ አጋንንትን ማውጣት፣ ሰማያዊው መንግሥት ወደ ምድር መመለሱን የሚያሳይ የተጨበጠ ማስረጃ መሆኑን ነበር። ይህ ስለ እምነት ብንል፣ ስለ ፈውስ ወይም ስለ ተአምራት ብንል ለሁሉም የመንፈስ ስጦታዎች በተመሳሳይ የሚሠራ እውነት ነው። ስጦታዎቹ የእግዚአብሔር አስተዳደር ህልውና፣ ሥልጣንና ኃይል በምድር ላይ ለመስፈኑ ማረጋገጫዎች ናቸው።

> **የመጠመቅ ኃይል የመንግሥቱን እውነታ ያረጋግጣል**

መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎቹን ወደ ኢየሱስ ልኮ፤ ገዢውን ለመመለስ ወደ ምድር የሚመጣው ንጉሠ - ልጅ እርሱ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ



እንዲነግረው ለጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው መልስ ይህንን የሚመለከት ነበር። የማቴዎስ መጽሐፍ እንዲህ ይዘግበዋል።

> "ዮሐንስም በወህኒ ሣለ የክርስቶስን ሥራ ሰምቶ ከደቀመዛሙርቱ ሁለት ላከና የሚመጣው አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ አለው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤ እውሮች ያያሉ፤ አንካሶችም ይሄዳሉ፤ ለምፃሞችም ይነፃሉ፣ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፣ ሙታንም ይነሳሉ፣ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል።"

ኢየሱስ ከሰማያዊው አስተዳደር እንደመጣና በምድርም ላይ የመንግሥቱን የበላይት እያሰፈነ መሆኑን ለዮሐንስ ማረጋገጫ እየሰጠው ነበር። ሁሉን ነገር ያብራራ የነበረው ከመንግሥቱ አንጻር ሲሆን፤ የዮሐንስም መልዕክት ይሄው በመሆኑ ኢየሱስ የሰጠውን መግለጫ እንደሚረዳው ያውቅ ነበር።

## የሰው ልጆች የንጉሡን ጥያቄዎች እንዲያረጋግጡና የመንግሥቱን መስፈን በተጨባጭ እንዲያሳዩ ያስችሳቸዋል።

የማቴዎስ መጽሐፍ የኢየሱስን መግለጫ እንዲህ ሲል ይዘግባል፤ "ለአህዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል።" "ምስክር" የሚለው ቃል በጥቅሉ የሚያመለክተው ስለ አንድ ሁኔታ እውነት የሆነውን ነገር በመመስከር መናገርን ነው። ከላይ በተገለጸው ማብራሪያ ውስጥ የተጠቀሰው ይህ ቃል በጥንታዊው የግሪክ ቋንቋ "የተረጋገጠ ነገር" ማለት ነው። ለምሳሌም "የተሰጠ ማስረጃ" ሊሆን ይችላል። በጥምቀት አማካይነት ኃይልን ማስፈን፤ ስለ መንግሥቱ እውነታዊነትና የዓላማውን ሐቅነት ለዓለም የማሣያ አንድ መንገድ ነው።

## የሰው ልጆች የንጉሡንና የመንግሥቱንም ክብር ይገልጡ ዘንድ ብቃት ይሰጣቸዋል።

የጥምቀቱ ኃይል ሁሉን ቻይ የሆነውን የሰማይና የምድር ሁሉ ፈጣሪ ባህርይ ሥራዎች በሕይወታችን እንገልጥ ዘንድ ያስችለናል። መዝሙረኛው ንጉሥ ዳዊት እንዲህ ጽፏል፤

"ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣
የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል፣
ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፣
ሌሊትም የሌሊት እውቀትን ትናገራለች፣

ነገር የለም፤ መናገርም የለም
ድምፃቸውም አይሰማም::
ድምጻቸው ወደ ምድር ሁሉ፣
ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ::

ከላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር ክብር በባህርይ ቋንቋ ሊገልጸው ከሚችለው በላይ ነው:: የሁሉም ዓይነት ዘሮች፣ ህዝቦችና ከየትኛውም ወገን የሆናችሁ ሰዎች ተመልከቱት፤ ይህ በማያቋርጥ ሁኔታ ለዓለም ሁሉ ፈጣሪ ጮኾ ምስክርነትን የሚሰጥ ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታም በገዢው በኩል የመንግሥቱ ዜጎች የሚያከናውኑት ተግባር ከሰው ልጆች ቋንቋና ባህል አልፎ የሚሄድ ነው:: ቋንቋውን መናገር ወደማትችለው ወደ አንድ አገር ብትሄድና፤ ገዢውም ለዓመታት ያህል ሽባ ሆኖ ለኖረ ሰው አንተን ተጠቅሞ ፈውስን ሊያመጣ ቢፈልግ፤ እርሱ የአንተን ቃላት ከመረዳት ጋር ጉዳይ የለውም፤ ምክንያቱም ድርጊትህን ሊረዳው ይችላልና ነው:: ክብር የሚለው ቃል የሚገልጸው የአንድን ነገር መሠረታዊ ባህርይ ነው:: አንድ ሰው በግል የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማሟላት የንጉሡ ባህርይ መሆኑንና፤ እነዚህን ነገሮች ስማግኘት ኃይል እንዳለው ወደ መረዳት ሊመጣ ይችላል:: ስለዚህ ንጉሥና ስለመንግሥቱም ለመስማት ጆሮዎቹን ይከፍታል:: ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን ያከብሩ ዘንድ፤ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ" እንዳላቸው ማለት ነው::

## የሰው ልጆች የሰማይ ዜጎች መሆናቸውን ማሳየት የሚችሉበትን ብቃት ይሰጣቸዋል::

ይህንን አስመልክቶ፤ በጥምቀት በኩል የተገለጸው ኃይል የሰማያዊው መንግሥት ዜጎች መሆናችንን የሚያረጋግጥ ነው:: ልክ እንደ ፓስፖርት ነው፤ እኛ የንጉሡ መሆናችንንና የመንግሥቱንም ሥራ ልንሠራ እውቅና የተሰጠን መሆኑን ያረጋግጥልናል:: የመንግሥቱን ሥራ ለመሥራት "መሞከር" ብቻውን በቂ አይደለም፤ ሥራህን ለመስራት የሚያስችልህ የሥልጣን ድጋፍ የግድ ያስፈልግሃል:: በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንደተገለጸው የአስቄዋ ሰባት ልጆች የገጠማቸው አስቸጋሪ ሁኔታ ይኼው ነበር:: ጳውሎስ በኢየሱስ ስም አጋንንትን ማስወጣቱን ያውቁ ስለነበር፤ እነርሱም ደግሞ እንደዚያው ለማድረግ ሞከሩ:: ነገር ግን በሰማያዊው መንግሥት እውቅና ያለው ሥልጣን ያላቸው አልነበሩም፤

"የካህናትም አለቃ ለሆነ አስቄዋ ለሚሉት አንድ አይሁዳዊ ይህን ያደረጉ ሰባት ልጆች ነበሩት:: ክፉውም መንፈስ ግን መልሶ፤ ኢየሱስን አውቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፤



እናንተስ እነማን ናችሁ? አላቸው:: ክፉውም መንፈስ ያለበት ሰው ዘለለባቸው፤ ቆስለውም ከዚያ ቤት ራቁታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው፣ አሸነፋቸውም:: ይህም በኤፌሶን በሚኖሩት ሁሉ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች ዘንድ የታወቀ ሆነ፣ በሁላቸውም ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው፤ የጌታም ኢየሱስ ስም ተከበረ::"

ጳውሎስ የሰማያዊው መንግሥት ሥልጣን ያለው ዜጋ ነበር፤ በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ ያለውን ሥልጣን የጨለማው መንግሥት ወኪሎች ያከብሩትና ይታዘዙትም ነበር:: የሰማያዊውን መንግሥት ኃይል በቀላሉ ከቶ ልንጠቀምበት አንችልም፤ ነገር ግን በውስጣቸው በሚኖረው መንፈሱ በኩል በንጉሡ ሥልጣን የተሰጣቸው ብቻ ኃይሉን ይጠቀማሉ::

## ገዢውን በሕይወትህ መቀበል

በሚቀጥሉት ምዕራፎች፤ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኩል ስለሚመጣው ኃይል ሰፋ አድርጌ አብራራለሁ:: አሁን ግን፤ በግል ሕይወትህ ገዢውን እንዴት መቀበል እንደምትችል እንድታተኩር እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም ይህ በመጀመሪያ ደረጃ ከንጉሡ - አባት ጋር ያስታርቅሃል፤ እንዲሁም የመንግሥቱን ሥልጣን መቀበል እንድትችል ብቁ ያደርግሃል::

በአዲስ ልደት በኩል እርቅን ስለማድረግ ልትሰማ ከምትችላቸው መልካም የምስራቾች ሁሉ የላቀው ነው! ይህም ማለት ንጉሡን ያለ ፍርሃት ልትቀርበው ትችላለህ ማለት ነው:: ኢየሱስ ስለ ዐመጽህና ከመንግሥቱ ነፃ ስለመውጣት መንፈስህ ይገባህ ስለነበረው ቅጣትህ ዋጋ ከፍሏል:: በበዓለ ሃምሣ ቀን ተሰብስበው ለነበሩ ህዝብ የኢየሱስ ደቀመዝሙር የነበረው ጴጥሮስ በተናገራቸውና እየሆነ ስለነበረው ነገር በገለጸላቸው ጊዜ፤ ህዝቡ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ጠየቁ:: እንዲህም ሲል ገለጸላቸው፤ "ንስሃ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ::" በመሆኑም አዲስ ልደትን ታገኙ ዘንድ እናንተ . . .

በመጀመሪያ፤ *ንስሃ ግቡ::* በሰማያዊው መንግሥት መስኪያና መስፈርት አኳያ እንዴት መኖር እንደሚገባችሁና እንዴትስ ልትኖሩ እንደምታቅዱ አመለካከታችሁን ለውጡ::

ሁለተኛ፣ *በኢየሱስ መስዋዕትነት የተገኘውን ምህረት ተቀበሉ::* ዛሬ ዛሬ በሰው ልጆች ዘንድ ካሉት ዋንኛ ችግሮች አንዱ፤ ከንጉሡና ከመንግሥቱም ባህርይ ተፃራሪ በሆነ መንገድ ስለሠራናቸው ስህተቶች የሚሰማን ከባድ በደለኝነት ነው:: ይቅርታ ማድረግ ማለት ከተጠያቂነትና ከወንጀለኝነት ነፃ ማድረግ ማለት ነው:: በመሆኑም በመንግሥቱ ነፃነት ውስጥ ለመኖር በኢየሱስ በኩል የተሰጠህን ይቅርታ የግድ መቀበል

ይኖርብሃል፤ ከዚያም በኋላ ጳውሎስ እንደጻፈው፤ "በአዲስ ሕይወት" ተመላለስ::

አንድ ጊዜ ከላይ በጠቀስኳቸው ደረጃዎች ካለፋችሁ፤ በውስጣችሁ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡ ይህ የርስት መያዣና ወደ መንግሥቱ ለመግባት ማረጋገጫው ነው:: ይህንን በዋጋ የማይተመን ስጦታ ስለሰጠችሁ ለንጉሥ - አባት ምስጋና አቅርቡ::

ይህን ልብ እንበል፤ በተጨማሪም በውሃ እንድንጠመቅ ትእዛዝ ተሰጥቶናል:: በኢየሱስ ስም በውሃ መጠመቅህ፤ ለኢየሱስ መንግሥት ትምህርት ቤት ራስህን አሳልፈህ መስጠትህን፣ ከዚህ በኋላ እርሱ ጌታ መምህርህ ለመሆኑና ለእርሱም ታማኝ መሆንህን እንዲሁም ስለ ዐመጽህ ሁሉ ሙሉ ምህረትን መቀበልህን የሚያሳይ ነው::

አዲስ ልደት ማለት ሕይወትን ከዚህ በኋላ በራስህ መንገድ ልትመለከት አለመሞከር ማለት ነው:: ንጉሡ ያንን ሸክምና ጭንቀትህንም አስወግዶታል:: ልክ አንድ በቅኝ አገዛዝ ሥር ያለ አገር መንገዶችን ለመሥራት፣ የውሃ አቅርቦትንና የመሣሰሉትን ለማግኘት በገዢው መንግሥት ላይ እንደሚደገፍ ሁሉ እንዲሁ ደግሞ የመንግሥቱ ዜጋ በሕይወቱ ለንጉሡ ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጥ ከሆነ የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ ይቀርቡለታል:: ለዚህም ነው ኢየሱስ እንዲህ ያለው፤

> "እንግዲህ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንን ሁሉ አህዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና:: ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፤ ስለዚህም ስለ ነገ አትጨነቁ፤ ነገ ስለራሱ ያስባልና::"

የመንግሥቱ ሕይወት ይህ ነው፤ በቅድሚያ የመንግሥቱን መልካምነት መፈለግ፤ ቀጥሎም በሰማያዊው ገዢ በኩል በሰጠህ ሥልጣንና ኃይል እርሱን እያገለገልክ ሁሉንም ፍላጎቶችህን ያሟላልህ ዘንድ መፍቀድ::



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ግንኙነትን እንደገና የመመሥረት ውጤቶች

*የዓሣ ስኬታማነት በውሃ ውስጥ መቆየቱ ነው::*

ማንም ሰው ያለገዢው፤ የሰማያዊው መንግሥት ዜጋ ሊሆን አይችልም:: ዮሐንስ በወንጌሉ የኢየሱስን ቃል እንዲህ ሲል ይዘግበዋል፤ "እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም:: ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው::"

አንድ ሰው ብዙ ጥቅም ያላቸውን ነገሮች ሊያከናውን፣ መልካም በሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ሊሣተፍ እንዲሁም ሃይማኖታዊ የሆነ መነሻም ሊኖረው ይችላል፤ ይሁን እንጂ የመንግሥቱ መንፈስ የሌለው ከሆነ በመንግስቱ ውስጥ ያለ ሰው አይደለም:: የሰማዩ ንጉሥ ሃይማኖታዊ በሆኑ ልምምዶችና የመስዋእት ሥርዓቶች የሚደሰት አይደለም:: ልክ ዲራይቦ ኒኩሊክ አሲድ (DNA) የተባለው ንጥረ ህዋስ የአንድን ሰው ማንነት እንደሚወስን ሁሉ፤ በሰው ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ የመንግሥቱ ዜጋ አድርጎ ይፈርጀዋል:: እዚህ ጋ ለስህተት ዳርቻ የለም::

በገዢው በኩል ከንጉሡ ጋር ግንኙነትን በጀመርክበት ጊዜ ሙሉ ለሙሉ አዲስና አስደናቂ ሕይወት ይከፈትልሃል:: በመንግሥቱ የሕይወት ሥርዓት ውስጥ እንዴት እንደምንኖር፤ በገዢው የምንሰለጥንባቸውንና በምድር ላይ ከእርሱ ጋር የአገዛዝ አጋሮቹ የምንሆንባቸውን የተወሰኑ መንገዶች ከመመልከታችን በፊት፤ ገዢውን ወደ ሕይወታችን በምንቀበልበት ጊዜ የሚከሰቱትን የመነሻ ሽግግሮችና ጥቅሞች በክለሣ መልክ እንመልከት::

### ከንጉሥ - አባት ጋር እንደገና የታደሰ ዝምድና

ግንኙነትን እንደገና የመፍጠር የመጀመሪያው ውጤት ከንጉሥ - አባት ጋር ዝምድናን ነው:: የሰው ልጆች ከሰማያዊው አስተዳደር የመለየት ነጻነት ባወጁ ጊዜ፤ ከሕይወት ምንጭ ራሳችንን አገለልን፤ ጎስቋሎችና ግራ የተጋባን ሆንን፤ እናም ሕይወት ዛሬ በምድር ላይ እንዲህ ባለ ጥፋት፣ አመጽ፣ ስቆቃና አቅም አልባነት ውስጥ የተዘፈቀችው ለዚህ ነው:: ምድር አንድ ትልቅ እቅድ እንዳለው ነገር ግን ይህን እቅድ ለመተግበር ግን የገንዘብ አቅም የሌለውን ሰው ትመስላለች::

ገዢው ወደ አንድ ሰው ሕይወት በገባ ጊዜ፤ ያንን ሰው ከራሱ የሕይወት ምንጭ ጋር ያገናኘዋል፤ ከፈጣሪው ጋር ዝምድና ይሰጠዋል - ዝምድናው ፈጣሪውን እንደ ንጉሥ ብቻ ሳይሆን እንደ ሰማያዊ አባቱ ጭምር ያደርግለታል። አሁን የንጉሡ የቅርብ ቤተሰብ ሆኗል፤ ማንኛ ውም የሰማያዊው ንጉሣዊ ቤተሰብ አባል ያለው መብትና ጥቅም ተካፋይም ነው።

ከንጉሥ አባታችን ጋር በተስማማን ጊዜ፤ "የመጣሁት ከአንተ ዘንድ ነው፤ እናም በአንተ ልደገፍ የግድ ነው፤ በአንተ ላይ እታመናለሁ" ብለን ማረጋገጫ እየሰጠን ነው። በእግዚአብሔር የመደገፍ ግዴታ ውስጥ እንኖራለን። ነቢዩ ኢሣያስ እንደተናገረው፤ አለቅነት በንጉሡ ጫንቃ ላይ ነው። እርሱ ህዝቡን ሊመራ ሃላፊነት አለበት። እርሱ የተጠራባቸው ስሞች የሚያመለክቱት ሃላፊነቱን ብቻ ሳይሆን ችሎታውን ጭምር ነው፤ ለምሣሌም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ የሚሉት ስሞች ለእኛ ማድረግ የሚችለውን አቅሙን የሚያሳዩ ናቸው።

## ልዩነትና ክፍፍል ወደሌለበት መንግሥቱ መግባት

ግንኙነትን እንደገና የመመስረት ሁለተኛው ውጤት፤ ልዩነትና መከፋፈል ወደሌለበት መንግሥት መግባት ነው። ቀደም ሲል፤ የአብን የተስፋ ቃል መምጣት አስመልክቶ የነቢዩን ኢዮኤልን ቃል ተመልክተን ነበር፤

> "ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፣ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሣለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ህልምን ያልማሉ፤ ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈሣለሁ።"

ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሣ ቀን የጠቀሰው ይህንን ትንቢት ነው። ጴጥሮስ የሰጠውን መግለጫ ያደምጡ የነበሩ ሰዎች፤ ይህ እነርሱ ከሚያውቁት ሕይወት እጅግ ልዩነት ያለው ሆኖባቸው ነበር። የገዢው መመለስ በምድር ላይ ለሚኖሩ የማንኛውም መንግሥት ዜጎች ወንዶች ቢሆኑ ሴቶች፣ ወጣቶች ቢሆኑ አዛውንቶች ሕይወት ክብርንና ዋጋ ያለውን ያለልዩነት ያረጋገጠ ነበር። በቀደመው ጊዜ ግን፣ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ፊት መሆን የሚችለው ሊቀካህኑ ብቻ ነበር። እርሱም ቢሆን ይህን ማድረግ የሚችለው በመስዋዕቱ ደም ከተቀደሰ በኋላ ብቻ ነበር። በተጨማሪም ካህናት መሆን የሚችሉት ወንዶች ብቻ ነበሩ። ይሁን እንጂ ጴጥሮስ እዚህ የኢዮኤልን ትንቢት በመጥቀስ፤ ሥጋ በለበስ ሁሉ ላይ መንፈሱ ይፈሳል ሲል ተናገረ።

ከዚያ በኋላ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትን ይቀበሉ ዘንድ በካህኑ በኩል መሄድ አላስፈለጋቸውም። ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሔር ዘንድ



የሚመጣላቸውን ቃል ይሰጧቸው ዘንድ በነቢያት ላይ መደገፍ አላስፈለጋቸውም። መንፈሱ በእነርሱ ላይ ይፈሣል፤ ከንጉሡ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ይኖራቸዋል።

ዛሬ፤ እጅግ ብዙ ሰዎች "ከጌታ በፊት የነበሩ ልምምዶች" ብዬ በምጠራቸው ልማዶች ተይዘዋል። የገዢው መምጣት ጊዜው ያለፈባቸው (ኋላቀር) ያደርጋቸው ልማዶች ናቸው። ለምሳሌ ያህል፤ አንዳንድ ሰዎች ኃጢአታቸው ሊሰረይ የሚችለው ለካህን የተናዘዙ ብቻ እንደሆነ ያምናሉ። ይህ በኢዮኤል ዘመን የነበረ መንገድ ነው። አንድ ሰው ብቻ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ወዳለው የእግዚአብሔር መገኘት ይቀርባል፤ ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖርህ ያስችልሃል - ያም ሰው ካህኑ ነበር። ኢዮኤል እንዲህ ነበር ያለው፤ ይሁን እንጂ ንጉሡ ልጅ ይህ ሥርዓት እንዲያከትም (ያበቃለት) የሚያደርግበት ቀን ይመጣል፤ ምክንያቱም እርሱ የሚያቀርበው መስዋእት የኃጢአታችንና የዓመጻኝነታችን ሙሉ ስርየት ይሆናል። በዚህ በምትክነት በተደረገ ሞቱ ምህረትን የተቀበለ ማንኛውም ሰው፤ ወደ ንጉሥ አባት መገኘት መቅረብ ይችላል። ማንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት አያስፈልገውም፤ ምክንያቱም በገዢው በነሱ መኖር ቅድስተ ቅዱሳን በውስጣቸው ይሆናል! ምናችንም ቢሆን - ንስሃችን ይሁን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማወቃችን ቢሆን፣ ዝማሬያችን ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ጉባኤዎች መሄዳችን፤ ከእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲኖረን አያደርገንም። የንጉሡ ልጅ መስዋእት ብቻ ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፤ ገዢውም በእኛ ውስጥ እንዲኖር ያስችለዋል።

በተጨማሪም ደግሞ፤ በቀደመው ሥርዓት ውስጥ ማንኛይቱም ሴት ካህን ትሆን ዘንድ አትጠበቅም። ይሁን እንጂ ኢዮኤል፤ የጌታ ቀን በመጣ ጊዜ ንጉሡ ገዢውን ያለ ምንም ጾታዊ ልዩነት ለማንኛውም ሰው እንደሚሰጥ ይነግረናል። "ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ" ይለናል። ለምንድን ነበር "ሴቶች ልጆች" የሚለው ቃል የተጠቀሰው? ይህ የሆነው የመንግሥቱን ባህርይና መጠን ለማሳየት ነው። የኢዮኤል ትንቢት እንዲህ የሚል አንድምታ ያለው ነበር፤ ንጉሡ ወደ ምድር የሚመጣበትን ቀን አያለሁ፤ በጾታ ረገድ የተደረገውን የሰዎችን ክፍፍል ያጠፋዋል ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ትንቢትን ይናገራሉ፤ ይህም ማለት የአገር ቤቱን መንግሥት ሀሣብና ልብ በቅኝ ግዛት ላሉት መናገር ይጀምራሉ" ማለት ነው። "ትንቢት" የሚለው ቃል የግሪክ ቋንቋ ትርጉም፤ "ሊመጡ ያሉትን ሁኔታዎች አስቀድሞ መናገር"፣ "መጭውን ማሣወቅ" ወይም "በመነዳት ውስጥ ሆኖ መናገር" ማለት ነው። እግዚአብሔርን ወክሎ ሊመጡ ስላሉት ነገሮች መናገር ማለት ነው። ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ከሰማያዊው ሀሣብ ጋር መገናኘት ይችላሉ። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤

በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም። ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፣ እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።

> **በሰማያዊው መንግሥት የሰው ባህላዊ ልዮነቶች ይጠፋሉ።**

በኢዮኤል ውስጥ የሚቀጥለው ቃል፣ "ጎልማሶቻችሁ ራዕይን ያያሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁ ህልምን ያልማሉ" የሚል ነው። "ወጣት ካህናቶቻችሁ ራዕይን ያያሉ" ወይም፣ ሽማግሌ ካህናቶቻችሁ ህልምን ያልማሉ" አልነበረም ያለው። ገዢው ያላቸው ሰዎች ሁሉ ይህን ለማድረግ ህጋዊ ናቸው። ህፃን ልጅ፣ ወጣት፣ ጎልማሣ መሆንህ ወይም የቆየ ዜግነት ያለህ መሆኑ የሚያመጣው ለውጥ የለም፣ ገዢውን ወደ ሕይወትህ ልትቀበለው ትችላለህ፣ እርሱም በመንግሥታዊ ዓላማዎች ተካፋይ እንድትሆን ያደርግሃል። በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ የእድሜ ልዩነት የለም።

ከዚያም፣ ባጋጣሚ ሃሳቡን ብንዘነጋ፣ ኢዮኤል እንዲህ ይላል፣ "በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪዎቼ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ።" ንጉሡ ያለውን ነገር ራሱ እንደገና እንዲህ ሲል እየደገመው ነበር፣ "ጾታን፣ ዕድሜንና ማህበራዊ ማበላለጫዎችን አስመልክቶ በሰው ባህል ውስጥ ያሉ እንቅፋቶች ጠፍተዋል፣ በምድር ግዛት ላይ መንፈሴን ባፈሰስኩ ጊዜ፣ ማንኛውም ሰው መንፈሴን ሲሞላ ይችላል።"

እንደገናም፣ ንጉሡ *በስጋ ለባሽ ሁሉ* ላይ መንፈሱን ለማፍሰስ ይፈልጋል። በምድር ላለ ለማንኛውም ሰው ገዢው ያስፈልገዋል። ያለ መንፈስ ቅዱስ የሆኑ፣ ይገንዘቡትም አይገንዘቡትም፣ እርሱን እንዳጡት ይሰማቸዋል፣ በሕይወታቸው የጎደለውን ነገር ለመሙላት ድንገት ሲፍጨረጨሩም ያገኙታል። ከሁሉም ይልቅ ደግሞ እምነት የሌላቸው በከፍተኛ ደረጃ መንፈስ ቅዱስን ይሹታል። እንደዚሁም ደግሞ ተጠራጣሪ ሰዎች፣ የቡድሃ፣ የሂንዱና የእስልምና እምነት ተከታዮች ሁሉ ይፈልጉታል።

በበዓለ ሃምሣ ቀን መንፈስ በወረደ ጊዜ፣ ጴጥሮስ በዚያ ለተሰበሰቡት ህዝብ እንዲህ አላቸው፣ "ንስሃ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።



የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ፣ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።"

በመቀጠልም፣ ጴጥሮስ የኢየሱስ መንግሥት ተከታዮች ለሆኑት በጻፈው በሁለተኛ መልዕክቱ ውስጥ እንዲህ ብሏል፣ "ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል። የሰው ዘር ባመጸ ጊዜ ሰዎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስን አጥተዋል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉም ሰው ከእርሱ ጋር እንዲታረቅና በገዢው እንዲሞላ ይፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች የገዢውን እውቀት ለራሳቸው ለማከመቸት የሚፈልጉ ይመስላሉ። ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም የሰው ልጅ ነው። እርሱን ወደ ሕይወትህ መቀበልህ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የተሻልክ አያደርግህም። የመንግሥቱ ሥልጣንና ኃይል ባለአደራ ያደርግሃል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም። ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም።"

ሌሎችም መንፈሱን እንዲቀበሉና በተለይም ደግሞ መንግሥቱ መላውን ምድር እንዲሞላ ልንፈልግ ይገባናል። ከመንግሥቱ ጋር ተስማምቶ የመኖርን ሕይወት የሚያመጣውን ኃይል መቀበል ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ ችሮታ ነው፣ ምክንያቱም ንጉሡ ልጅ የሞተው ለሰው ልጆች ሁሉ ይህንን መብት ለመስጠት ነው። ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ፣ ለአዲሱ መንግሥት ዜጎች በጻፈው የመጀመሪያ መልዕክቱ፣ "እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፣ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ" ሲል ጽፏል። ሌሎች ሰዎች በኢየሱስ በኩል ከአብ ጋር ስለሚኖራቸው ስምምነትና የአብን የተስፋ ቃል መንገር፣ ሌሎች ሰዎች ውድ የሆነውን የመንፈስን ስጦታ እንዲቀበሉ እድል ይሰጣቸዋል።

## ለመግዛት የታደሰ ብቃት

በሦስተኛ ደረጃ፣ ግንኙነትን እንደገና መፍጠራችን በዙሪያችን ያለውን ዓለም ለመግዛት የታደሰ ብቃት ይሰጠናል። ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለኃይል የሰጠነውን ትርጉም ልብ ይሏል። ኃይል ሁኔታዎችን የመግዛትና የመቆጣጠር ብቃት ነው። መንግሥታት እያደረጉ ያሉት ዋነኛ ነገር ይሔው ነው፣ የገዢውም ወደ ምድር መምጣት ለዚሁ ዓላማ ነው።

በአንድ ቅኝ ግዛት ውስጥ የገዢው ተግባር የዚያችን ቅኝ ግዛት ሕይወት መግዛትና እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር ነበር። ከሰው ዘር የመጀመሪያው ዐመጽ ጀምሮ ዓለም እየተገዛችና በቁጥጥር ሥር ውላ ያለችው በጨለማው መንግሥት ነው፣ እናም እንደገና ሕይወት በምድር

ላይ ትክክለኛውን መስመር የሚይዘው በገዢው ኃይል በኩል ብቻ ነው። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ተከታዮች ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፎ ነበር፤ "የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና። እንደዚህ አድርጎ ለክርስቶስ የሚገዛ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው።" ገዢው ቅኝ ግዛት በሆነች ምድር ላይ ለመግዛት የሚያስፈልገንን የመንግሥቱን ሥልጣን ይሰጠናል፤ ይህም የንጉሡን ባህርይ ያንፀባርቃል።

## የውክልና ሥልጣንና የብቃት - ሥልጣን

ቀደም ባለው ምዕራፍ ውስጥ መወያየት እንደጀመርነው፤ ሁለት ዐይነት የመንግሥት ሥልጣኖች አሉ፤ (1) ህጋዊ ወይም የውክልና ሥልጣን እና (2) የብቃት - ሥልጣን ናቸው። አንደኛው አንድን ነገር ለመስራት መብት ይሰጥሃል። ሌላኛው ደግሞ ግዳጅህን ለማከናወን የሥልጣን ከለላና ኃይል እንዲሁም ብቃትን ይሰጥሃል።

ንጉሣዊ ገዢው በቅኝ ግዛት ውስጥ በንጉሡ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን አለው። በቱርክስና ካይኮስ ደሴቶች ንጉሣዊ ገዢ መኖሪያ ቤት በእንግድነት በተገኘሁበት ጊዜ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ንግሥቲቱ በቅኝ ግዛቶቹ ውስጥ ንጉሣዊ ለመኖራቸው ብቸኛ አካላዊ ማረጋገጫ የሆኑት ገዢው ብቻ ነበሩ። ሆኖም ሁሉም ሰው በታላቅ አክብሮት ይንከባከባቸዋል፤ ይሰግዳል፣ እጃቸውን ይጨብጣል፤ ክቡርነትዎ እያሰም ይጠራቸዋል። ለምን? ምክንያቱም በቱርክስና በካይኮስ እርሳቸው የእንግሊዝ አስተዳደር ስለነበሩ ነው። እርሳቸው ንጉሣዊ አገዛዝ ነበሩ። የእንግሊዝ መንግሥት የሥልጣን ከለላ አላቸው።

ንጉሣዊ ገዢ በቅኝ ግዛት ዘመን በተጨማሪ የብቃት - ሥልጣን ነበረው፤ ይህም ማለት ተግባሩን ያከናውን ዘንድ በንጉሡ ኃይል ተሰጥቶታል ማለት ነው። ገዢው የተሰጠውን ሃላፊነት ይወጣ ዘንድ ንጉሡ ሰዎችንና ቁሳቁሶችን በማቅረብ የብቃት - ሥልጣን ሰጥቶታል። በመሆኑም ገዢው፣ በመንግሥቱ ባሉ በሰውና በጥሬ ዕቃዎች ኃይል የታገዘ ነበር። ይህ ታላቅ ነጥብ ነው፤ ምክንያቱም የውክልና - ሥልጣን ቢኖርህና ነገር ግን የብቃት - ሥልጣን ባይኖርህ፤ ምናልባት ያን ያህል ብዙ ሥራዎች ተፈጽመው አታያቸውም። የመተግበር ኃይል ማለት ገዢው ምንም ነገር ቢፈልግ ንጉሡ ያቀርብለታል ማለት ነው። ለምሣሌ ያህል፤ ኢየሱስ በምድር

> **የውክልና ሥልጣን ቢኖርህና የብቃት - ሥልጣን ባይኖርህ ብዙ ነገሮች ተከናውነው አታያቸውም**



ይኖር በነበረበት ዘመን ጲላጦስ፣ በፍልስጤም እንደ ሮም መንግሥት ተጠሪነቱ፤ ሥልጣኑን የሚደግፉለት የሮም ወታደሮች ነበሩት።

እንዲሁ ደግሞ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ለማያዊው ንጉሥ ከማንኛውም ሰዋዊ ከሆነ ተቋም ወይም ኃይል ይልቅ የበለጠ ተሰሚነት ያለው ህጋዊ ሥልጣንና የብቃት - ሥልጣን ይሰጣል። ኢየሱስን በጲላጦስ ፊት ባቀረቡት ጊዜ፣ ሮማዊው ገዢ ኢየሱስን በሞት እንደሚቀጣው እንዲህ በማለት አስፈራራው፤ "ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው።" ጲላጦስ ገዢ ነበር፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ በውስጡ የሰማያዊ አስተዳደር ኃይል ተሞልቶ ንጉሥ እንደነበር አልተገነዘበም። ጲላጦስ ከነበረው ኃይል ይልቅ የማይወሰን (አለቅጥ) ኃይል ነበረው። ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ፣ ለጴጥሮስ ሊታደጉት የሚችሉ ዐስራ ሁለት ምድብ የንጉሥ ጦረኞች (የመላእክት ሠራዊት) መጥራት ይችል እንደነበር ነግሮታል። በመሆኑም ኢየሱስ ለጲላጦስ እንዲህ መልስ ሰጠው፤ "ከሰማያዊው አስተዳደር ሥልጣን ካልተሰጠህ በስተቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን የለህም። በምድር ላይ የሚያስፈልገኝን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ከመንግሥቴ ኃይል አለኝ። ይሁን እንጂ የእኔ ዓላማ ራሴን ነፃ ለማውጣት አይደለም፤ ይልቁንም በመስዋእትነቴ የሰውን ዘር ከአባት ጋር ለማስታረቅ ነው።" ይሰቀል ዘንድ በጲላጦስ እጅ ታልፎ መሰጠቱ በእርሱ ዘንድ ኃይል በመጥፋቱ አልነበረም፤ በምድር የመንግሥቱን ተልዕኮ እየፈጸመ ነበር።

ከትንሳኤው በኋላ፤ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው፣ እንደ ንጉሥ፣ ሰዎችን ከመንግሥቱ ጋር የማስማማት ተግባራቸውን እንዲወጡ የውክልና - ሥልጣንንና የብቃት - ሥልጣንን ሊሰጣቸው ኃይል እንዳለው ነው። ቃሎቹ በማቴዎስ መጽሐፍ ውስጥ ተዘግበዋል፤

> ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜም ከእናንተ ጋር ነኝ።

በዚህ ስፍራ ለተጠቀምነው "ሥልጣን" ለሚለው ቃል የግሪክ አቻ ቃል፤ "ብቃት" እና "አንድን ነገር የማድረግ ኃይል" ማለት ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ፣ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ" ባለ ጊዜ፤ "ኃይል" ለሚለው ቃል የተሰጠው የግሪክ አቻ ቃል "ዱናሚስ" ነው። ይህም ማለት "ተአምራዊ ኃይል" "ኃይል"፣ "ጉልበት" እና "ጥንካሬ" ማለት ነው። ተከታዮቹ ሁሉ የተሰጣቸውን ሃላፊነት ይወጡ ዘንድ የሰማይ መንግሥት ኃይል ይኖራቸዋል። ይህ የብቃት - ሥልጣን ወደ ሕይወታቸው የመጣው በበዓለ ሃምሣ ቀን ከገዢው መፍሰስ ጋር ነበር።

## በስሙ ኃይል

የንጉሣዊ ገዢ ሥልጣን በሚያገለግለው አገር የበላይ በሆነው ስም ነበር:: ነገሮችን በሥልጣን ማከናወን በሚያስፈልገው ጊዜ ያንን ስም ይጠቀማል:: የእርሱ የራሱ ስም ያን ያህል ክብደት የሰውም፤ በንጉሠ ነገሥቱ ስም መናገር የግድ ያስፈልገዋል::

ንጉሡ ልጅ በምድር ላይ ይሠራ የነበረው በሥልጣን ነበር፤ እናም አገዛዝን ለማስፈን ስሙን እንዴት መጠቀም እንዳለብን አሳይቶናል:: እርሱ፣ " እኔ ከራሴ አልተናገርኩምና ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትዕዛዝ ሰጠኝ" ሲል ተናግሯል:: ገዢውም በምድር ላይ የሚሠራው በተመሣሣይ መንገድ ነው:: ኢየሱስ ወደ ሰማያዊው መንግሥቱ ሊመለስ በተቃረበ ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ ይህንን ተናገረ፤

> "አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፡ *እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል::"*

> ግን እርሱ፣ የእውነት መንፈስ፣ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውንም ሁሉ ይናገራል እንጂ *ከራሱ አይናገርም*፡ የሚመጣውንም ይነግራችኋል፤ እርሱ ያከብረኛል፤ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና::"

በመሆኑም፣ መንግሥቱን ወክለን በምንሠራበት ጊዜ፤ ከአባቱ ዘንድ ሥልጣን ሁሉ የተሰጠውን የንጉሡን ልጅ የኢየሱስን ስም በመጥራት ነገሮችን ማከናወን ይገባናል:: ኢየሱስ ወደ አባቱ ለመመለስ በተዘጋጀ ጊዜ፤ ይህንን አስመልክቶ እንዲህ ሲል ተናገረ፤

> እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን እንደገና እያችኋለሁ፤ ልባችሁም ደስ ይለዋል፤ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም:: በዚያ ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም:: እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ *በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል*:: እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ፣ ትቀበሉማላችሁ . . . በዚያም ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤ እናንተ ስለወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እንደወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና:: ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተዋለሁ፣ ወደ አብም እሄዳለሁ::



በቅኝ ግዛት ሥር በነበርንበት ጊዜ፤ በባሃማስ ንጉሣዊ ገዢ የነበሩት ሰው፣ በላዩ ላይ ንግሥት ኤልሳቤጥ ሁለተኛ የሚል ስም የተቀረጸበት ማህተም ነበራቸው:: ይህን የሚመለከቱ ሁሉ፤ በማህተሙ የተጠቀመበት ሰው የእንግሊዝ መንግሥት ሥልጣንና ኃይል ከለላ እንዳለው የሚያውቁበት ምልክት ነው:: በባሃማስ ውስጥ ያተሙት ምንም ነገር ቢሆን፤ በእንግሊዝ ውስጥ ደግሞ የታተመ ይሆን ነበር:: ያንን ሥልጣን የተቀበሉት ከንግሥቲቱ ነበር::

አንድ ነገር ልብ በሉ፤ ኢየሱስ፤ "የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማይ የምትፈታው ይሆናል" ብሎ ሲናገር፤ ለተከታዮቹ ተመሳሳይ ሥልጣን መስጠቱ ነበር:: ከንጉሡ ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት ካለን፤ ገዢው የሰማያዊ መንግሥቱን ኃይል ሽፋን በመስጠት የመንግሥቱ ህጋዊ ወኪሎች መሆናችንን ያረጋግጥልናል::

> **መንግሥቱን ወክለን ስንሠራ በኢየሱስ ስም ማከናወን ይኖርብናል**

## የታደሰ ገዥነት

በአንድ መልኩ፤ የገዢው መመለስ ንጉሡ በምድር ላይ ሊያደርገው ካለው ዓላማ አንጻር ሲታይ፤ በእርግጥ የመጨረሻው ጉዳይ አይደለም:: የሱ ፍላጐት የሰው ዘር በዓለም ላይ እንደገና ገዢነት እንዲኖረው ነው:: ከመጀመሪያውም እቅዱ ይህ ነበር፤ ይህንን ዓላማውን እንደገና ተግባራዊ ለማድረግ የመቤዠት እቅዱን በተግባር ፈጸመ:: ይህንን ነጥብ እየዘነጋን እንደሆንንና ንጉሡ እንደርስበት ዘንድ ከሚፈልገው ስፍራ ሳንደርስ ከወዲሁ እንደቆምን እምናለሁ:: እንደገናም፣ በቀጥታ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንድንሄድ ብቻ ወደ መንግሥቱ የተጠራን አይደለንም:: የተጠራነው (ተለይተን የወጣነው) በምድር ላይ ልንሠራው ለተሰጠን ሥራ ነው::

ጥቂት የማይባሉ ክርስቲያኖች ዘመናቸውን የሚጨርሱት ኢየሱስ በመስቀሉ ላይ በፈጸመው መስዋእትነት ላይ ብቻ በማተኮር ነው፤ እናም እግዚአብሐር የሰጠውን የተስፋ ቃል ማለትም የመንፈሱን መፍሰስ ወደ ሕይወታቸው መቀበል እንዳለባቸው አይገነዘቡትም:: ሌሎች ደግሞ እንደተስፋ ቃሉ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ተቀብለዋል፤ ይሁን እንጂ ይህ ከመንግሥቱ ሕይወት ጋር ያለውን ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ አይረዱትም:: ሁላችንም ብንሆን በምድር ላይ ለእግዚአብሔር መንግሥት ገዥነትን እየተለማመድን ዋንኛ ወደ ሆነው ነጥብ ልንቀሳቀስ ያስፈልገናል:: ይህ እግዚአብሔር ለሰው ዘር የሰጠው የመነሻ ሥራ (ግዳጅ) ነው፤ እርሱም ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ ነው:: አንድ ጊዜ

ሉሲፈርና የጨለማው መንግሥት ሙሉ ለሙሉ በሰማያዊው ንጉሥ ሲሸነፉ፤ በርግጥ "ዘፍጥረት ሁለት" ይኖረናል። ንጉሡ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚኖሩ ቃል ገብቷል፤ በዚያም የሰማያዊውን መንግሥት ክብር ሙሉ ለሙሉ እናንጸባርቃለን። ከዚህ በታች የምንጠቅሳቸው ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ቃሎች የተወሰዱ ስለ አዲሱ መንግሥት የሚያብራሩ መግለጫዎች ናቸው።

ነገር ግን ጻድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።

"አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ፤ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፤ ባህርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ፤ ታላቅም ድምጽ ከሰማይ እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል፣ እነርሱም ህዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከአይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ ሀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲያ አይሆንም፤ የቀደመው ሥርዓት አልፏልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።

## በሕይወት ላይ የተለወጠ አመለካከት

ዐራተኛ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በእውነት እየኖሩ አለመለወጥ በጭራሽ የማይቻል ነገር ነው። የሰው መንፈስ፣ ነፍስና አካል እንደገና በአግባቡ ተቀናጅተው የሚሠሩበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ ምክንያቱም ማንም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው ቢሆን እንደገና እውነተኛ ሰው ሆኗል።

ለምሳሌ ያህል፤ በአመለካከታችን ላይ ታላቅ የሆነ ለውጥ ይከሰታል። ቀደም ሲል እንዳየነው ከዐመጽ በፊት የአዳም እውቀት የመንፈሱ ባሪያ ነበር። ከዚያ በኋላ፤ መንፈሱ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሙት በሆነ ጊዜ፤ እውቀቱና ስሜቱ ስፍራውን በመያዛቸው ገዢዎች ሆኑ። ከንጉሡ ጋር ያልተሰለፉና መንፈሱንም ያልተቀበሉ ሁሉም የሰው ልጆች ራሳቸውን የሚያገኙት በዚሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነው።

> በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በእውነት እየኖሩ አለመለወጥ በጭራሽ የማይቻል ነገር ነው።

ገዢው በአንድ ሰው ውስጥ ለመኖር በሚመጣበት ጊዜ፤ በዚህ ዓለም መንግሥት ተጽእኖ የተደረገበትን የዚያን ሰው የአመለካከት ቅኝት ፈጥኖ



ማጥቃት የሚጀምረው በዚህ ምክንያት ነው። እንደገናም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የሰማያዊው መንግሥት ህገ መንግሥት ብለን ልንጠራው የምንችለው በማስጠንቀቂያ ቃላት የሚመክረን በዚህ ምክንያት ነው፤

"ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በስጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በእርሳቸው ይቃወማሉ።"

"ነገር ግን እሳለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የስጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ"

"የሰውንም ሃሣብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን፤ ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን።"

እነኚህ መግለጫዎች ሁሉ የሚያመለክቱት በሰማያዊው መንግሥት የአመለካከት ቅኝትና በጨለማው መንግሥት የአመለካከት ቅኝት መካከል ያለውን የከረረ ግጭት ነው።

አመለካከታችን፤ የንጉሡን አስተሳሰብና መንገዶች በመረዳትና በመቀበል እንዲሁም ገዢው ለሕይወታችን የሚሰጠውን ትእዛዝና መመሪያ በመቀበል ሊለወጥ ይገባዋል። ሕይወትን በቀደመው የአመለካከት ቅኝታችን ልናስተናግዳት ብንሞክር፤ የመንግሥቱ የአስተሳሰብ ባህርይ ባልሆነ የቀደመ አመለካከት ላይ እንወድቃለን። ገዢው የንጉሡን መንገዶች እንዲያስተምረን እንፈልጋለን።

የምንኖርበትን አዲስ መንገድ በማስተማር ገዢው ውስጣዊ የአኗኗር ባህላችንን ይለውጠዋል። የንጉሡን አስተሳሰብና መንገዶች ይገልጥልናል፣ በመሆኑም እንረዳቸዋለን፣ እንከተላቸዋለንም። ንጉሡ እንዲህ ሲል የገለጸውን ልብ በሉ፤ "ሀሣቤ እንደ ሀሣባችሁ መንገዳችሁም እንደመንገዴ አይደለምና . . . ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ ሀሣቤም ከሀሣባችሁ ከፍ ያለ ነው"። በዚህ ስፍራ "መንገድ" የሚለው ቃል "እውራ ጎዳናን" የሚያመለክት ሲሆን ይህም የሕይወትን ጉዞ ወይም የአተገባበር ስልትን አመለካች ሆኖ በተምሳሌት የቀረበ ነው። በሌላ አገላለጽ፤ ስለ ሕይወት ዘይቤ የሚናገር ነው። እናም ምድርን ለመግዛት ይረዳን ዘንድ የንጉሡን የመሰለ የሕይወት ዘይቤ እንዲኖረን ካስፈለገ የአመለካከት ቅኝታችንን ልንለውጥ ይገባናል። ከዚያ በኋላ እንደ ቀደመው የጨለማ መንግሥት አሮጌ ባህል ሳይሆን፤ እንደ ሰማያዊው መንግሥት አዲስ የሕይወት ባህል ለመኖር እንችላለን።

ቀደም ባለው ምዕራፍ ውስጥ፤ የአንድ ቅኝ ግዛት ዜጎች የተገዙለትን መንግሥት ታሪክ እንዴት እንዲማሩ እንደሚደረግ አውርተናል። በተመሣሣይ መንገድ ንጉሡ ከእርሱ መንግሥት ውጭ በነበርክበት ጊዜ የነበረውን የቀደመ ሕይወት እንድትረሣው ይፈልጋል። በሰማያዊው

መንግሥት ውስጥ የራስህን አዲስ ታሪክ እንድትገነባ ይሻል። በሰው ትውልድ እና በግል ያለን ታሪክ የዐመጸኛነት፣ የውድቀት፣ የተዛባና ዓላማውን የሣተ የሞት ታሪክ ነው። ነገር ግን በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ አዲስ በተወለድን ጊዜ ተቀባይነት ያለው (የመዋጀት) ታሪክ ያለን ሆነናል። አሁን እንደገና ዓላማና አቅም ያለን ሆነናል። ታሪካችን የሕይወት ያውም የዘላለም ሕይወት ታሪክ ነው። ገዢውም ይህንን ታሪካችንን ያለማቋረጥ እንድናጠናው ያበረታታናል፤ በመሆኑም ከጳውሎስ ጋር፤ "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏልና፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል" ማለት እንችላለን።

ይህም ማለት ከቀደመው የኃጢአት ታሪካችን ሙሉ ለሙሉ የተሰየ ትምህርት ልንማር ይጠበቅብናል ማለት ነው። የዕብራውያን መጽሐፍ እንዲህ ሲል ይዘግባል፤ ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ። ህጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ"፣ ካለ በኋላ እንዲህ ሲል ሌላ ሀሣብ ያክልበታል፤ "ዐመጻቸውንና ኃጢአታቸውንም ደግሞ አላስብም።" ንጉሡ እንዲህ ነው የሚለው፤ "ተመልከቱ፤ ኃጢአታችሁ ተወግዷል። ከጨለማው መንግሥት እንዳመለጣችሁ በእውነት አስተውሉ።"

የመንግሥቱ ታሪክ የሆነው "ጽድቅ፣ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሆነው ደስታ" ያንተ ነው። ሉሲፈር "አንተ ኃጢአተኛ ነህ" እያለ በከሰሰህ ጊዜ ሁሉ፤ "በንጉሡ ልጅ ደም ተቤዥቻለሁ። ኃጢአቴን ሁሉ አንጽቶታል፣ አጥቦም አስወግዶታል" ብለህ ልትመልስለት ትችላለህ።

የዕብራውያን መጽሐፍ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤ "ከክፉ ህሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውሃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ። ልባችን እንኳ በነፃ አውጪአችን ደም ነጽቷል። በተጨማሪም አንድ ሰው ያለፈ ታሪክህን ቢያነሳብህ፤ "እያወራህ ያለኸው ስለሞተ ሰው ነው። በአዲስ ሕይወት ልመላለስ ከሞት ተነስቻለሁ" ልትለው ትችላለህ። በመሆኑም ገዢው የራስህ የሆነውን አዲሱን የመንግሥቱን ታሪክ ያስተምርሃል፤ ንጉሡ ለአንተ ያለው ፈቃድ ይህ ነው።

ጳውሎስም እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ።" በዐመጽ፣ በወንጀል፣ በድብርት፣ በፍርሃት፣ በግራ መጋባትና በጭንቀት ከተሞላ የአመለካከት ቅኝት ነጻ ወጥተን በጽድቅ፣ በሰላምና በመንፈስ ቅዱስ ደስታ በተሞላ ሕይወት ለመመላለስ አዕምሯችን መሰወጥ ያስፈልገዋል።

ገዢው በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት መገኘትና ባህርይ መሆኑን አስተውሉ። ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስን የተቀበላችሁ ከሆነ፤ ኢየሱስ እንዳደረገው፤ "እኔን ያየ አብን አይቷል" ለማለት የምትችሉ



ትሆናላችሁ። ወደ ገዢው ባህል ስለመሸጋገራችን በይበልጥ ዘርዘር አድርገን በምዕራፍ ዐሥራ አንድ ላይ የምንመለከተው ይሆናል።

## አዲስ ጀግንነትና በራስ መተማመን

የኢየሱስ ደቀመዝሙር የሆነው ዮሐንስ፤ ከዋናው መምህሩ ከኢየሱስ የተማረውን ስመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የመንግስቱ ዜጎች እንዲህ ሲል አስተምሯል፤ "ልጆቼ ሆይ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ፤ አሸንፋችኋልም (የጨለማውን መንግሥት)፤ በዓለም ካለው ይልቅ (ሉሲፈርና ተከታዮቹ) ይቂቅ በእናንተ ያለው (ገዢው) ታላቅ ነውና።" መንፈሱ በእናንተ ውስጥ ሲኖር፤ መንግሥተ ሰማይ አገር ቤታችሁ ይሆናል፤ የመንግሥቱም ሥልጣንና ኃይል ይኖራችኋል። ከንጉሡ የላቀ ኃይልና አቅርቦት (ሀብት) ያለው በዚህ ዓለም ላይ ምንም ነገር ወይም ማንም የለም። በመሆኑም፤ በምድር ላይ ሊያስፈራራህ ወይም ሊያጠቃህ በሚሞክር በማናቸውም ነገር "አጠፋለሁ" ብለህ ልትሰጋ አይገባህም። በዚህ ጉዳይ ላይ ኢየሱስ ያስተማረውን ባለመድኃኒቱ ሉቃስ እንዲህ ሲል ይዘግበዋል፤

ለእናንተ ለወዳጆቼ እላችኋለሁ፤ ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም አንድ ስንኳን የሚበልጥ ሊያደርጉ የማይችሉትን አትፍሩ። እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ፤ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ። አዎን እላችኋለሁ እርሱን ፍሩ። አምስት ድንቢጦች በዐስር ሣንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ስንኳ በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም። ነገር ግን የእናንተ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ የተቆጠረ ነው። እንግዲያስ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ። እላችሁማለሁ በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል።

ሰውን መፍራት በመንግሥተ ሰማይ ዜግነታችን ላይ እንደተጠመደ መጥመድ ነው፤ ምክንያቱም ከመንግሥቱ የአመለካከት ቅኝትና ደረጃ ውጭ እንድንኖር ያደርገናል። ስንፈራ በስልጣንና በኃይል ነገሮችን ልንተገበር አንችልም፤ ይልቁንም በስጋትና በፍርሃት እናደርጋቸዋለን። ጳውሎስ "ንጉሡ የሰጠን የፍርሃትን መንፈስ ሳይሆን፤ የፍቅርን፣ የኃይልንና ራስን የመግዛት መንፈስ" እንደሆነ ጽፏል። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሳንናወጥ ፅንተን መቆም እንችላለን፤ ምክንያቱም በገዢው ህልውና በኩል ንጉሡ በእኛ ውስጥ እንደሚኖር እናውቃለን።

> መንፈሱ በእናንተ ውስጥ ሲኖር፤ መንግሥተ ሰማይ አገር ቤታችሁ ይሆናል፤ የመንግሥቱም ኃይል ይኖራችኋል።

## ከሕይወት ዓላማ ጋር እንደገና መገናኘት

ገዢው በአንድ ሰው ውስጥ ለመኖር ሲመጣ፤ ያ ሰው ከተፈጠረለት የሕይወት ተልዕኮ ጋር እንዲገናኝ ይረዳዋል። ነቢዩ ኢዮኤል ሽማግሌዎች ህልም እንደሚያልሙ፣ ጎልማሶች ራዕይ እንደሚያዩ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆች የንጉሡን ፈቃድ እንደሚተነብዩ ይናገራል። እኔ ለህልም የምሰጠው ትርጉም ወደፊት ሲከናወን ልታዩት የምትችሉት አንድ ነገር እንደሆነ ነው። ምናልባትም እናንተ ሙሉ ለሙሉ ሲፈጸም በሕይወት ኖራችሁ ላታዩት እንኳን ትችላላችሁ። ራዕይ ግን ልታደርጉት የምታዩት ነገር ነው፤ በሕይወት ዘመናችሁ ልታጠናቅቁ የምትችሉትም ነው።

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን"። ገዢው በእኛ ውስጥ ሊኖር በመጣ ጊዜ አዲስ ፍጥረት ሆነናል። በመሆኑም ገና ከመፈጠራችን በፊት እንኳን ንጉሡ እንተገብረው ዘንድ ለእኛ ያቀደውን መልካም ሥራ በመንግሥቱ ውስጥ ለመሥራት መጀመር እንችላለን። ገዢው፤ ሽማግሌዎች አጥተናል ብለው ያሰቡትን ለመጪው ዘመን የሚሆነውን ህልም እንደገና ይሰጣቸዋል። ለጎልማሶች ደግሞ በማይረባ ነገር ላይ ጊዜያቸውንና ኃይላቸውን እንዳያባክኑ ይረዳቸው ዘንድ ራዕይን ይሰጣቸዋል። በተሰጡን የተለየዩ ስጦታዎቻችን አማካይነት እኛን ሁላችንን ገዢዎች ያደርገናል።

አንዳንድ ሰዎች ገዢው በሕይወታቸው የሚኖርበትን ትርጉም ይስቱታል። ቀደም ብለን እንዳየነው፣ እርሱ የመጣው "ደስ የሚል ስሜት" እንዲሰማቸው፤ ወይም የሰዎችን አትኩሮት ወደ እነርሱ ለመሣብ የሚችሉበትን ብቃት ሊሰጣቸው ይመስላቸዋል። ይልቅስ፣ እርሱ የመጣው እኛ ብቻ ልናከናውን የምንችለውን የአንድ ነገር ራዕይ ወይም ህልም ሊሰጠን ነው፤ ምክንያቱም ይህ ነገር በምድር ላይ እንድንሠራው ለኛ እርሱ የሰጠን የተለየ ሥራ ነው። ይህ የተለየ ሥራ ይተገበር ዘንድ ኃይልን ሊሰጠን መጣ።

በተጨማሪም፤ ነጻታችሁና ገዢውንም ተቀብላችሁ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የመንግሥቱን ሕይወት ለመኖር ኃይልን ሊሰጣችሁ እንደሚፈልግ ላታውቁ ትችላላችሁ። ስለዚህም የተፈጠራችሁለትን ታላቅ ሥራ ለመስራት እንድትችሉ፣ ከመንግሥቱ ባህርይ ጋር ተጻራሪ የሆኑ ዝንባሌዎቻችሁንና መሻቶቻችሁን በመንፈሱ ሥልጣንና ኃይል አማካይነት ከማሸነፍ ይልቅ ዘወትር ከእነርሱ ጋር ስትታገሉ ጊዜያችሁን ሁሉ ታባክናላችሁ። ኃይሉ በእናንተ በኩል ስለሚሠራ ሕይወታችሁ በመንግሥቱ አገዛዝ ሥር ለመሆኑ ማስረጃ ማሳየት (ማቅረብ) ትችላላችሁ። ገዢው የመጣው "ለሥራ" አስፈላጊ የሆነውን ኃይል ሊሰጣችሁ ነው። እርሱ በምድር ያለው በእናንተ ራዕይ ወይም ሕልም



አማካይነት ምድር ለሰማይ እንድትገዛ ለመጫን ወይም ተፅዕኖ ለማድረግ ነው።

## ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር ተግባቦት

በመጨረሻ፤ ግን በጣም ከፍ ባለ መልኩ፤ የገዢው መመለስ ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ተግባቦት መፍጠር የምንችልበትን ብቃት ይሰጠናል። የሰማዩን መንግሥት ወደ ምድር ለማምጣትና በእርሱም መግዛት የምንችለው ከንጉሡ ዘንድ ግልጽ መመሪያ ካገኘን ብቻ ነው። የአንድ መንግሥት የውክልና ሥልጣን በአግባቡ ሊሠራ የሚችለው፤ የንጉሡ ዓላማ፤ ፍቃድና መሻት የውክልና ሥልጣን ለተሰጠው አካል ሲተላለፍ ብቻ ነው።

ንጉሡ ለምድር ያለው መሻት በገዢው በኩል ለምክትል ገዢዎቹ መተላለፍና በእነርሱም አማካይነት ተግባራዊ ሊሆን ያስፈልገዋል። ገዢው በሌለበት ወይም ከገዢው ጋር ያለው ተግባቦት ችላ በተባለ ጊዜ፤ የንጉሡ አገዛዝ በምድር ላይ አይኖርም (አይታሰብም)። አንዳንድ የአስተዳደሩ መገለጫዎች (መገኘቶች) ሊታዩ ይገባቸዋል። መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ የሰማያዊው መንግሥት ቁልፍ የሆነው ስለዚህ ነው። ገዢው በሰው ዘር አገዛዝ በኩል የእግዚአብሔር ሀሣብ የመገለጫ ወኪል ነው።

## ወደ ንጉሡ መድረስ

እስኪ እሁን ደግሞ፤ ከንጉሡ ጋር ለሚኖረን ተግባቦት ገዢው እንዴት ወሳኝ እንደሆነ በምሳሌ ላብራራው። በባሃማስ በቅኝ ግዛቱ ዘመን፤ *ማንኛውም ሰው*፤ ደግሜ እላለሁ "*ማንኛውም ሰው*" የምክር ቤት አባል ቢሆን፣ የአገር ውስጥ ኮሚሽነሮች ወይም ጳጳሱ ቢሆኑ፣ ወደ እንግሊዝ ሄደው ንግሥቲቱን ለማየት ቢፈልጉ፤ በቅድሚያ በንጉሣዊው ገዢ በኩል ካልሄዱ በቀር በፍጹም ወደ ንግሥቲቱ ሊደርሱ አይችሉም ነበር። ይህ ደግሞ ለቅኝ ግዛቲቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጭምር ተመሳሳይ ነበር።

ከንጉሥ አባት ጋር ባለን ግንኙነትም ቢሆን ተመሳሳይ የሆነ ሂደት ነው ተግባራዊ የሚሆነው። አንዳንድ ሰዎች በትምህርት ደረጃቸው፤ ወይም በባለጠግነታቸው ወይም ለድሆች ካደረጉት ታላቅ ነገር የተነሣ ወደ ሰማያዊው ዙፋን ለመቅረብ (ለመድረስ) እንደሚችሉ ያስባሉ። በእኛ ምትክ በመሞት መንገዱን በከፈተልን፣ በንጉሡ - ልጅ በኩል ካልሆነ፣ በአብ ፊት ልንናገርበትና ልንሰማበት በሚያስችለን በገዢው ኃይል በኩል ካላደረግን፤ በንጉሥ - አባት ዘንድ ሰሚ (አድማጭ) ማግኘት አንችልም።

በባሃማስ ወዳሉት ገዢ ዘንድ በመሄድ ንግሥቲቱን ለማየት ፍቃድ ስትጠይቁ፤ በዚያ ስለሚኖራችሁ ቆይታና ተግባር ስለማንነታችሁ ጭምር ገዢው መልዕክትን ወደ እንግሊዝ ያስተላልፋሉ፤ የናሳሁ መንግሥት

ገዢ ደግሞ አስፈላጊውን የመውጫ ፍቃድ ከሰጠ መግባት ትችላላችሁ:: እንደዚሁ ደግሞ፤ ንጉሡ - ልጅ የመግቢያውን ፈቃድ ከሰጣችሁና ጥያቄያችሁንና መሻታችሁን በገዢው በኩል ባላችሁ ግንኙነት ለማቅረብ የምትታመኑ ከሆነ፤ በሰማያዊው ቤተመንግሥት በውስጠኛው ክፍል ወዳለው ወደንጉሥ - አባት ዙፋን ችሎት በቀጥታ መሄድ ትችላላችሁ:: የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሀፊ እንዳጻፈው፤ "እንግዲህ ምህረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ::"

ጆን ኤፍ. ኬኔዲ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ጊዜ፤ ክብ ቅርጽ ባለው ቢሮአቸው ውስጥ ተቀምጠው ከሚኒስትሮቻቸው ጋር ስብሰባ ያደርጉ እንደነበር ሰምቻለሁ:: በዚያ ጊዜ በዓለም ውስጥ ስለነበረው እጅግ አደገኛ ሁኔታ ይወያዩ ነበር፤ ፀረ ካስትሮ የሆኑ ኃይላት በኩባ መንግሥት ላይ መጋቢት 17 1961 ባደረጉት ወረራ መነሻነት ኩባና የሶቪየት ህብረት የኒኩሊየር መሣሪያ ሊጠቀሙ ይችላሉ የሚል ስጋት አንዱ የውይይታቸው አጀንዳ ነበር:: በአስተዳደር ዘመናቸው ካደረጓቸው ጉባኤዎች ሁሉ ይህኛው እጅግ አሳሳቢ በሆነ ጉዳይ ላይ የተደረገ ስብሰባ ነበር:: ታሪኩ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፤ የስብሰባው አዳራሽ ቢሮ በድንገት ተከፈተ፤ አንድ ትንሽ ልጅ በክፍሉ ውስጥ በሚኒስትሮቹ ዙሪያ እየሮጠ አዳራሹን አቋረጠና በፕሬዚዳንቱ ጭን ላይ በደረቱ ተኛ:: እነኛ እጅግ የተከበሩ የካቢኔ አባላት ሁሉ በድንገት ጸጥ አሉ:: ይህ ትንሽ ልጅ በዓለም ላይ እጅግ ኃያልና ተደማጭነት ወዳለው - ወደ አባቱ ቀና ብሎ ተመለከተና - "አባባ፤ እነኚህ ሰዎች እነማን ናቸው?" ሲል ጠየቀ:: ፕሬዚዳንቱም፤ "ልጄ፣ እነኝህ ሚኒስትሮቼ ናቸው" ሲሉ መለሱለት፤ ልጁም በክፍሉ ያሉትን ኃያል ሰዎችን ከተመለከተ በኋላ ወደ አባቱ በጣቱ እያመለከተ፤ "ይህ የእኔ አባት ነው" አለ:: በዚያ ጊዜ ውስጥ ፕሬዚዳንቱ ከነማን ጋር ለስብሰባ መቀመጣቸው ቁም ነገር ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አልነበረም:: ልጁ ለአባቱ ፍፁማዊ የሆነ ቅርበት ስላለው ለማነጋገር ሙሉ መብት ነበረው:: ከንጉሥ - አባታችን ጋር ያለን ግንኙነትም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው::

> የሰማዩን መንግሥት ወደ ምድር ለማምጣት የምንችለው ከንጉሡ ዘንድ ግልጽ መመሪያ ካገኘን ብቻ ነው::

## የንጉሡን ፈቃድ መስማት

ንጉሡ ዜጎቹን ሲገናኝ በፈለገ ጊዜ፣ ገዢው በዚህ ሂደት ተሳትፎአል:: ለምሳሌ፣ በማንኛውም ጊዜ የእንግሊዝ ንግሥት ለጉብኝት ወደ ባሃማስ ስትመጣ፣ ወደ ባሃማስ እንደምትመጣ ራስዋ በቀጥታ ለሕዝቡ አታሳውቅም:: እርስዋ ለንጉሣዊ ገዢው ትነግራለች፣ እርሱ ደግሞ ለሕዝቡ ይናገራል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በማንኛውም ጊዜ ሰማያዊው ንጉሥ ምንም ነገር በምድር ላይ ለማድረግ ሲፈልግ፣ ለኛ በሚገልጽልን በገዢው በኩል ያደርጋል:: ጳውሎስ እንደ ጻፈው፣ "በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም::" በሕይወታችን የገዢው መገኘት፣ ንጉሡ ለኛ ያለውን ፈቃድ እንድንሰማና እንድናውቅ ያስችለናል::

ከንጉሡ መስማት ማለት በእውነቱ ለመንግሥቱ ዜጎች ተገቢ የሆነ ጉዳይ ነው፣ ለዚህ ጉዳይ ኢየሱስ አርአያ እንደሆነልንም ተቀምጦልናል:: አዲስ ኪዳን እንደሚነግረን፣ ኢየሱስ ሁልጊዜ የንጉሥ- አባቱን መመሪያ ለመስማት ከደቀመዛሙርት ተለይቶ ብቻውን ይሆን ነበር:: የአስተዳደሩን ሥራ ለማከናወን ፀሎት የርሱ ብቸኛ መንገድ ነበር:: በእውነቱ እርሱን በትክክል ለመወከል፣ ከሰማያዊ አስተዳደር መመሪያዎችን ለመቀበል መቻል ያስፈልጋል:: ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ፣ "ስትፀልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ ... አንተ ግን ስትፀልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ፀልይ" አላቸው:: ስለዚህ፣ ፀሎት የምርጫ ጉዳይ አይደለም፤ ነገር ግን የየዕለት አስተዳደራዊ ተግባቦት (ግንኙነት) ነው:: በገዢው እርዳታ ንጉሡን ልንጠይቀው ይገባል፣ "ዛሬ ምን እንዲደረግ ትፈልጋለህ?" ብለን መጠየቅ አለብን:: እናም ለማዳመጥና ለመመለስ መዘጋጀት አለብን::

## ትክክለኛ በሆነ ግንኙነት (ዝምድና) ውስጥ መቆየት

ንጉሡን ማምለክ ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር የሚደረግ የተግባቦት ሌላኛው መልክ ነው:: ብዙ ሰዎች የአምልኮ ሥርዓት ያደርጋሉ፤ ሥርዓቱ ከንጉሡ ጋር ያለው ትክክለኛ ግንኙነት ተጠብቆ እንዲቆይ በመፈለግ ነው፣ በርግጥ ይህ ከበላይ ገዢአችን ጋር በማይቋረጥ ግንኙነትና ህብረት ለመቆየትና ለአስተዳደሩ ክብር ለመስጠት እንድንችል የሚያደርግ መንገድ ነው::

አምልኮ በምድር ላይ፣ ከሰማያዊው አስተዳደር ውጭ፣ የየራሳችንን መንግሥት እንዳንመሠርት ይጠብቀናል፤ ምክንያቱም በአምልኳችን የእርሱ መሻትና ፈቃድ በሕይወታችን የበላይ መሆኑን እውቅና እንሰጣለን፤ እናረጋግጣለንም:: አሁን በምድር ላይ የምንኖርበት የመጨረሻው ምክንያት የአስተዳደሩ ፍላጎት መሆኑን እናረጋግጣለን::

በገዢው በኩል ከመንግሥቱ ጋር የመገናኘት አስፈላጊነት በሚቀጥሉት ምዕራፎች የመንፈስ ቅዱስን ባህርይና ሚና እንዲሁም በየግል ሕይወታችን ባህልና በጥቅሉም በምድር ባለው ባህል ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ስንቃኝ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ይመጣል::